“በኢትዮጵያ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ እልባት ሲያገኝ”

- ዶክተር ጌታቸው ተድላ
የግብርና ተመራማሪና ደራሲ



ገጽ 6

“ኮሮና የለም” ከሚል አስተሳሰብ እንውጣ

ገጽ 8

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
81ኛ ዓመት ቁጥር 274 ሰኔ 4 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ሕወሓት በፈጸማቸው ወንጀሎች ላይ ምርመራ እንዲካሄድ መንግሥት ለአውሮፓ ህብረት ጥያቄ ሲያቀርብ ነው



ፎቶ፡ፀሐይ ንጉሤ

ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት በአማራና አፋር ክልሎች በፈጸማቸው አሰቃቂ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ወንጀሎች ላይ የጥምር ምርመራ እንዲካሄድ ለአውሮፓ ሕብረት ጥያቄ እንደሚያቀርብ የፌዴራል መንግሥት አስታወቀ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ ትናንትና በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በአማራና አፋር ክልሎች በወረራ በቆየባቸው ጊዜያት የፈጸማቸውን አሰቃቂ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ወንጀሎች በተመለከተ አስፈላጊው የጥምር ማጣራት እንዲካሄድ መንግሥት ለአውሮፓ ሕብረት ጥያቄ ያቀርባል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ ከአውሮፓ ሕብረት 27 አባል አገራት የተውጣጡ የሕብረቱ የፖለቲካና የደህንነት ኮሚቴ አባል አምባሳደሮች ወደኢትዮጵያ መጥተዋል። በቆይታቸውም ከፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ምክክር ያደርጋሉ።

የሕብረቱ አምባሳደሮች ከኢትዮጵያ መንግሥት ኃላፊዎች ጋር በሚኖራቸው ውይይት አሸባሪው ሕወሓት በፈጸማቸው አሰቃቂ ወንጀሎች ላይ ገለልተኛ በሆነ መንገድ እንዲጣራ መንግሥት ጥያቄ እንደሚያቀርብ ሚኒስትር ዴኤታዋ ተናግረዋል ።

በተጨማሪም የሰብዓዊ ድጋፍን በተመለከተ ሕብረቱ

ሕወሓት በፈጸማቸው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






ፎቶ፡ሐዱሽ አብርሐ

“ኢትዮጵያ ሽብርተኝነትን ለመቀልበስ ቀጠናዊና ዓለምአቀፋዊ አጋርነትን ወደላቀ ደረጃ እያሳደገች ትገኛለች”

- አቶ ተመስገን ጥሩነህ (የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል)

ገጽ 4

# መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ ያለገደብ እርዳታ እንዲደርስ ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ነው

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ ያለገደብ እርዳታ እንዲደርስ ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ ።

የሚኒስቴሩ ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በወቅታዊ ዲፕሎማሲያዊ ጉዳዮች ዙሪያ ትናንት መግለጫ ሲሰጡ እንዳስታወቁት፤ ለትግራይ ሕዝብ የሰብዓዊ እርዳታ መሄዱን ይቀጥላል ። ወደ ትግራይ ክልል እርዳታ እንዲደርስ መንግሥት ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ይገኛል ። ከማንኛውም ዓለም አቀፍ ተቋምና ከማንኛውም የዜጎች ተሚጋች ድርጅት በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ ይቀርበዋል ብለዋል ።

ወደ ትግራይ የሚደረገው የሰብዓዊ እርዳታ ማጓጓዝ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት አምባሳደር ዲና፤ አሁን ያለው ችግር ባይፈጠር እንደ ሀገር ጥሩ ነበር፤ ነገር ግን ችግሩ ስለተፈጠረ እርዳታ እንደሚያስፈልግ መንግሥት አምኖበት ዕርዳታው ያለገደብ እየሄደ ነው ። በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ገልጸዋል ።



አምባሳደር ዲና ሙፍቲ

ባለፉት ሳምንታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ከበርካታ የዓለም አቀፍ

መንግሥት ለትግራይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ‹‹ማህበራዊ እርሻን በማስፋፋት ምርታማነትን ማሳደግ ያስፈልጋል››

- ዶክተር ጌታቸው ተድላ
የግብርና ተመራማሪ

ማህሌት አብዱል

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ሁሉም ክልሎች የማህበራዊ እርሻ ስርዓትን በማስፋፋት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ የግብርና ተመራማሪና ደራሲ ዶክተር ጌታቸው ተድላ አስታወቁ ። አርሶአደሩ እንደልቡ እንዲያለማም የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ እልባት ሊሰጠው እንደሚገባም አመልክተዋል ።

የግብርና ተመራማሪና ደራሲ ዶክተር ጌታቸው ተድላ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤ አሁን ላይ በተወሰኑ አካባቢዎች የተጀመረውን የኩታ ገጠም እርሻን ወደ ማህበራዊ እርሻ በማስፋፋት የግብርናን ምርታማነት ማሳደግ ያስፈልጋል ። ይህ ዘዴ መሬትን



ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

‹‹ማህበራዊ እርሻን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ገጽ 9

ሠልስቱ የአመራር ተግዳሮቶች



## ‹‹በነዳጅ ላይ የዋጋ ማስተካከያ መደረጉ ህገወጥ የነዳጅ ንግድን ለመከላከል ያስችላል ››

- ፕሮፌሰር ብርሃኑ ቡርጂ
የምጣኔ ሀብት ምሁር

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በነዳጅ ላይ የዋጋ ማስተካከያ መደረጉ ከኢትዮጵያ በህገወጥ መንገድ ወደተለያዩ ሀገራት የሚወጣውን ነዳጅ ለመከላከልና ሀገሪቱ የምታጣውን ከፍተኛ ሃብት ለማዳን ያስችላል ሲሉ የኢኮኖሚ ባለሙያው ፕሮፌሰር ብርሃኑ ቡርጂ አስታወቁ ።

በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ምጣኔ ሀብት መምህር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ቡርጂ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በሀገሪቱ የሚታየውን የዋጋ ግሽበት ለመከላከል ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ማስገባት ብቻ ሳይሆን ምርቱንም በህገወጥ መንገድ ከሀገር እንዳይወጣ ቁጥጥር ማድረግ ይገባል ። መንግሥት እስከ አሁን ድረስ ነዳጅ በድጎማ እያቀረበ መሆኑ መልካም ነገር ቢሆንም ለሀገር በሚጠቅም መልኩ ጥቅም ላይ አለመዋሉ ችግር እያስከተለ ነው ብለዋል ።

እንደ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ገለጻ ኢትዮጵያ መንግሥት ኅብረተሰቡ በአማካይ በሊትር 38 ብር ነዳጅ ሲያቀርብ ጎረቤት ሀገሮች እስከ 70 ብር ይሸጣሉ ። ህገ ወጥ ነጋዴዎች ልዩነቱን ለማግኘት በስንት ድጎማ ሀገር ውስጥ የገባውን በህገወጥ መልኩ ከሀገር እንዲወጣ በማድረግ ህብረተሰቡ ለከፋ ነዳጅ ዋጋ ንረት እየተጋለጠ ይገኛል ።

በቀጣይ ከሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ጎን ለጎንም ችግሩን ለመከላከል የሚያስችል አቅም መፍጠር ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የተደራጀ የጸጥታ መዋቅር ያላት ሀገር እንደመሆኗ መጠን በድንበር አካባቢ ነዳጅን ከሀገር በሚያስኮበልሉ ህገወጥ ነጋዴዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅባታል ። ቦቴ ነዳጅ ጭኖ ከሀገር ሲያወጣ አይታይም ማለት ስለማይቻል እስከ ሚሊሻው ድረስ ቁጥጥር መደረግ አለበት ብለዋል ።

መንግሥት ድጎማውን ማንሳቱ ተገቢ መሆኑን እንደሚያምኑበት ገልጸው፣ ቁጥጥሩ ግን ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለዋል ። ድሃ ሀገር እንደ መሆናችን መጠን ከውስጥና ከውጭ የሚታዩ ሁኔታዎች በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጫና የሚያደርሱትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የኑሮ ውድነት እንዳይከሰት ከወዲሁ ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባው ጠቁመዋል ።

እንደ ሀገር የነበርንበት ህግ የማስከበር ዘመቻ በኢኮኖሚው ላይ የራሱ ተጽዕኖ አለው ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ የዓለም አካል እንደመሆናችን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ በተለይ በሩስያ እና በዩክሬን መካከል እየተደረገ ያለው ጦርነት በሁሉም አካባቢ ጫና እየፈጠረ ይገኛል ። በስጋት ምክንያት ወደቦች ሥራቸውን በሚያቋርጡበት ሁኔታ ውስጥ በምርት እጥረት አላስፈላጊ የዋጋ ግሽበት ተፈጥሯል ። ይህም ሁኔታ የመንግሥትን አቅም ክፉኛ ስለተፈታተነው በነዳጅ ላይ ሲያደርግ የነበረውን ድጎማ ለማንሳት ተገድዷል ። ውሳኔውም አግባብና ሁሉንም እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው ብለዋል ።

# 3ኛው ዙር አገር አቀፍ የኮቪድ-19 ክትባት መሰጠት ተጀመረ

## - ለዘመቻው 25ሚሊዮን ዶዝ ክትባት ተዘጋጅቷል

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ 3ኛው ዙር አገር አቀፍ የኮቪድ-19 ክትባት ዘመቻ ከሰኔ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ መሰጠት መጀመሩን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ ።

የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ዱጉማ በመግለጫቸው እንደተናገሩት፣ በኢትዮጵያ 3ኛው ዙር አገር አቀፍ የኮቪድ-19 ክትባት ዘመቻ ከሰኔ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ለ10 ተከታታይ ቀናት ይሰጣል ።

የ3ኛው ዙር የኮቪድ-19 ክትባት መርሐ-ግብርም በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንደሚሰጥ ጠቁመው፣ ለክትባት ዘመቻውም 25ሚሊዮን ዶዝ ክትባት መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

ከዚህ ቀደም ያልወሰዱ የማህበረሰብ ክፍሎች ክትባቱ በሚሰጥባቸው የጤና ተቋማትና በሚዘጋጁ ጊዜያዊ የክትባት ኬላዎች በመሄድ ክትባቱን እንዲወስዱ አሳስበው፤በሶስተኛው ዙር የኮቪድ ክትባት ዘመቻ እድሜያቸው ከ12 ዓመት በላይ ለሆኑ ሁሉም ሰዎችና ከዚህ ቀደም ክትባት ቢከተቡም ባይከተቡም ለሁሉም ክትባቱ እንደሚሰጥም ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ደረጀ ገለጻ፣ በዛሬው እለትም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የክትባት ዘመቻው የማስጀመር ንቅናቄው እንደሚካሄድ ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ደግሞ ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ ክትባቱን መስጠት እንደሚጀመር አስታውቀዋል።

በ2013 ዓ.ም መጋቢት ወር ላይ 24 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶዝ ክትባት የተሰጠ ሲሆን፤ በሁለተኛ ዙር ደግሞ 21 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሰዎች ክትባት መውሰዳቸውን ተናግረዋል።



የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በድጋሚ እያንሰራራ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በአሁኑ ወቅት 22 ሰዎች በጽኑ ህሙማን ክፍል ውስጥ እንደሚገኙም ጠቁመዋል።

ወረርሽኙ በድጋሚ እየተስፋፋ በመሆኑ ህብረተሰቡ ጥንቃቄውን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበው፣የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልም ነባሮቹን የመከላከያ ዘዴዎች በተገቢው መንገድ መተግበር እንደሚያሻ ዶክተር ደረጀ አሳስበዋል ።

ሁሉም ዜጋ ወረርሽኙ የሚያስከትለውን ጉዳት ከወዲሁ በመገንዘብ ለክትባት ዘመቻው መሳካት የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ዶክተር ደረጀ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከፍተኛ አመራሮች ከጋምቤላ ክልል ከፍተኛ አመራሮች ጋር ተወያዩ

አዲስ አበባ ፡- የኢትዮጵያ አገራዊ የምክክር ኮሚሽን ከፍተኛ አመራሮች ከጋምቤላ ክልል ከፍተኛ አመራሮች ጋር የትውውቅ እና የውይይት መድረክ አካሂደዋል።

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ፣ መሠረታዊ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚታየውን ስር የሰደዱ የሃሳብ ልዩነቶች እና አለመግባባቶች ለመፍታት ሰፋፊ አገራዊ የሕዝብ ምክክሮችን አካታች በሆነ መንገድ ማስኬድ እንዲቻል መደረጉ ተገቢ ነው ብለዋል።

በውጤቱም ለዜጎች የምትመች፣ ለጎረቤት አገራትም የሰላም እና ብልፅግና ተምሳሌት የሆነች ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመገንባት እንደሚያስችል ነው የተናገሩት።

እንደ አገር ካሳለፍናቸው ፈተናዎች ይበልጥ ወደ ፊት የሚቀሩን ይበልጣሉ እና በፈተና ላለመውደቅ ልዩነታችንን በማጥበብ አንድነታችንን ማጠናከር ይገባል ሲሉም አስረድተዋል።

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ተገኘወርቅ ጌቱ በበኩላቸው ፣ እስካሁን መግባባት ላይ ያልተደረሱባቸው እና የኢትዮጵያን ህልውና የሚፈታተኑ የተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች መኖራቸውን አንስተዋል ።

አገራዊ ምክክሩ እነዚህን ችግሮች በመፍታት ለመጪው ትውልድ ሰላማዊ አገር ለማስረከብ እንደሚያስችልም አብራርተዋል።

በክልሉ ያሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች ማልማት ከተቻለ የተፈለገውን ሰላም እና ዕድገት ማረጋገጥ እንደሚቻል በውይይት መድረኩ ተመላክቷል።

ከዚህ ባለፈም በመድረኩ ስለ ኮሚሽኑ አላማ ተልዕኮ እና ዕራይ ማብራሪያ መሰጠቱን ከክልሉ ፕሬስ ሴክሬታሪያት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል ።



አቶ ኡሞድ ኡጁሉ

ዜና

# በውሃ እጦት እየተቸገሩ መሆኑን የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ተናገሩ

**በኃይሉ አበራ**



አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች ያለውን የውሃ አገልግሎት በተመለከተ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው ነዋሪዎች በውሃ እጦት እየተቸገሩ መሆኑን ገልጸዋል።

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ግንፍሌ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት እና ልብስ በማጠብ ቤተሰቦቻቸውን እያስተዳደሩ የሚገኙት ወይዘሮ አየለች ሽፈራው እንደተናገሩት፣ በሳምንት ከሐሙስ እስከ ቅዳሜ ከሰዓት በአካባቢው ውሃ አይገኝም ።ይህ ሁኔታ ደግሞ ከዓመት በላይ እንዳስቆጠረና በስራቸውም ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደረባቸው ገልጸዋል ።

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 አካባቢ ያነጋገርነው ወጣት ኃይሌ አየነው በበኩሉ 15 ያህል ወጣቶች ተደራጅተው መኪና በማጠብ እንደሚተዳደሩ በመግለጽ የውሃው መቆራረጥ ሥራቸው እና የዕለት ገቢያቸው ላይ ችግር እየፈጠረባቸው መሆኑን ተናግሯል ።

በአራዳ ክፍለከተማ ወረዳ ስምንት ሺ ሰማንያ አካባቢ የሚኖሩት አርቲስት ሰለሞን ጥላሁን በበኩላቸው ቀደም ሲል ውሃ ማታ ማታ በየጊዜው ይጠፋ ነበር፤ አሁን ደግሞ በሳምንት ሁለትና ሶስት ቀን እየጠፋ እንደሚመጣ ገልጸዋል።

አቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ መሰረት አዳም በበኩላቸው በሰርጢ ማርያም አካባቢ በተከታታይ የውሃ አገልግሎት የሚቆራረጥ መሆኑን ጠቁመዋል።

የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ቀበሌ 21 በሳምንት አንድ ጊዜ፤ ጣፎ ወረዳ ሁለት፣ ሀያት ቁጥር አንድ እና ሁለት በሳምንት ሁለት ቀን ብቻ የሚመጣ መሆኑንም ነዋሪዎች ጠቁመዋል።

ጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 2 አሜሪካን ኤምባሲ ጀርባ፤ አዲሱ ገበያ ፅዮን ሆቴል አካባቢ፤ 41 እየሱስ ራስ ካሳ ሰፈር፤ ሰሚት ኮንዶሚኒየም፣ ለሚ ኩራ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ግንፍሌ እና ወረዳ 8 ሺ ሰማንያ አካባቢ እንዲሁም አቃቂ ቃሊቲ መኮድ ጀርባ ሰርጢ ማርያም ነዋሪዎች የውሃ ችግር ቅሬታ አቅርበዋል።

በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ የውሃ ሲስተም አብይ የሥራ ሂደት መሪ የሆኑት አቶ ጌትነት እጅጉ በበኩላቸው የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ለከተማዋ ነዋሪዎች ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ እየሰራ ቢሆንም የአቅርቦት እና የፍላጎት አለመጣጣም እንቅፋት እንደሆነበት ተናግረዋል ። በአንድ አንድ አካባቢዎችም ለማዳረስ ሲባል ውሃ በፈረቃ ለማሰራጨት መገደዳቸውን ገልጸዋል።

ውሃ በፈረቃ ለማዳረስ በሚደረገው የስርጭት ፕሮግራም ላይም እንደየአካባቢው ሁኔታ ልዩነት መኖሩን የገለጹ ሲሆን በሳምንት አንድ ቀን፣ በሳምንት ከሁለት እስከ ሦስት ቀን ወይም ከሦስት እስከ አራት ቀን የሚያገኙ አካባቢዎች መኖራቸውን ጠቅሰዋል።

አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ማታ የሚከፍተውና የሚዘጋው አሰራር የለውም ያሉ ሲሆን በስርጭት ሂደቱ ሲለቀቅ ብዙም ጊዜ ተዳፋታማ አካባቢ ያሉ መንደሮች ደርሶ ዳገታማ አካባቢዎች ላይ ዘግይቶ የመድረስ አጋጣሚዎች እንደሚኖር ጠቁመዋል ።

በግፊት ጣቢያዎች አካባቢ መብራት በሚጠፋበት ጊዜም የውሃ መቆራረጥ ሊያጋጥም ይችላል ያሉት እነዚህም በሚደርሱ ጥቆማዎች አማካይነት ምላሽ እያገኙ መሆኑንም ጠቁመዋል።


አጠቃላይ የከተማዋን የንጹህ መጠጥ ውሃ ፍላጎት ለማሟላት የተለያዩ ፕሮጀክቶች እየተተገበሩ ነው ያሉት አቶ ጌትነት ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው ጊዜ ወደ ሥራ እንደሚገቡ ገልጸዋል። የለገዳዲ ክፍል ሁለት የከርሰምድር ውሃ ፕሮጀክት በቅርቡ ወደ ሲስተም ሲገባ ከተማው አካባቢ ላይ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቶቹ የህዝብ አሰፋፈር ሁኔታን ማዕከል ባደረገ መልኩ እየተሰሩ መሆኑንና የውሃ አቅርቦቱ እስኪቃለል ህብረተሰቡ የአቅርቦት እና ፍላጎት አለመጣጣም ችግር መኖሩን ተረድቶ ውሃ በቁጠባ እንዲጠቀም ሲሉም አሳስበዋል።

በግለሰቦችም ሆነ የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ሲያካሂዱ የውሃ መስመሮች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ አመላክተዋል።

# ኢንዱስትሪው የአገሪቱን የግብርና ማሽነሪዎች ፍላጐት ለማሳካት በትኩረት እንደሚሰራ ተገለጸ

**አዲሱ ገረመው**



ፎቶ፡ ገባቡ ገብሬ

አዳማ፡- በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የአዳማ ግብርና ማሽነሪ ማምረቻ ኢንዱስትሪ የአገሪቱን የግብርና ማሽነሪዎች ፍላጐት ለማሳካት በትኩረት እንደሚሰራ ተገለጸ።

የአዳማ ግብርና ማሽነሪ ማምረቻ ኢንዱስትሪ የ2014 ዓ.ም የሥራ እንቅስቃሴ ትላንት በአዳማ ከተማ ተጐብኝቷል። እንቅስቃሴውን አስመልክተው ገለጻ ያደረጉት የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አምባሳደር ምስጋናው አርጋ ኢንዱስትሪው የአገሪቱን የግብርና ማሽነሪዎች ፍላጐት ለማሟላት በትኩረት እየሰራ እንዳለ ተናግረዋል።

ግሩፑ በብረታ በረት፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በፕላስቲክ፣ በአውቶሞቲቭ፣ በኮንስትራክሽንና በግብርና ማሽነሪ ዘርፍ ሥር የተደራጁ ዘጠኝ ያህል ኢንዱስትሪዎችን ያቀፈ ግዙፍ የልማት ድርጅት መሆኑን ጠቅሰዋል። ከነዚህ ውስጥ አንዱ የሆነው የአዳማ ግብርና ማሽነሪ ማምረቻ ኢንዱስትሪ የተለያዩ የግብርና ማሽነሪዎችን የማምረት ተልእኮን ይዞ የተደራጀ እንደሆነ አመላክተዋል።

ባለፉት ዓመታት ሰፊ የሪፎርም ሥራዎችን በማከናወን በአገሪቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ላይ የበኩሉን ሚና ለመወጣት በስፋት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ነው ያሉት።

በአሁኑ ወቅትም የአዳማ ግብርና ማሽነሪ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ከ516 ነጥብ 9 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የግብርና ማሽነሪዎችን በማምረት ወደ ኢኮኖሚው በማስገባት ላይ እንዳለ ጠቅሰዋል።

ወደ ኢኮኖሚው ውስጥ እየገቡ የሚገኙት ማሽነሪዎች የበጋ መስኖ ሥራን በማገዝና የግብርና ሜካናይዜሽንን በማስፋፋት ጉልህ ድርሻ እንዳላቸውም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል። ተጨማሪ ፍላጐቶችን ለማሳካት በኢንዱስትሪው ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገና የማምረቻ “ፋሲሊቲውን” የማዘመን ሥራ እየተተገበረ መሆኑን አስታውቀዋል። ይህም የበጋ ስንዴን በማምረት ረገድ ክልሎች እያደረጉት ያለውን እንቅስቃሴ የሚደግፍ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ እየሄደችበት ያለው የግብርና ፖሊሲ በምግብ ራስን በመቻልና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ፣ በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ ለማምረት የሚቻልበትን ስትራቴጂ በመቀየስ እየተሰራ እንዳለ ጠቅሰው፣ ይህንን ለመደገፍ የግብርና ማሽነሪዎችን ዝግጁ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል። በአሁኑ ወቅትም የአዳማ ግብርና ማሽነሪ ማምረቻ ኢንዱስትሪ በአሰራር ችግር ምክንያት ኢኮኖሚው ውስጥ ሳይቀላቀሉ የቆዩ የተለያዩ ማሽነሪዎችን ወደ ኢኮኖሚው እያስገባ እንደሚገኝ ጠቁመዋል። ይህም አገራዊ አቅምን ሊያሳድግ እንደሚችል ተናግረዋል።

ፋብሪካው የቅርቦት አቅሙን የሚያሳድግ ሲሆን፣ ደንበኞቹም በተቋሙ እምነት እንዲኖራቸው በማድረግ አገልግሎቱን አስፍቶ እንደሚሰራም ነው አምባሳደር ምስጋናው የጠቆሙት።

የኢንዱስትሪው ሥራ አስኪያጅ አቶ እያሱ ጥላሁን በበኩላቸው፣ የግብርና መሳሪያዎች ከቀረጥ ነጻ መሆናቸው ዘርፉን ማነቃቃት እንደቻለና ኢንዱስትሪውም ይህንን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በርካታ የእርሻ መሳሪያዎችን በማምረት ለገበያው በማቅረብ ላይ መሆኑን አስታውቀዋል። ይህ የአገሪቱን የግብርና ዘርፍ ለማዘመን ጉልህ ሚና እንዳለው አንስተዋል። ወደፊትም በቂ የማሽነሪ ምርት ለገበያው በማቅረብ የአርሶ አደሩን ፍላጐት ለማሳካት እንደሚሰራ ገልጸዋል።

የግሩፑ መረጃ እንደሚያመላክተው ኢንዱስትሪው፣ በ2014 ዓ.ም ከ277 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ ለበልግና ለመኸር እርሻ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ የፈረስ ጉልበት ያላቸው ትራክተሮች፣ የትራክተር ተቀጽላ መሳሪያዎች እንዲሁም የውሃ ፓምፖችን በመገጣጠም ለሶማሌ ክልል፣ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ለከፋ ዞን፣ ለመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር፣ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ፣ ለመቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደርና ለሶስት ለባለሀብቶች በማቅረብ ላይ ይገኛል።



# ለመኸር ግብርና ከ118 ሚሊዮን ሜትሪክ ኪዩብ በላይ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ተዘጋጀ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- ለ2015 በጀመት ዓመት የመኸር ወቅት ከ118 ሚሊዮን ሜትሪክ ኪዩብ በላይ የኮምፖስት ተፈጥሮ ማዳበሪያ መዘጋጀቱን ግብርና ሚኒስትር አስታወቀ ።

በግብርና ሚኒስቴር የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክተር አቶ ተፈራ ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ለመኸር ወቅት በአጠቃላይ ከ118 ሚሊዮን ሜትሪክ ኪዩብ በላይ የኮምፖስት፣ 130 ሺ ኩንታል በላይ ቨርሚኮምፖስት፣ ባዮስለሪ በኮምፖስት መልክ 842 ሺህ 436 ኩንታልና በፈሳሽ መልክ 25 ሚሊዮን 750 ሺህ 527 ሊትር ተዘጋጅቷል ።

የተከሰተው የማዳበሪያ ዋጋ መናር ሊያስከትል የሚችለውን የምርት መቀነስ የተለያዩ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎችን እንደ ኮምፖስት፣ ቨርሚኮምፖስት፣ ባዮስለሪ፣ የእቀባ እርሻ፣ አረንጓዴ ማዳበሪያና የከብት ፍግን በስፋት በመጠቀም ማካካስ ይቻላል ። ይህን ለማድረግ እየተሰራ ነው ።

አብዛኞቹ ክልሎች የተፈጥሮ ማዳበሪያን በማምረት አርሶ አደሩ እንዲጠቀም ከፍተኛ ቅስቀሳና ድጋፍ እያደረጉ እንደሆነ የተናገሩት አቶ ተፈራ፣ አርሶ አደሩም የማዳበሪያ እጥረት መኖሩን በመገንዘብ ችግሩን ለመቋቋም ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል ብለዋል ።

የተፈጥሮ ማዳበሪያን አጠቃቀም የማስፋት ተግባርን ለመደገፍ ግብርና ሚኒስትር ከክልል የሥራ ኃላፊዎች፣ ከምርምርና የልማት ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ግብረ-ኃይል እንዲቋቋም መደረጉን የገለጹት አቶ ተፈራ፣ የሥራ መርሐ-ግብር በማውጣት በስልጠናና በቅስቀሳ ለመደገፍ ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል ።

የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ መናር ለጊዜው ችግር ቢሆንም የተፈጥሮ ማዳበሪያ ላይ በመስራት ከማዳበሪያ ውጪና ጥገኝነት ለመላቀቅ በመረባረብ ላይ እንገኛለንም ብለዋል ።

እንደ አቶ ተፈራ አገላለጽ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ጤናማ የሆነና ተፈጥሯዊ ይዘቱን የጠበቀ ምርት በማምረት የኛንም የትውልዱንም ጤና በመጠበቅ በዓለም አቀፍ ገበያም ተወዳዳሪ የሆነ ምርት እያመረትን የውጭ ምንዛሪያችንን እንድናሳድግ ያደርጋል ።

የተፈጥሮ ማዳበሪያንም በስፋት በመጠቀምም ጤንነቱና ለምነቱ የተጠበቀ የእርሻ መሬት ለትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል ሲሉ አቶ ተፈራ አክለው ተናግረዋል ።

እንደ አቶ ተፈራ ገለጻ፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀም ከማዳበሪያ እጥረት ጋር በተያያዘ ብቻ መሆን የለበትም ። ሁሌም የአፈር ጤንነትና ለምነት ተጠብቆ እንዲቆይ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ወሳኝ ሚና ይጫወታል ።

# “ኢትዮጵያ ሽብርተኝነትን ለመቀልበስ ቀጠናዊና ዓለምአቀፋዊ አጋርነትን ወደላቀ ደረጃ እያሳደገች ትገኛለች”

\- አቶ ተመስገን ጥሩነህ
(የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል)

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የሽብርተኝነትን ስጋት ለመቀልበስ ቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊ ትብብርና አጋርነትን ወደላቀ ደረጃ እያሳደገች ትገኛለች ሲሉ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል አቶ ተመስገን ጥሩነህ ተናገሩ ።

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል አቶ ተመስገን ጥሩነህ ከትናንትናው ዕለት ጀምሮ “ሽብርተኝነትን በመከላከል የጋራ ቤታችን የሆነችውን ኢትዮጵያን እንጠብቃለን” በሚል መሪ ቃል እየተካሄደ በሚገኘው ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር ሽብርተኝነትን የመከላከል ተግባር የጋራን የትብብር ሥራ በመሆኑ በኢትዮጵያ ላይ ሊቃጡ የነበሩ የሽብር ጥቃቶችን በማክሸፍ ረገድ የጎረቤትና የሌሎች ሀገራት አቻ ተቋማት በመረጃ ልውውጥ የበኩላቸውን ሚና ያበረከቱ በመሆኑ ምሥጋና ይገባቸዋል ብለዋል ።

ሽብርተኝነትን በጋራና በትብብር የመከላከል ጠቀሜታን ቀድማ የተረዳችው ኢትዮጵያ የሽብርተኝነትን ስጋት ለመቀልበስ ቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊ ትብብርና አጋርነትን ወደላቀ ደረጃ እያሳደገች ትገኛለችም ብለዋል ።

በሀገር፣ በአህጉርና ዓለም አቀፍ ደረጃ የፀጥታና ደህንነት ስጋት በደቀነው ሽብርተኝነት ዙሪያ ለመምከር በተዘጋጀው ሀገራዊ ሲምፖዚየም አቶ ተመስገን እንዳሉት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለሽብርተኝነት አንድ ዓይነት ትርጉም ተሰጥቶታል ለማለት አያስደፍርም ብለዋል ። በጉዳዩ ላይ የጋራ ግንዛቤ የተያዘበት ቢሆንም ሽብርተኛን በመፈረጅ ደረጃ ግን ሰፊ ክፍተትና አለመግባባት ይታያል ሲሉም አክለዋል ።



አንዱ አገር ሽብርተኛ ብሎ የፈረጀውን ሌላው አገር የነፃነት ታጋይ በማለት ሲደግፍ ማየት የተለመደ ኩነት ሆኗል ያሉት ጀነራል ዳይሬክተሩ በተለይም በአፍሪካ ሀገራት መሪዎችን በየደረጃው ያሉ አስፈፃሚ አካላትን ሽብርተኛ መዝገብ ላይ ለማስፈር የሚቀናው የዓለም ሕግ ጡንቻ ያላቸው እና ያደገ ኢኮኖሚ ያላቸው አገራት መሪዎችና አስፈፃሚዎችን ሕጉ ሆን ብሎ ሲዘላቸው አለያም ዓለም እንዳላየ የሚያልፍበት ሂደት መኖሩን ጠቁመዋል ።

ሆኖም ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በትብብር ላይ የተመሰረተና የማይበገር የፀጥታ መዋቅር እየገነባች መሆኑን በመጠቆም ኢትዮጵያ ላይ ተደጋጋሚ የሽብር ጥቃቶች ቢሰነዘሩም ተመጣጣኝ እርምጃ በመውሰድና በማክሸፍ ጠንካራ የአሠራር ሥርዓት ያላት መሆኑን እና የታሰቡ የሽብር ጥቃቶችን ቀድሞ በማወቅና በማክሸፍ ጠንካራ የፀጥታና የደህንነት መዋቅር ካላቸው ሀገሮች ተርታ የተሰለፈች ሆና መቆየቷን አብራርተዋል ።

ኢትዮጵያ ሽብርተኝነትን በቁርጠኝነት ከሚዋጉ ግምባር ቀደም የዓለም ሀገራት የምትሰለፍ መሆኗን ያነሱት አቶ ተመስገን ሀገሪቱ በፈጠረችው ጠንካራ መዋቅር ሀገርና ሕዝብን ከጥፋት የታደጉ በርካታ ተልዕኮዎች በፀጥታ፤ መረጃና የደህንነት አካላት መራር ትግልና መስዋዕትነት ተፈፅመዋል ብለዋል ።

የለውጡ መንግሥት ከዴሞክራሲ ምህዳሩ መስፋት አኳያ ያሳየውን ታጋሽነት ጥቂት ሕግና ሥርዓት የማያከብሩ በአንድ በኩል የፖለቲካ በሌላ በኩል የነውጥና የለየለት ሽብርተኝነት ዘውግ እንደቦታው፣ ጊዜውና ጥቅሙ ይዘው የሚዓዙ አካላት በዜጎች ውድ ሕይወት፣ ንብረት እና በሀገር ደህንነት ቁማር ሲጫወቱ እያዩ ከማለፍ ይልቅ ተመጣጣኝ መልስ እየተሰጠ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል ።

‹‹በአመለካከትና በተግባር በጥቅም በጎጥ ሃይማኖትና ብሔር ተጋርተውና ተጣብተው ቀን ቀን ከእኛ ጋር፤ ከመጋረጃ ጀርባ ደግሞ ከአጥፊ ቡድን ጋር የሚመክሩ በውስጣችን ተሰግስገው የመሸጉ አካላትን ጉዳይ ከኛ መነፅርና ዕይታ ውጭ ባለመሆናቸው ሁኔታው በአፅንዖት ታይቶ አቅጣጫ ማስቀመጥ ያስፈልጋል ››ብለዋል ። ይህን ፈጥኖ ማረም ካልተቻለ ሀገሪቱን ከጥፋት ሕዝቡን ከመድማት ማዳን አይቻልምም ብለዋል ።

ሕዝባችን ሁሌም ሰላም፣ ፍትህ ልማት ፤ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፤ አብሮነትና የጋራ ብልፅግና የሚፈልግ ለዚህም መስዋዕትነት የሚከፍል ነው ያሉት አቶ ተመስገን፤ የእኛ ቁርጠኝነትና ንፁህ አገልጋይነት ከታከለበት ከጎናችን እንደሚሰልፍ በተግባር ያረጋገጠ ነው ሲሉ ተናግረዋል ።

---

## ‹‹ማህበራዊ እርሻን...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በአግባቡ በመጠቀም ምርታማነትን ከማሳደጉም ባሻገር ለማዳበሪያና ለፀረ-ተዋሲያ የሚለውን ወጪ፤ ጊዜንና ጉልበትን በመታደግ ረገድ የጎላ ሚና ይኖረዋል ።

ማህበራዊ እርሻ ስትራቴጂ በኢኮኖሚ በበለፀጉ ሃገራት በስፋት የተለመደና በተጨባጭም ውጤት ማምጣት መቻሉ የተረጋገጠ መሆኑን ዶክተር ጌታቸው አስረድተዋል ። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ አነስተኛ መሬት ላይ የሚያርሱ አርሶአደሮችን ምርታማነት በማሳደግ ሀገራዊ ኢኮኖሚውን መደገፍ የሚያስችል መሆኑን አብራርተዋል ። ‹‹በእኛም ሃገር አርሶአደሩ እያረሰ ያለው የበሬ ግምባር በምታክለው መሬት ላይ ነው ። ይህ አካሄድ በማህበር እርሻ ስርዓት መቀየር አለበት›› ብለዋል ።

አሁን ላይ በተወሰኑ አካባቢዎች የተጀመረውን የኩታ ገጠም እርሻን ወደ ማህበራዊ እርሻ ከፍ በማድረግና በሁሉም ክልሎች በማስፋት ሃገርአቀፍ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ማምጣት እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ‹‹የማህበራዊ እርሻ ልማት ሥራ በጥቂቱም ቢሆን ከጀመርን በሂደት ሃገር አቀፍ ማድረግ ይቻላል ። በዚህ መልኩ መቀጠል ከቻልንም እነዚህ የማህበር እርሻዎች ኢኮኖሚውን አቅፈው ይደግፉታል፤ አርሶ አደሩ ከነጋዴው ያልተናነሰ ተጠቃሚ ይሆናል›› በማለትም አብራርተዋል ።

በሌላ በኩል ግን አርሶአደሩ የመሬት ባለቤትነቱ ጉዳይ ለዓመታት ሲንከባለል የቆየ ጉዳይ መሆኑን ያስታወሱት ተመራማሪው አርሶአደሩ በገዛ መሬቱ ባይተዋር ሆኖ በስጋት ውስጥ እያመረተ እንዲኖር ያደረገው መሆኑን አስረድተዋል ። ይህም በምርታማነቱ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ መፍጠሩን አመልክተው፤ ‹‹መሬት የግል ሆኖ ለወለዱት ልጅ ማውረስ፤ መሸጥ መለወጥ እንዲሁም ለባንክ ማስያዝ እስካልተቻለ ድረስ ምርትና ምርታማነት በብዙ ይቀንሳል ። አርሶ አደሩ ዋስትና ስለማይኖረው ብዙ አቅዶ ለመስራት ይቸገራል›› ብለዋል ።

አክለውም ‹‹እንደ ኢትዮጵያ ያለ ህግ የትም የለም፤ የወያኔ መንግሥት የመሬት ባለቤትነትን ከህዝብ ሲቀማ ምርታማነቱ የዚያኑ ያህል እንደሚቀንስ አላሰበውም ነበር ። እነ ኬንያ፣ ታንዛኒያ ምርታማ ሲሆኑ ለምን ብሎ ቢጠይቅ ሚስጥሩ ይህ መሆኑ በተገነዘበው ነበር›› በማለት አብራርተዋል ።

ስለዚህ አርሶ አደሩ እንደልቡ እንዲያለማ ከተፈለገ መሬቱ የእርሱ መሆን እንዳለበትና ይህም ጉዳይ እልባት ሊሰጠው እንደሚገባ አስገንዝበዋል ። ከሁሉ በላይ መንግሥት መሬት ላራሹ ተብሎ የተከፈለውን የዚያን ሁሉ ወጣት ህይወት ከግምት ውስጥ በማስገባት የፖሊሲ ማሻሻያ ማድረግ እንደሚጠበቅበት ተናግረዋል ።

---

## መንግሥት ለትግራይ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ድርጅት ተወካዮች ጋር መወያየታቸውን የገለጹት ቃል አቀባዩ፤ ለአሜሪካ የኮንግረስ አባል፣ ለአውሮፓ ህብረትና የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልክተኛ በወቅታዊ የአገሪቱ ጉዳዮች ላይ ገለጻ ማድረጋቸውን አስታውሰዋል ።

ሁሉም ባለስልጣናት በመንግሥት በኩል እየተደረጉ ያሉ ድጋፎችን እንደሚደግፉ አመልክተው፤ የአፍሪካ ልዩ ሉዑክ ፕሬዚዳንት አባሳንጆ የሚያደርጓቸውን ጥረቶች በጥሩ ሁኔታ እንደተመለከቷቸውም ገልጸዋል ።

የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አሸባሪው ሕወሓት አሁንም ለሌላ ጦርነት ዝግጅት እያደረገ መሆኑን በመገንዘብ በግልጽ ሊያወግዘው እንደሚገባ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለባለስልጣናቱ ገልጸውላቸውል ። የሀገራቱ ልዑካንና ባለስልጣናት በበኩላቸው መንግሥት ለሰላም የሰጠውን ትኩረት አድንቀው፤ በተለይ ሀገራዊ ምክክር ለማከናወን የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ መናገራቸውን አምባሳደር ዲና ገልጸዋል ። እንዲሁም በሳውዲ አረቢያ በችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ወደ ኢትዮጵያ የመመለሱ ሥራ ተጠናክሮ ስለመቀጠሉም ጠቁመዋል ።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ አላማን አጣሞ ለአረቡ ዓለም በማቅረብ የውሃውን ጉዳይ የኢትዮጵያና የአረቡ ዓለም አድርጎ በማስቀመጥ በኢትዮጵያ በኩል ተገቢነት የሌለው አስተሳሰብ በአረቡ ዓለም ውስጥ አለ ብለዋል ። የህዳሴ ግድብ ትርክት በተሳሳተ መልኩ በማቅረቡ ከአረብ ሀገራት ጋር ባለው ግንኙነት ላይ የተወሰኑ ችግሮችን ቢፈጥርም ሁኔታዎችን ለማስተካከል ዲፕሎማሲያዊ ጥረት እንደሚደረግ አውስተዋል። ኢትዮጵያ ከአረቡ ዓለም ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖራት ትፈልጋለች ብለዋል ።

---

## ሕወሓት በፈጸማቸው...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በምን ጉዳዮች ላይ ኢትዮጵያን ሊያግዝ ይችላል በሚል ጉዳይ ላይ ውይይት እንደሚደረግም ጠቁመው፤ ከሰብዓዊ ድጋፍ ጋር በተያያዘ ሕብረቱ ሲያከናውን የቆያቸውን ተግባራት ማጠናከር እንዲቻል ውይይቱ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር አስታውቀዋል።

የአምባሳደሮቹ የኢትዮጵያ ቆይታ የኢትዮጵያ መንግሥት በተፈጸሙት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች ለሕብረቱ ይበልጥ ለማስረዳት እንደሚያግዝ ገልጸዋል።

የአውሮፓ ሕብረት ከሁለት ሳምንት በኋላም በሚያደርገው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያነሳቸውን ጉዳዮች ዋና አጀንዳ ሆነው እንዲታዩ ለማድረግ ከአምባሳደሮቹ ጋር የሚደረገው ውይይቱ ጠቀሜታ እንዳለው ሚኒስትር ዴኤታዋ ገልጸዋል።

ከሕብረቱ አምባሳደሮች ጋር የሚደረገው ምክክር የሕወሓት የሽብር ቡድን የሚነዛቸውን የውሸት ፕሮፓጋንዳዎች ለማጥራት ይረዳል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ስለጉዳዩ ተገቢውን መረጃ የሚያገኝበትን መንገድ ለማመቻቸት እንደሚያግዝ አስረድተዋል።

የአውሮፓ ሕብረት የፖለቲካና የደህንነት ኮሚቴ አባል አምባሳደሮቹ በዋናነት ከአፍሪካ ሕብረት የሰላምና ፀጥታ ምክር ቤት ጋር በአህጉራዊ ጉዳዮች ላይ እንደሚመክሩም ጠቁመዋል።

ከሰብዓዊ ድጋፍ ጋር በተያያዘ ያነሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ መንግሥት በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች የሚያደርገውን የሰብዓዊ ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ሚኒስትር ዴኤታዋ በሰጡት መግለጫ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉልና በሶማሌ ክልል ክልሎች የተፈጸሙ የሕግ ማስከበርና የሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የህብረተሰቡ አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደነበር ተናግረዋል።

ሕዝቡም ለሰላምና ደህንነት ሥራዎች ላደረገው ድጋፍ ምስጋና ይገባዋል ብለው፤ ሕዝቡ ሲያደርግ የቆየውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

የሕግ ማስከበር ሥራውም በተለያዩ የመንግሥት መዋቅሮች ውስጥ ያሉ ወንጀለኞችን የማጥራት ተግባርንም ያጠቃልላል፤ በመሆኑም የተጀመረው የሕግ ማስከበር ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

ከግብርና ጋር በተያያዘም በበልግ የሰብል ልማት ሥራ በአምስት ክልሎች ማለትም በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በደቡብ ምዕራብና በሲዳማ ክልልች ሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማረስ ታቅዶ ሁለት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መታረሱን አስረድተዋል። ከዚህ ውስጥም 85 በመቶው መሬት በዘር መሸፈኑን ጠቁመዋል።

በመደበኛው መስኖ ልማት በተለይም አትክልትና ፍራፍሬን በ655 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ለማልማት ታቅዶ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት መልማቱን ገልጸው፤ 150 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መሰብሰቡን አስታውቀዋል።

በስርጭትና አቅርቦት ረገድ መዳከም የታየበትን የማዳበሪያ ግብዓት በቀጣይነት በሰፊው አርሶአደሩ ጋር በማዳረስ የግብርና ምርት ዕድገት እንዲመዘገብ ጥረት ማድረግ እንደሚገባም ሚኒስትር ዴኤታዋ አሳስበዋል።

በተያያዘ በክረምቱ ወቅት የሚከናወነው የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ፤ ዜጎች ለአገራቸው ያላቸውን ፍቅር ለዓለም የሚያሳዩበትና ኢትዮጵያ በአንዳንድ መገናኛ ብዙሃን የምትቀርብበትን መጥፎ እይታ ለመቀየር የሚያስችል አጋጣሚ መሆኑን ገልጸዋል።

የቀዳሚ መጽሄት

# አገልግል



‹‹በኢትዮጵያ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ እልባት ሊያገኝ ይገባዋል››

- ዶክተር ጌታቸው ተድላ
የግብርና ተመራማሪና ደራሲ

ገጽ 6



‹‹ደንበኛህን ለማስደሰት ሠራተኛህን ተንከባከብ››

- አቶ ደረጀ እያሱ

ገጽ 13



ከጣራው ስር - ለመኖር አለመብላት፣ባለመብላት መኖር

ገጽ 16

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## አዲስ ዕጣ የሚወጣባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች

**ሶሎሞን በየነ**

በመዲናዋ የሚስተዋለውን የቤት አቅርቦትና ፍላጎት ልዩነት ለማጣጣም በ10 ዓመት ውስጥ ሁለት ሚሊዮን ቤት ለመገንባት እቅድ ተይዟል። መንግሥት ይህንን ዕቅድ ለማሳካት የቀጣይ የቤቶች ልማት ስትራቴጂ 80 በመቶ በግሉ ዘርፍ 20 በመቶ ደግሞ በመንግሥት ድጎማ እንዲከናወን ወስኗል። በዚህም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በአዋጅ 74/2014 በድጋሚ ሲቋቋም የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት 20 በመቶ በመንግሥት አስተባባሪነት የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ገንብቶ ማስተላለፍ ሆኗል።

ስለዚህ ተቋሙ በአዋጅ ከተሰጠው ሁለት አበይት ተግባራት (የጋራ መኖሪያ ቤቶችን መገንባትና ማስተላለፍ) አኳያ እያከናወነ ያለው ተግባራት ምን እንደሚመስል በኮርፖሬሽኑ የቤት ማስተላለፍ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ አውራሪስ ከበደ የሰጡንን ማብራሪያ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

እንደእርሳቸው ገለጻ፤ ላለፉት 18 ዓመታት በተለያዩ የቤት ልማት ፕሮግራሞች ማለትም በ40/60 መካከለኛ ገቢ ላላቸው፣ በ20/80 ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው እና አሁን ላይ ቢቋረጥም በ10/90 በጣም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛ የመንግሥት ድጎማ ተደርጎበት 317 ሺ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ተገንብተው ለቤት እድለኞች ተላልፈዋል።

ይሁን እንጂ የቤት ልማትና አስተዳደር ሥራዎች አፈጻጸሙ ከኅብረተሰቡ የቤት ልማት ፍላጎትና ተጠቃሚነት አንጻር የግንባታ ፕሮጀክቶች በከፍተኛ ሁኔታ መዘግየት እና አዳዲስ ፕሮጀክቶች አለመጀመር ይስተዋላል። እንዲሁም ከቤት ልማት ማስተላለፉና ማስተዳደሩ አንጻር ለክትትልና ለቁጥጥር ሥራ በማያመች መልኩ መደራጀቱ፣ የተግባርና የኃላፊነት መደራረብ መኖሩ፣ በወቅቱ ቤት አለማስረከብና የማዋዋል ጊዜ መርዘም የመሳሰሉት የኅብረተሰቡን የቤት ጥያቄ ለመመለስ የአሠራርና የአደረጃጀት ክፍተቶች ታይተውበታል።

በመሆኑም በአገሪቱ የመጣውን ፖለቲካዊ ለውጥ ተከትሎ እንደከተማ አስተዳደር ችግሩን ለመፍታት ጥናቶች በማካሄድ እና መሠረታዊ መነሻ ምክንያቶችን በመለየት በቤቶች ማልማት፣ ማስተላለፍና ማስተዳደር ላይ የነበረውን አደረጃጀትና አሠራር በማሻሻል፣ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽንን በአዲስ መልክ ተግባርና ኃላፊነቱን በመቅረጽ የመዋቅር አደረጃጀት ጥናት ተዘጋጅቶ እና ጸድቆ ወደ ሥራ ተገብቷል።

ኮርፖሬሽኑ በአዋጅ 74/2014 በድጋሚ ሲቋቋም የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት 20 በመቶ በመንግሥት አስተባባሪነት የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ገንብቶ ማስተላለፍ እንደሆነ አቶ አውራሪስ ጠቁመው፤ አዲሱ የለውጥ አመራርም ቁርጠኛ አቋም ይዞ የቤት ልማት ሥራው ለክትትልና ለቁጥጥር ሥራ በሚያመች መልኩ በማደራጀት የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን አጠናቆ ለህብረተሰቡ ለማስረከብ እርብርብ ሲደረግ ቆይቷል።

በዚህም ኮርፖሬሽኑ 139 ሺ በተለያየ የግንባታ ደረጃ ላይ የሚገኙ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በእጁ ላይ ያሉ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 80 ሺ በ40/60 እና በ20/80 የቤት ልማት ፕሮግራሞች የተገነቡ ቤቶች በ2011 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ለቤት እድለኞች እጣ ወጥቶባቸዋል። አመራሩም እነዚህን እጣ የወጣባቸውን የጋራ መኖሪያ ቤቶች ከሞላጎደል አጠናቆ ለቤት እድለኞች ለማስረከብ የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶ በሠራው ሥራ፤ ባለፉት ወራት ከ61 ሺ በላይ ዕጣ የወጣባቸውን ቤቶች አጠናቆ ለቤት ዕድለኞች አስረክቧል። በዚህም ከ50 ሺ በላይ አባወራዎች ቤታቸውን ተረክበው የራሳቸውን ማስተካከያ አድርገው ወደቤታቸው ገብተው እየኖሩ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

በጀት ዓመቱ ሳይገባደድ የኅብረተሰቡን ችግር የሚያቃልሉ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን አጠናቆ ለኅብረተሰቡ ለማስረከብ እርብርብ እየተደረገ እንደሚገኝ አቶ አውራሪስ ገልጸው፤ በዚህም ዕጣ የወጣባቸው ነገር ግን ግንባታቸው ተጠናቀው ለቤት እድለኞች ያልተላለፉ ቀሪ 19 ሺ 49 ቤቶችን መሠረታዊ ሥራቸውን አጠናቆ ለቤት ዕድለኞች ለማስረከብ እየተሠራ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በነባር በ1997 እና በዳግም ምዝገባ በ2005 ዓ.ም ተመዝግበው እየቆጠቡ ላሉ ቤት ፈላጊዎች 30 ሺ (በ40/60ና በ20/80 የቤት ልማት ፕሮግራሞች) አዲስ እጣ የሚወጣባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለማስተላለፍ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው። ስለዚህ በተያዘው እቅድ የቤቶቹ ግንባታ ተጠናቆ ለቦርድ ይቀርባል። ቦርዱ ዕጣ የሚወጣበትን ቀን፣ የቤት አይነት፣ የቤቶች ብዛትና የማስተላለፊያ ዋጋውን ሲወስን ዕጣው ለቤት እድለኞች የሚወጣ ይሆናል ብለዋል።

አቶ አውራሪስ፤ ከዚህ በፊት የቤት ምዝገባ ሥርዓቱ ዲጂታል ወይም የተጠናከረ ስላልነበር በሕገወጥ መንገድ ለግለሰብ ወይም ለተቋማት ቤቶች ተሰጥተው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በተለይ ከ2005 ዓ.ም ወዲህ የምዝገባ ሥርዓቱ ዲጂታል ስለሆነ የሚጭበረበርበት ዕድል አልነበረም። እጣውንም የሚያስተዳድረው የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ኢመደኤ) ነው። ስለዚህ አዲስ እጣ የሚወጣባቸው ቤቶች በነባር በ1997 እና በዳግም ምዝገባ በ2005 ዓ.ም ተመዝግበው እየቆጠቡ ላሉ ቤት ፈላጊዎች ብቻ ነው።

ነገር ግን ሁሌም ግንባታቸው ተጠናቀው ዕጣ ከሚወጣባቸው ቤቶች ውስጥ እስከ አምስት በመቶ መጠባበቂያ ቤት ለልማት ተነሺዎችና በተለያዩ ሰውሰራሽና ተፈጥሮ አደጋ ከቤታቸው ለሚፈናቀሉ ዜጎች እንዲያዝ መመሪያው ይፈቅዳል። በዚህ መሰረት ለአብነት በ2011 ዓ.ም እጣ ከወጣባቸው 80 ሺ ቤቶች ውስጥ በቦርድና በከተማ አስተዳደሩ ልዩ ውሳኔ ለአመራር የተላለፈው ሁለት ሺ ቤቶች ናቸው። ይህም የሚያሳየው ማንም በዘፈቀደ ቤቶቹን አንስቶ የሚሰጥበት እድሉ እንደሌለ ነው። ሌላው ብዙ ቁጥር ያለው የልማት ተነሽ ስለነበር 23 ሺ ቤቶች ለልማት ተነሺዎች ተላልፈዋል። ስለዚህ 98 በመቶ ቤቶቹ የተላለፉት ለትክክለኛው የቤት እድለኛና ለልማት ተነሺዎች ነው።

በተጨማሪም ቤቶቹ ለቤት እድለኞች ከተላለፉ በኋላ ከታለመላቸው ዓላማ ውጭ እንዳይውሉ ከአምስት ዓመት በፊት መሸጥ መለወጥ እንደማይቻል በመመሪያው በግልጽ ተቀምጧል። እንዲሁም የቤት እድለኛው ከ1997 ዓ.ም ወዲህ በራሱም ሆነ በትዳር አጋሩ ቤት ካለው፣ ብቸኛ ወራሽ ሆኖ ቤት በውርስ ካገኘ እንዲሁም በራሱም በትዳር አጋሩም ቤት ኖሮት በስጦታና በሽያጭ ያላስተላለፈ ከሆነ ተገቢው የማጣራት ሥራ ተሠርቶ ዕጣ ቢደርሰውም ቤቱ ሊተላለፍለት አይችልም። ስለዚህ ከሞላ ጎደል በዚህ አግባብ ቤቶቹ ከታለመለት ዓላማ ውጭ እንዳይተላለፉ ይገደባል። ነገር ግን ቤቱን በስጦታ ወይም በብድር በሚል በመንደር ውለታ ቤቱን በውስጥ ታዋቂነት ከታለመለት ዓላማ ውጭ የሚያውሉ አሉ። ስለዚህ በውስጥ ታዋቂነት ቤቶቹን ከታለመለት ዓላማ ውጭ የሚያውሉ አካላትን ህብረተሰቡ መታገል አለበት። ይህንን ሕገወጥ ተግባር በፍትህ ስርዓቱ ያሉ ተቋማት ለመከላከል በጋር መሥራት እንደሚጠበቅባቸውም አሳስበዋል።


ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹በኢትዮጵያ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ እልባት ሲያገኝ ይገባዋል››

- ዶክተር ጌታቸው ተድላ
የግብርና ተመራማሪና ደራሲ

ማህሌት አብዱል



ፎቶ፡- ገበበ ገብሬ

የተወለዱት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ቢሆንም ያደጉትና የተማሩት አሰላ ከተማ ነው:: እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ የቄስ ትምህርት ቤት ገብተው ፊደል ቆጥረዋል:: የመጀመሪያ ደረጃም ሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩት ራስዳርጌ ትምህርት ቤት ነው:: የዘመናዊ እርሻ ፋና ወጊ ከሆኑት አባታቸው ሥር ቁጭ ብለው በእውቀትና በጥበብ ያደጉት እኚሁ ሰው የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን እንደጨረሱ ጭላሎ እርሻ ልማት ውስጥ በሹፌርነትና አስተርጓሚነት ተቀጥረው ሰርተዋል:: እንዲሁም በዚሁ ተቋም ውስጥ የእቅድና ልማት ዘርፍ ምክትል ሃላፊ በመሆን አገልግለዋል:: በነበራቸው ቅልጥፍና እና ታታሪነትም የውጭ እድል አግኝተው ሲዊዲንና ሃንጋሪ በመሄድ በእርሻ፤ በእርሻ ኢኮኖሚክስና በእርሻ ልማትና ማህበረሰብ አቀፍ ግብርና ከመጀመሪያ ዲግሪ እስከ ዶክትሬት ዲግሪ ድረስ ተምረዋል::

በተማሩበት የሙያ ዘርፍ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውስጥ እስከ ከፍተኛ ዓመራርነት ድረስ ከአርባ ዓመታት በላይ ያገለገሉት እንግዳችን በዚህም ስራቸው 74ሃገራትን የመጎብኘት እድል ያገኙ ሲሆን በማደግ ላይ ያሉ ሃገራት ላይ የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ያበረከቱት አስተዋፅኦ በከፍተኛ ደረጃ ይጠቀሳል::

ወደሃገራቸው ከተመለሱም በኋላ በተለያዩ ሃገራት ያካበቱትን እውቀትና ተሞክሮ ለማካፈል እንዲሁም የግብርና ልማቱን ለማገዝ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ቢጠይቁም ጥያቄያቸው ተቀባይነት አላገኘም:: በመሆኑም ፊታቸውን ወደ እርዳታ ድርጅቶች በማዞር በገንዘብና በጉልበት መደገፍ ያዙ:: ከዚሁ ጎን ለጎንም የወላጅ አባታቸውን ታሪክ የሚያትተውን ‹‹ተድላ አበበ-የዘመናዊ እርሻ ፋና ወጊ›› የተሰኘውን መፅሃፍ ከመፃፍ ጀምሮ 16 የተለያዩ ታሪክና ይዘት ያላቸውን እውነተኛ ታኮችና ልቦለዶችን በመፃፍ ለህትመት አብቅተዋል:: ለአብነትም የአክሊሉ ሃብተወልድን ማስታወሻ፣ የአፄ ኀይለስላሴን ትክክለኛ ማንነት እንዲሁም የኢትዮጵያን ውብ ገፅታ የሚያሳዩ መፅሃፍትን በምስል በማስደገፍ ለአንባቢያን ያደረሷቸው መፅሃፍት ተጠቃሽ ናቸው:: አዲስ ዘመን ጋዜጣም እኚህን ታላቅ ሰው የዛሬው የዘመን እንግዳ አድርጎ እንደሚከተለው ይዞላችሁ ቀርቧል::

**አዲስ ዘመን፡- የውጭ የትምህርት እድል ያገኙበትን አጋጣሚ ያስታውሱንና ውይይታችን እንጀምር?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** ጭላሎ እርሻ በ18 ዓመቴ በሹፌርነትና በአስተርጓሚነት ተቀጥሬ በምሰራበት ወቅት በዋናነት ሞዴል ገበሬዎችን እንከታተል ነበር:: አንድ ዓመት ተኩል እንደሰራሁ ሪፖርት ፃፉ ተባለ:: ይሄ ነው እንግዲህ የህይወት አቅጣጫዬን ሙሉ ለሙሉ የቀየረው:: በመሰረቱ እኔ ከዚህ በፊት ሪፖርት እንዴት እንደሚፃፍ አላውቅም ነበር:: በመሆኑም ጸሃፊዋን ከዚህ ቀደም ተፅፎ ከሆነ ጠየኳትና ሰጠችኝ:: በነገራችን ላይ ከእኔ ጋር የሚሰሩት ሌሎቹ አራቱ ሰዎች አለማያ ኮሌጅ የጨረሱ ሲሆኑ እኔ ብቻ ነኝ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀኩት:: ግን የሚገርምሽ የቀደሙትን ሪፖርቶች እያየሁ የራሴን ሪፖርት ቆንጆ አድርጌ ሰርቼ ለዳሬክተሩ ሰጠሁት:: እሱም የሌሎቹን እናየዋለን ግን የጌታቸውን ዩኒቨርስቲ ስላልጨረሰ እኔ እሞላበታሁ አለ:: ሃሙስ እለት ይህንን ብሎኝ ሲያበቃ ሰኞ እለት አስጠራኝና ከመቀመጫው ተነስቶ አቅፎ ሳመኝ:: እንዲህ አይነት ሪፖርት ማንም የፃፈ የለም፤ እጅግ በጣም ጥሩና ትክክለኛውን የፕሮጀክቱን ገፅታ የሚገልፅ ሪፖርት ነው የፃፍከው አለኝ::

በወቅቱ ታዲያ ከአለማያ ኮሌጅ የመጡት ባለሙያዎች ይከፈላቸው የነበረው 550 ብር ሲሆን እኔ የማገኘው ደግሞ 275 ብር ነበር:: ዳይሬክተሩ በዚያ ሪፖርት በመደሰቱ የሚመለከታቸው አካላት ጋር ደውሎ ስለምሰራው ስራ ጥሩነትና ደመወዝ ከሌሎቹ እኩል እንዲከፈለኝ ቢጠይቅም በወቅቱ የነበሩት ሃላፊ ለዩኒቨርስቲ ምሩቃን እንጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለጨረሰ ሰው አይሰጥም አሉ:: ይሁንና የትምህርት እድል እንዲሰጠኝ ተስማሙ:: እናም ያቺ ሪፖርት ሲዊዲን ሃገር ነፃ የትምህርት እድል እንዳገኝ በር ከፈተችልኝ:: የመጀመሪያ ዲግሪዬን እንደጨረስኩኝ ተመልሼ ወደ ኢትዮጵያ ስመጣ ልክ እንደ ጭላሎ እርሻ (ካዱ) አይነት ፕሮጀክት ወላይታ ሶዶ ላይ ዋዱ የተባለ ፕሮጀክት እንዳቋቁም የእርሻ ማናጀር ሆኜ ተመደብኩኝ::

ስምንት ወር ከሰራሁ በኋላ አንድ ቀን እንደተለመደው የከረመ ጋዜጣ ሳገላብጥ ሃንጋሪ በእርሻ ትምህርት የማስተርስ ዲግሪ ለመማር የሚፈልግ ካለ ማመልከት እንደሚችል የሚገልፅ ማስታወቂያ አነበብኩኝ:: የሚገርምሽ ጋዜጣው ከወጣ አንድ ወር ያለፈው ቢሆንም እድሌን ልሞክር ብዬ ኢምባሲ ስደውል አንድም ሰው እንዳላመለከተ ነገሩኝ:: ያ የሆነበት ምክንያት በንጉሱ ዘመን አሜሪካና ሌሎች የምዕራብ ሃገራት እንጂ እንደሃንጋሪ ያሉ ኮምዩኒስት ሃገር ለመማር የሚያስበውም አልነበረም:: መልቀቂያ አስገብቼ እርሻ ሚኒስቴር በኩል አመለከትኩኝ:: ሀንጋሪ እንደሄድኩኝ ሁለት መኝታ ቤት ያለው አፓርትመንት ተሰጠኝ፤ ሶስት ወር ቋንቋዉን የምታሰለጥነኝ ሴት ተመደበችልኝ፤ የአራት ፕሮፌሰሮች ደመወዝ የሚያክል ገንዘብ ተከፈለኝ፤ በዚያ ላይ ትምህርቱ እንደሰጋሁት በሃንጋሪኛ ሳይሆን በእንግሊዘኛ መሆኑ ትልቅ እረፍት ሰጠኝ:: በአጠቃላይ ለመግለፅ በሚቸግር ሁኔታ ማንም የማያገኘው እድል ነው የተሰጠኝ::

ማስተርሴን እንደጨረስኩኝ ዶክትሬትን እዛው ለመስራት ሳመለክት ግን በኢትዮጵያ መንግስት በመለወጡ ምክንያት በአዲሱ መንግስት እውቅና ካልተሰጠኝ እንደማልቀጥል ተነገረኝ:: እኔም ፈጠን ብዬ በወቅቱ አመራር ለነበሩት ዶክተር ፀጋአምላክ አሳወኩዋቸውና ዶክትሬቴን እንድቀጥል ተፈቀደልኝ:: ትምህርቴን ልጨርስ ስል ቀይ ሽብርና ነጭ ሽብር የሚባል ነገር ተከሰተ:: በዚያ ወቅት ደግሞ ሚስት አግብቼ ልጆችም ወልጄ ስለነበር እንዴት እመለሳለሁ ብዬ ሳስብ ሌሎችም ሰዎች እንዳልመለስ መከሩኝ:: በዚህ መሰረት ቤተሰቤን ይዤ ወደ ሲዊዲን ተመለስኩና በተማርኩት ትምህርት ዘርፍ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተቀጠርኩ:: ሌሴቶ የሚባል ሃገር ተመደብኩ፤ በመቀጠልም ታንዛኒያ፤ በተከታታይ 17 ሃገራት በቋሚነት ተመድቤ የሰራሁ ሲሆን 74 የአለም ሃገራትን ደግሞ በስራ አጋጣሚ እየተዟዟርኩኝ ለማየት ችያለሁ:: ብዙ ጊዜዬን የአለም አቀፉ የምግብ ድርጅት ውስጥ ነው የሰራሁት፤ በመቀጠል ግን የአለም አቀፍ የፍልሰተኞች ድርጅት ውስጥ አገልግያለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- እስቲ አሁን ደግሞ ስለእርዳታ ሥራዎት በጥቂቱ ያብራሩልን?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውስጥ 45ዓመት አገልግዬ ወደ ተወለድኩባት ሃገር ከተመለስኩ በኋላ ሜቄዶኒያ በመሄድ ድርጅቱ በሁለት እግሩ እስከሚቆም ድረስ ከየድርጅቱና ባለሃብቱ ገንዘብ እየለመንኩ የበኩሌን ድጋፍ ሳደርግ ቆይቻለሁ:: በመቀጠልም እድገት የተባለ የህፃናት መርጃንም በተመሳሳይ እናትና አባት የሌላቸውን ህፃናትን ሙሉ ጊዜዬን በመስጠትና የቦርድ አባልም ሆኜ እየሰራሁ ነው ያለሁት:: ከዚህም ባሻገር የማሳትማቸውን መፅሃፍት ገቢ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ለእነዚህ ድርጅቶች ነው ያስረከብኩት:: በቅርቡም ሁለት መፅሓፌን አሳትሜ በቀጥታ ለሜቆዶንያ ሰጥቻለሁ:: የመጨረሻ መፅሓፍቶቼን ደግሞ አምባ ለሚባል የህፃናት ማሳደጊያ ሙሉ ለሙሉ ሰጥቻለሁ:: አሁንም ቤቴ ውስጥ የማሳድጋቸው ሁለት ልጆች አሉኝ:: ይህንን የማደርገው እኛ ረጅሙን መንገድ ጨርሰናል፣ ነገ አገር ተረካቢ የሆነውን ዜጋ ግን የመደገፍና የማብቃት ሃፊነት አለብን ብዬ ስለማምን ነው:: በቀጣይም አቅሜ የቻለውን ያህል የማደርግ ነው የሚሆነው::

**አዲስ ዘመን፡- የግብርና ባለሙያ ሆነው ሳለ በርካታ መፅሓፍትን በመፃፍ ለንባብ አብቅታዋል:: ከዚህ በመነሳት እንዳው የተደበቀ የስነ-ፅሁፍ ተሰጥኦ አሎት ማለት እንችላለን?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** እውነት ለመናገር በተለይ ከውጭ እንደተመለስኩኝ ግብርና ሚኒስቴርም ሆነ የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት በመሄድ በሙያዬ ሃገሬንና ህዝቤን ለመደገፍ ጥያቄ አቅርቤ ነበር:: ሆኖም የሚቀበለኝ አላገኘሁም:: እንደሚታወቀው የመጣሁት በወያኔ ጊዜ ነው፤ እዚህ ሃገር ዓለም-አቀፍ ተሞክሮ ያለውና ብዙ እውቀት ያካባተ ባለሙያ ላግዝ ሲል ለምን እንደሚከለከል አይገባኝም:: እንደነገርኩሽ በርካታ የዓለም ሃገራትን ጎብኝቻለሁ፤ ከ147 በላይ ነጮች በስሬ ስመራ የነበርኩ ሰው የገዛ ወገኖቼን ልደግፍ ባልኩኝ እንዴት ተቀባይ ማግኘት እንዳልቻልኩ ለእኔ ዛሬም ድረስ እንቆቅልሽ ነው:: በወቅቱ ከነበሩ የመንግስት ሰዎች ምላሽ በኋላ ምላሽ በማጣቴ አዲስ አበባ በሚገኘው የዓለም የምግብ ድርጅት ውስጥ የሥራ አስኪያጁ ዋና አማካሪ ሆኜ አንድ ዓመት ተኩል ሰርቻለሁ::

ከዚያ በኋላ ግን ቁጭ ከምል ብዬ መፃፍ ጀመርኩኝ፤ በቅድሚያም የአባቴን ታሪክ ፃፍኩና አሳተምኩኝ:: ቀጠልኩና ሁልጊዜ የሚሳዝኑንኛ ዓለም ያላወቃቸው ኢትዮጵያዊው ተመራማሪ አክሊሉ ሃብተወልድን ታሪክ ‹‹የአክሊሉ ማስታወሻ›› ብዬ ከፃፍኩኝ በኋላ የቀድሞ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት እንድሪያስ እሸቴን ጠይቄ አምስት ፕሮፌሰሮች ድጋፍ አግኝቶ ታተመ:: ይህ መፅሃፍ ከጠበኩት በላይ በብዙ ሺ ኮፒ ነው የተሸጠው:: ከዚያ በኋላ ደግሞ የራሴን የህይወት ታሪክ ፃፍኩኝ:: በመቀጠልም የሰባት ዲያስፖራዎች ታሪክ የያዘ ‹‹ከዝታ ጓዳ›› የተሰኘ መፅሃፍ አሳተምኩኝ:: በዚህም አላበቃሁም፤ ሃንጋሪ ሳለሁ አንድ አባስዩም ኀይቶም የሚባሉ ሰው ያጫወቱኝን ታሪክ በመፅሓፍ መልክ አሳትሜዋለሁ:: እቅድ 27 የተባለ ልብወለድ ፤ በኮሪያ የዘመቱ ጀግኖቻችንን የሚያወሳ አንድ መፅሃፍ ለአንባቢዎች አድርሻለው::

በተጨማሪም ሁልጊዜ የኢትዮጵያ ታሪክ በአለም ላይ ጦርነትና ረሃብ ብቻ ይታወቃል? ለምን ጥሩ ገፅታችንን አላሳይም? ብዬ የሃገራችንን ጥሩ ጥሩ ጎኖች የሚያሳዩ 500 የሚሆኑ ፎቶግራፎችን አሰባስቤ ከነማብራሪያው የሚያሳይ ትልቅ መፅሓፍ ከኢትዮጵያ አየር መንድ ጋር በመተባበር ዱባይ አምስት ሺ ኮፒ ታተመ:: በመቀጠልም ‹‹የማያባራው ጦስ›› የተሰኘ ልብ ወለድ ፅፌያለሁ:: በነገራችን ላይ ልቦለዶቹን ጨምሮ አብዛኛው መፅሓፎቼ እውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: ከእነዚህም መካከል ተነጣጥለው ሲዊዲንና ኢትዮጵያ ያደጉ ሳይተዋወቁ የኖሩ መንትያ ዶክተሮች ላይ ያነጣጠረው ‹‹መንታ ነፍሶች›› የተባለው መፅሓፌ ተጠቃሽ ነው:: እናም በዚህ መልክ አሁን ድረስ ቀጠለና ላይ 16ኛ መፅሓፌን ለማስመረቅ

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

እየተሯሯጥኩ ነው ያለሁት::

**አዲስ ዘመን፡- በጎንደሬው ነጋዴ ላይ ተመስርተው ስለፃፉት መፅሃፍ እስቲ በቅጡ ያብራሩልኝ?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** እኚህ ነጋዴ ከስማቸው ጀምሮ አስገራሚ ታሪክ ያላቸው ሰው ነበሩ:: የሚገርምሽ እኚህ ሰው ጎንደሬ ናቸው፤ የአባታቸውም ስም ጌታቸው ነበር፤ ከጎንደር ወደ አስመራ እየሄዱ እህል፤ ከአስመራ ደግሞ ጨው እያመጡ ይሸጡ ነበር:: እኚህ ነጋዴ እንደልባቸው እንዲገቡ እንዲወጡ ጌታቸው የሚለውን የአባታቸውን ስም በመተው ወደ ጎይቶም ቀይረውታል:: አንድ ቀን ማርዮ የሚባል ጣሊያናዊ ከአስመራ ምፅዋ ይወስዳቸዋል፤ «ሲጋራ ግዛ» ብሎ 10ሺ ሊሬ ይሰጣቸዋል:: በወቅቱ የ17 ዓመት ጎረምሳ የነበሩት እኚሁ ሰው በተባሉት መሰረት ሲጋራውን ገዝተው ሲመለሱ ውሃ ላይ የሚንሳፈፍ ቤት ያያሉ፤ ያለመሰረት ውሃ ላይ በሚናኘውን ቤት መሳይ ነገር ተደንቀው ጠጋ አሉት፤ ሰዎች ወደ ውስጥ ሲገቡ አይተውም ተከትለው ገቡ:: አንድ ነጭ መርከበኛ ያገኛቸውና «ለነጭ ብቻ የተፈቀደ ነው ምን ትሰራለህ» ብሎ ያፈጥባቸዋል፤ ማርዮ የተባለ ሰው ሲጋራ ግዛ ብሎ ልኳቸው እንደሆነና መውጫው እንደጠፋባቸው ይናገሩታል:: ያ ሁሉ ሲሆን ታዲያ አንድ ሰዓት ተኩል ያህል ጊዜ በመርከብ ተጉዘው እንደነበር አላወቁም ነበር:: በዚያው ተልከው ወጡ ሚላኖ አረፉ፤ በመቀጠልም ቡዳ ፔስት፤ አስትሪያ እየተዘዋሩ ሰርተዋል::

እኚህ ሰው በጉርምስና እድሜያቸው ከሃገራቸው ከወጡ በኋላ ጃንሆይም ሆነ መንግስቱ ሃይለማርያም አግኝቷቸዋል:: ጃንሆይ በሚሰሩበት የባሬስታነት ስራ ሃገራቸው ሆነው መስራት እንደሚችሉ ነግረዋቸው ሊወስዷቸው ቢጠይቋቸው አሻፈረኝ ብለዋል:: እንዳውም «አይነፋም» ብለው ሲመልሱላቸው ንጉሱ ክፉኛ ደንግጠው ነበር:: በነገራችን ላይ አሁን የአራዳ ቋንቋ ብዙ ሰው የሚመስለው ይህ ቃል በጎንደር የተለመደና አይሆንም እንደማለት ነው:: ያን ጊዜ በነጋዴው ስደተኛ ምላሽ ንጉሱ መደናገጣቸውን ያዩት የአትሌቲክስ አሰልጣኙ ወልደመስቀል ኮስትሬ ትርጉሙን ነግረው ነው ያረጓጓቸው:: መንግስቱን በተመሳሳይ ሁኔታ «አይነፋም» ብለውታል:: እናም የእኚህን ሰው የህይወት ታሪክ በመፃፍ ለህትመት አብቅቻለሁ::


**አዲስ ዘመን፡- አንድ ኮሌጅ ሄደው ካጋጠሞት ነገር ተነስተው ስለፃፉት መፅሐፍ ደግሞ እስቲ በጥቂቱ ያብራሩልኝ?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** አንድ ወቅት ላይ አንድ ኮሌጅ ሄጄ ስለጀግንነታችን ሳወራ የእኛ ወታደሮች እንኳን እዚህ ኮርያ ሄደው ጀግንነታቸውን ያሳዩ መሆናቸውን ገለፅኩኝ:: ይህንን ጊዜ አንድ ተማሪ ተነሳና «እኛ ከኮሪያ ጋር በድንበር ሆነ በክልልም ሳንዋሰን ለምንድነው እዛ ሄደን የተዋጋነው?» የሚል ጥያቄ በጩኸት አቀረበልኝ:: ይህም ትውልዱ ስለሃገሩ ታሪክ እንደማያውቅ እንድገነዘብ አደረገኝ:: ከዚህ በመነሳት የዘመቱ ጀግኖችን በማነጋገር ሰፊ ጥናት አካሄድኩኝ:: ፎቶግራፋቸውን አግኝቼም በማያያዝ በኮርያ የተፈፀመውን ጀግንነት የሚያሳይ በጣም ቆንጆ መፅሐፍ አዘጋጀሁኝ:: የሚገርመው ግን ኮርያ ድረስ ሄጄ ነገሩን ከስር መሰረቱ ለማጥናት ስሞክር ኮርያኖቹ የኢትዮጵያንና የጀግኖቿን ውለታ በሚዘክር ሁኔታ ቹንቻን በሚባል መንደር ማዕከል ከፍተው ለትውልድ እንዲተላለፍ ማድረጋቸውን አይቻለሁ:: በእውነቱ በዚህ በጣም ሊመሰገኑ ነው የሚገባቸው::

በተመሳሳይ አንድ ትምህርት ቤት ሄጄ ስለታሪክ እያስረዳሁ ስላ ስለጃኑሄ ተነሳና ተማሪዎቹ ያውቋቸው እንደሆነ ጠየኳቸው:: አንዱ ተነሳና «አዎ አውቀዋቸዋለሁ፤ ከሰው ይልቅ ለውሻ ምግብ የሚመግቡ ንጉስ ነበሩ» ሲል መልስ ሰጠኝ:: በሰማሁት ነገር በጣም ነው የተደናገጥኩት:: ሌሎቹም ከወሬ በስተቀር ስለንጉሱ ታሪክ እንደማያውቁ ነገሩኝ:: ስለሆነም በ11ሺ 800 የንጉሱ ፎቶዎች በእጄ ላይ ስለነበረኝ ከእነዚህ ውስጥም 306 ቆንጆ ፎቶግራፎችን መርጬ ለንጉሱ ቤተሰቦች አሳየኋቸው:: የገንዘብ ድጋፍ አድርገውልኝ ታሪካቸውን በምስል ያስደገፈ መፅሃፍ አዘጋጅቼ በቅርቡ ለማስመረቅ እየተሯሯጥኩኝ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ሁለት መፅሐፍቶችን አዘጋጅቻለሁ:: በድምሩ 16 መፅሐፍት ናቸው ያዘጋጀሁት::

**አዲስ ዘመን፡- ብዙ ጊዜ ስለወላጅ አባትዎት ሲናገሩ ይደመጣሉ፤ እስቲ እርሶ አሁን ሳሉበት ሁኔታ የአባትዎት አስተዋፅኦ ምን እንደነበር ያስታውሱኝ?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** እንደሚታወቀው አባቴ በኢትዮጵያ ዘመናዊ እርሻ ፋና ወጊ የሆኑ ሰው ናቸው:: በንጉሱ ዘመን በትራክተርና ኮምባይነር እንዴት ማረስ እንደሚቻል ያስተዋወቁ ሰው ከመሆናቸውም ባሻገር



ከሁለት ሺ ሰዎች በላይ በስራቸው ቀጥረው ያሰሩ ነበር:: የሚገርምሽ አባቴ ምንም እንኳን እስከ አራተኛ ክፍል ብቻ ቢማሩም አዳዲስ ነገሮችን የማሰብና የመቀበል ችሎታቸው ከፍተኛ ነበር:: ከዚህ በተጨማሪም ፈረንሳይኛና ጣሊያንኛ አቀላጥፈው የሚናገሩ ሰው ነበሩ:: ባይማሩም ግን የተማሩ ሰዎች በእሳቸው የግብርና እውቀት በጣም ነበር የሚገረሙት:: ከእርሻው ባሻገር ለአካባቢው ማህበረሰብ ትምህርት ቤት ፤ ክሊኒክ ከፍተዋል:: ንጉሱ እርሻቸውን በጎበኙበት ወቅት አባቴ ያስገነቡት ትምህርት ቤት በአባቴ ስም እንዲሰየም ቢነግሯቸውም እሳቸው ግን የራሳቸውን ስም ማጎላት ስላልፈለጉ በአካባቢው ስም ደነባ ትምህርት ቤት አሉት:: ያ ትምህርት ቤት አሁን ላይ በርካታ ዶክተሮችና ኢንጅነሮችን ማፍራት የቻለ የትምህርት ተቋም ሆኗል:: ብዙዎቹም እረኛ ሆነው ከመቅረት ታድገው ህይወታቸውን የለወጡላቸው መሆኑን ይመሰክሩላቸዋል::

ይሁንና ያ ሁሉ እርሻ፤ ያ በርካታ የአለም ባለሙያዎች የጎበኙት ሥፍራ፤ ለብዙዎች የሥራ እድል የፈጠረ ሃብት በአንድ አዋጅ ብቻ አመድ ሲሆን ማየት በጣም ነው የሚሳዝነው:: ደግሞም ከሁሉ በላይ የሚያሳዝነው ቦታውን ሆነ ቤቱን ይውሰዱ ግን ሲሆን እንዳለ ተረክቦ ማስቀጠል፤ ከተቻለም ማሻሻል ሲገባ ሙሉ ለሙሉ እንዲጠፉ መደረጉ በእጅጉ ልብ የሚሰብር ጉዳይ ነው:: በወቅቱ ከአባቴ ተቀምቶ ለእያንዳንዱ ሰው 10 ሄክታር ከተሰጠ በኋላ ሱማሌ ስትወረን ያ ሁሉ መሬት የተሰጠው ሰው ጦርሜዳ ሄዶ አንድም በህይወት የተመለሰ ሰው የለም:: አጥፍቶ መጥፋት ይሉሻል ይሄ ነው:: በአጠቃላይ ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ማውራት አልፈልግም::

**አዲስ ዘመን፡- አባቶት ባይማሩም ዘመናዊ ግብርና ባስጀመሩበት መንገድ ቢቀጥል ኖሮ የኢትዮጵያ ግብርና የት ይደርሳል ብለው ይገምታሉ?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** በጣም ቆንጆ ጥያቄ ነው! አንደኛ እንደዚያ ሆኖ ቢቀጥል ኖሮ ኢትዮጵያ ውስጥ የምግብ ዋስትና ጥያቄ አይነሳም ነበር:: ሌላው ቀርቶ ከአባቴም በተጨማሪ ከአለማያ ኮሌጅ የተማሩ ባለሙያዎች እርሻ ስራ ውስጥ ገብተው ነበር:: ቦሎቄና ጥጥ ሳይቀር በስፋት ይመረት ነበር:: ወደ ውጭ መላክም ተጀምሮ ነበር:: አንድ ጊዜ አባቴ ውስኪ ከፈቱና ምነው ብለን ብንጠይቃቸው 26 ብር ይሸጥ የነበረውን አንድ ኩንታል ስንዴ 28 ብር በመሸጣቸው ተደስተው እንደሆነ ነገሩን:: የሚገርምሽ ነጋዴዎቹ እዚያው ድረስ እየመጡ ነበር የሚረከቧቸው:: ሥራም ሆነ መሬት እንደልብ ነበር:: ደርግ የኢትዮጵያን መሬት ሲወርስ 20 በመቶ የሚሆነው መሬት ይታረስ ነበር:: 80 በመቶው ገና አልተነካም ነበር:: ቀሪውን ለሚፈልገው መስጠትና ማሳረስ ሲችል አልሚዎችን ማጥፋት ነበር የተያያዘው:: ያንን ሁሉ መሬት አባቴ በጀመሩት መንገድ ቢታረስ ኖሮ በኢትዮጵያ የምግብ እጥረት አይነሳም ነበር:: ሁለተኛ ህዝቡ በደንብ ጠግቦ ያድር ነበር::

ይህንን ስልሽ ፊውዳል ስርዓት አልነበረም እያልኩሽ አይደለም፤ ግን ደርግ እውቀት ስላልነበረው የሚያርሱና ለብዙዎች የሥራ እድል የፈጠሩ እንዳአባቴ ያሉ አምራቾችን አጠፋ:: በነገራችን ላይ በአባቴ መሬት ላይ የሚያርሱ ሰዎች ራሳቸው አርሶአደሮች ነበሩ፤ ስለሆነም ያ መሬት የተነጠቀው ከፊውዳሉ ሳይሆን ከአራሶአደሩ ጭምር እንደነበር ያሳይሻል:: በእኔ እምነት መውረስ የነበረበት አዲስ አበባ፣ አዳማና ቢሾፍቱ ቁጭ ብሎ እያሰረሰ በየዓመቱ የሚሰበስበውን ፊውዳል ነበር:: ከአራሹ ላይ እንዴት መሬት ይወሰዳል?:: በእርግጥ መጀመሪያ ላይ እኔ «መሬት ላራሹ» ሲባል የአባቴ መሬት አይነካም፤ እንዳውም ሌላ መሬት ይሰጣቸዋል የሚል እምነት ነበረኝ:: ምክንያቱም አባቴ አርሶአደር እንጂ ፊውዳል አልነበሩምና ነው:: በኋላ ላይ ግን መሬት ላራሹ ሳይሆን መሬት ለመንግስት ነው የሆነው:: እንዳልሽው ግን በተጀመረው ሁኔታ ከቀጠለ ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደምታድግ የውጭ ፃሃፍት ሳይቀሩ ፅፈውበት ነበር:: በወቅቱ ከኢንዱስትሪ እቃዎች በስተቀር እህልና ምግብ ከውጭ አናስገባም ነበር:: ከዚያ በኋላ ያ ሁሉ ልማት ጠፋና ልመና ውስጥ ተገባ:: አሁን ደግሞ ፈጣሪ ይመስገንና ገበሬው ነቅቷል እየሰራ ነው ያለው:: ግን ከሁሉ በላይ ሰላም ያስፈልጋል::

**አዲስ ዘመን፡- ግን እኮ ደርግ ከሰራቸው ጥሩ ነገሮች በዋናነት የሚጠቀሰው መሬት ለአራሹ መስጠቱ ነው፤ እርሶ ይህንን አይደግፉትም ማለት ነው? አሁን ካለው የመሬት አዋጅ ጋር እያነፃፀሩም ይንገሩኝ?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** በርግጥ «ደርግ መሬት ላራሹ» ብሎ ማወጁ የሚደገፍ ነው:: ሆኖም የዚህ ሃሳብ አመንጪ ደርግ ሳይሆን ለለውጥ የጮሁ ተማሪዎች ያመጡት ነው:: ግን መሬት ላራሹ ሲባል ለገበሬው ማለት ነው:: እንዳልሽው በዚህ አዋጅ በርካታ ገበሬዎች ተጠቃሚ ሆነውበታል:: እኔም ብሆን ለደርግ እውቅና የምሰጠውም ፊውዳላዊ ስርዓትን ማጥፋቱ ነው:: ፊውዳሎቹ ከተማ ቁጭ ብሎ በጭሰኛ ማሳረስ ብቻቸውን ነበር የሚጠቀሙት:: በወቅቱ ብዙዎቻችን አንድና ሁለት ሄክታር መሬት ያለው አርሶ አደር በማህበር ተደራጅቶ ትራክተርና ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያ አግኝቶ እንዲጠቀም፣ የእህል ማስቀመጫ መጋዘን በማህበር እንዲኖረው፣ ማህበር አቋቁመው ቀጥታ ለገበያ እንዲያቀርቡ እንወተውት ነበር:: ሃሳቡም ተቀባይነት አግኝቶ ስራዎች ተጀምረውም ነበር:: ይሄ ሥራ በጅምር ላይ እያለ ወያኔ መጣና ጠቅላላ መሬት የመንግስት ነው ተባለ:: አሁንም ድረስ አርሶአደሩ የሚያርሰው መሬት ባለቤት አልሆነም፤ መሬቱንም አስይዞ ከባንክ መበደር አይችልም::

ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ታሪክ ልንገርሽ:: አንድ የሃብታም ልጅ ሰራተኞች ያፀዱለታል፤ ልጁ ግን ተመልሶ ጭቃ ውስጥ ገብቶ ቦክቶ ይመጣል:: አንድ ቀን ግን አባትየው አየውና «ከዛሬ ጀምሮ ጭቃ ውስጥ ከገባ ራስህ አፅዳ» ብሎ አዘዘው:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያ ልጅ ሃላፊነቱ የራሱ መሆኑን ስለተረዳ ንፁህ ሆኖ ቤቱ ይመለስ ጀመር:: ያንን ያያ አባትም ለምን ጭቃ ውስጥ እንዳልገባ ቢጠይቀው «እንዴ አባባ እኔ ነኝ እኮ የማፀዳው» ብሎ መለሰለት:: የመሬት ባለቤት ጉዳይም እንዲሁ ነው:: መሬት የግል ሆኖ ለወለድሽው ልጅ ካልሰጠሽና «መሬቱ የእኔ ነው» እስካላልሽ ድረስ ምርትና ምርታማነት ብዙ ይቀንሳል:: ነገ ይወሰድ አይወሰድ አታውቂም፣ ዋስትና ስለማይኖርሽ ብዙ አቅደሽ አትሰሪም:: የእኔ የሚለው የትም አለም ውስጥ ትልቅ ነገር ነው:: ጫማዬንም ለማፅዳት የእኔ ነው ማለት አለብኝ:: ያን ጊዜ እኮራለሁ::

በነገራችን ላይ እንደ ኢትዮጵያ ያለ ህግ የትም የለም፤ የወያኔ መንግስት የመሬት ባለቤትነትን ከህዝብ ሲቀማ ምርታማነቱ የዚያኑ ያህል እንደሚቀንስ አላሰበውም ነበር:: እነ ኬንያ፣ ታንዛኒያ ምርታማ ሲሆኑ ለምን ብሎ ቢጠይቅ ሚስጥሩ ይህ መሆኑ በተገነዘበው ነበር:: ስለዚህ አሁንም ቢሆን ገበሬው እንደልቡ እንዲያለማ ከተፈለገ መሬቱ የእርሱ መሆን አለበት:: በኢትዮጵያ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ እልባት ሊያገኝ ይገባዋል:: መንግስት መሬት ላራሹ ተብሎ የተከፈለውን የዚያን ሁሉ ወጣት ህይወት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይጠበቅበታል:: በመሆኑም አሁን በመሬት ላይ ያለው ፖሊሲ መሻሻልና በዋናነትም መሬት የገበሬው መሆን አለበት:: ያንን ማድረግ ሲቻልም ነው ምርታማ የሆነ አርሶአደር መፍጠር የምንችለው::

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ ከኢትዮጵያዊነትና ከሃገር ፍቅር ጋር ተያይዞ የሚታዩ ክፍቶች ላይ ያሉትን አመለካከት ይንገሩንና ውይይታችንን እናብቃ?**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** እኔ በአሁኑ ጊዜ የተወለዱ ወጣቶች የታደሉ አይደሉም ባይ ነኝ:: ምክንያትም እንደኛ ከልጅነታቸው ጀምሮ ስለሃገር ፍቅርና ኢትዮጵያዊነት አስተምሮ ያሳደጋቸው ባለመኖሩ ነው:: ከሁሉም ህዝብ ጋር እንዴት ተቻችሎ መኖር እንዳለበት ተነግሮት አላደገም:: አልተዳለም የምለው፤ የኢትዮጵያዊነት ስሜቱን ከትውልዱ በመቀማቱ ምክንያት ነው:: አንድ ቀን የስምት ዓመት ልጄ ኳስ እየተጫወተ ሳለ ሮጦ መጣና «ብሔሬ ምንድን ነው» ብሎ ጠየቀኝ፤ ኢትዮጵያ ብዬ ነገርኩት:: ተመልሶ ሲሄድም ከኢትዮጵያዊነት ሌላ ብሔር የሚባል ነገር እንዳለ ነገሩትና መጣ:: አሁንም ደግሞ ከኢትዮጵያዊነት በስተቀር ብሔር የሚባል ነገር እንደሌለ አስረድቼ ዳግመኛ ቢመለስም አማራ ወይም ኦሮሞ የሚል ብሔር ስያሜ ይዞ ካልመጣ ኳሱ ቡድን ውስጥ አናስገባም ብለው መለሱት:: እንግዲህ የስምንት ዓመት ህፃናት አንደበት ይህ ሊነገር የቻለው ቤተሰቦቻው ቀርፀው ያሳደጓቸው በዚህ መልኩ መሆኑን ነው የሚሳየው::

ድሮ የትም ክልል ብንሄድ ጠያቂና ከልካይ አልነበረም፤ ምክንያቱም ሁሉም ቦታ ሀገራችን ነው ተብሎ ይታሰብ ስለነበረ ነው:: አሁን ግን ያ ሁሉ ተቀይሯል ፤ ማንም ሰው እንደፈለገ ከክልል ክልል መንቀሳቀስ አይችልም:: ሌላው ይቅርና ሲዊዲን በሰው ሃገር ስራ ተሰጥቶኝ በነፃነት ስኖር ቆይቼ እዚህ ስመጣ ግን ያ ሁሉ ተቀይሮ ነው የጠበቀኝ::

ስለዚህ በእኔ እምነት ጎሳ ላይ መሰረት ያደረገው ስርዓት መቀየር አለበት:: በመሰረቱ ክልላዊ አደረጃጀቱ በራሱ በአንድ ሃገር ውስጥ መፈጠር የሌለበት ነው:: አማራ እንዴት ከኦሮሞ ክልል ይኖረዋል?:: ክፍለ ሀገር እንጂ ክልል የሚባል ነገር በአንድ ሃገር ውስጥ ሊኖር አይገባም:: ይሄ ወያኔ እንድንለያይ ያደረገው ሴራ ነው:: አንድን ሃገር በክልል ከከፋልሽው በኋላ እኔና አንቺ መነጋገር አንችልም:: ከ17 ዓመት የትዳር ዘመን ቆይታ በኋላ ነው ባለቤቴን ከየትኛው ጎሳ እንደመጣች የጠየኳት:: ምክንያቱም ለእኔ ሰው መሆንዋ እንጂ ጎሳዋ ወይም የዘር ምንጪ ጉዳዬ ስላልሆነ ነው:: ልጆቼም ሆኑ ጋደኞቼ ፈረንጅ ነው ያገቡት፤ ከየት ጎሳ እንደመጡ ልጠይቃቸው ነው:: ኦሮሞ ጓደኞች አሉኝ፤ ጉራጌ ጓደኞች አሉኝ ለእኛ ጓደኝነታችን እንጂ የምናስቀድመው ጎሳችንን አይደለም:: እኔ ወደ ሀገሬ ከተመለስኩ በኋላ እስካሁን ሊዋጥልኝና ልቀበለው ያልቻልኩት ነገር ነው::

በመሆኑም አሁን ላይ ይህ ከፋፋይ አስተሳሰብ ያመጣብንን ጣጣ ስላየን እንደቀድሞ አንድ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊነት የሚል አስተሳሰብ መመለስ አለብን:: ከዚህ ሌላ ምርጫ የለንም:: ሁሉም ሰው በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ መኖር አለበት:: አሁን ያለው ትውልድ ከስህተቱ መመለስ አለበት:: መንግስት ይህ ሃገራዊ ስሜት እንዲመጣ ከልቡ መታገል አለበት:: ግብረ-ገብ ትምህርት በየትምህርት ቤቱ በቋሚነት ሊሰጥ ይገባል:: በተጨማሪ መንግስት በተለወጠ ቁጥር ባንዲራ የሚለወጥበት ነገር ላለመግባባታችን አንዱ ምክንያት ነው ብዬ አምናለሁ:: ሌላው አገር እንዲህ አይነት ነገር የለም:: ለምሳሌ አሜሪካ እንኳን 300 ሌሎቹም ከ400 እስከ 900 ዓመታት ባንዲራቸውን አስቀጥለው ነው የዘለቁት:: ሌሎች ነገሮች ይለዋወጣሉ፣ ፓርቲ ይለዋወጣል፣ አገር ይለዋወጣል፣ መሪዎች ይለዋወጣሉ፣ ይሞታሉ፣ ባንዲራ ግን ይቀጥላል:: እኛ ጋር ግን ሰው በተለዋወጠ ቁጥር ባንዲራ ስንቀይር ነው የኖርነው:: ይህ ክፉ ልምድ መሻሻል አለበት ብዬ ነው የማምነው:: ከሁሉ በላይ አባቶቻችን በጦር ሜዳ ታግለው ነጮችን ያንበረከኩበት አረንጓዴ፤ ቢጫ ና ቀይ ባንዲራችንን ቢቀጥል ብዙዎቻችንን የሚያስማማ ይመስለኛል::

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ::**

**ዶክተር ጌታቸው፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

# ማህደረ ጤና

## "ኮሮና የለም" ከሚል አስተሳሰብ እንውጣ

**እፀገነት አክሊሉ**

የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በዓለም ሕዝብ ላይ ጥርሱን እንደነከሰ ነው። የሚሊዮኖች ሞትና የብዙ ሚሊዮኖች ስቃይ የሰማው ጆሯችን አሁንም ይህንን አይነቱን ዜና በጥቂቱም ቢሆን ከመስማት አላረፈም። የሰማነውን እያየን በስጋት መኖር ከጀመርን ዓመታት ተተካክተዋል። የሕክምናው ማኅበረሰብ ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ ጋር የገጠመው ጦርነትም ገና መቋጫውን አላገኘም። አሸናፊነቱም ገና አልታወቀም። ሆኖም አሁንም ውጊያው እንደቀጠለ ነው። ምክንያቱ ይህ አስከፊ ቫይረስ ከዓለም ላይ አለመወገዱ ነው።

ዛሬ የብዙዎችን በሕመሙ መያዝ መሰቃየት ለመተንፈስ መቸገር ባስ ሲልም ለሞት መዳረግን በዓይናችን እያየን ነው። የተማመንባቸው በርካታ የስነ ልቦና አቅሞቻችን ብሎም ማኅበራዊ መስተጋብሮቻችንና ባህላዊ እሴቶቻችን ሁሉ ከዚህ በሽታ ሊታደጉን አቅም የተሳናቸው ነው የሚመስሉት፤

ሕዝብ ዘንጋ ማለቱን እየጠበቀም እንደ ረመጥ የተዳፈነው የበሽታው ወላፈን እየተስፋፋ ዛሬም ለሌላ እልቂት ሊያዘጋጀን ዳር ዳር እያለን ያለ ይመስላል ። ከጥቂት ወራት በፊት ጋብ ያለ የመሰለው የአገራችን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ዛሬም እንደትላንቱ የሆስፒታል አልጋዎቻችንን ሊያጨናንቅ ብሎም ሕዝብን ሊፈጅ እንደገና የማንሰራራቱ ዜናም እየተሰማ ይገኛል። በመሆኑም አሁን ከጅምሩ ጥንቃቄ ያላደረግንበት ኮሮና ኋላ እንደ ዛሬ ዓመቱና ሁለት ዓመቱ የሆስፒታሎቻችን አልጋዎች ሞልተው የት ልንታከም ነው የሚለው ጭንቀት ውስጥ ስንገባ አይደለም መንቃት ያለብን ዛሬውኑ እንጂ።

ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በነበረው መረጃ ከቱኒዚያ ቀጥላ በአፍሪካ በርካታ ሰዎች በቫይረሱ የተያዙባት አገር መሆኗ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፤ በእስከ አሁኑ ምርመራ ማለትም እስከ ሰኔ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ 4 ሚሊዮን 968 ሺ 76 ሰዎች የላብራቶሪ ምርመራ ያደረጉ ሲሆን ከእነዚህም መካከል 12 ሺ 996 ሰዎች የኮሮና ቫይረስ ተገኝቶባቸዋል ፤ እስከ አሁን ባለው መረጃም በበሽታው ምክንያት ሕይወታቸውን ያጡ ሰዎች ቁጥር 7 ሺ 516 ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን ከበሽታው ያገገሙት ደግሞ 456 ሺ 492 ሰዎች መሆናቸውን ከጤና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ከዚህ የምንረዳው ከዚህ ቀደም ባሉት ወራቶች ምርመራው ቢደረግም በበሽታው ተይዘው የሚገኙ ሰዎች መጠን እጅግ አናሳ የነበረ መሆኑን ነው። ዛሬ ላይ ግን ከፍ የማለት ሁኔታ ታይቶበታል ። በዚሁ በሰኔ 1 ቀን 2014 ዓም ብቻ 4ሺ 678 ሰዎች የኮሮና ቫይረስ ምርመራ ተደርጎላቸው 634 ቱ ሰዎች በሽታው ተገኝቶባቸዋል። ከእነዚህ መካከልም 16ቱ በጽኑ ታመዋል። ጠፍቶ የነበረው የሟች መጠንም አንድ ሰው ሕይወቱ በማለፉ ዳግም ሊመዘገብ ችሏል።

ስርጭቱ በሕዝቡ ውስጥ ይፋዊ በሆነ መልኩ የተሰራጨ ስለሆነ ከክልል ክልል ይለያይ ይሆናል እንጂ ሁሉም ቦታ ላይ ስለመኖሩ ግን አያጠያይቅም። የኮቪድ ሕክምና ማዕከሎቻችን በታካሚዎች ተሞልተው፤ ድንገተኛ ክፍሎቻችን በሕክምና ፈላጊዎች ተጨናንቀው ፤የኦክስጂንና የመተንፈሻ አጋዥ ሜካኒካል ቬንቲሌተር እጥረት ብዙዎችን ለስቃይና ሞት ሲዳርግ ፤ የሕክምና ማዕከላት መጀመሪያ ኦክስጂን ለሚያስፈልጋቸው እየተባሉ የሕክምና ልዩነት እንዲፈጠር ሲያስገድድ የነበረበት ሁኔታ ዛሬ ቢያልፍም አስተምሮ ያለፈው ነገር ግን አለ ። እናም ወደዚህ ችግር ላለመግባት ሁላችንም ቆራጥ መሆን አለብን።

ይህ ቫይረስ መዘናጋታችንን አይቶ ዳግም ለሶስተኛ ጊዜ መጥቶ እንዳይጎዳን ልንጠነቀቅም ይገባል። ለመጠንቀቅ ትልቁ መንገድ ደግሞ ከማን እንደያዘን እንኳን አናውቅምና የግል ጥንቃቄያችንን ከማድረግ በቀር አስተማማኝ አማራጭ የለንም።

በሽታው በአንድ በኩል በሕዝቡ ሕይወትና የሕክምና ሥርዓቱ ላይ ያሳደረው ጫና ከፍተኛ መሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ አሁንም ልናመጣ የሚገባን የግንዛቤና የአመለካከት ለውጥ መኖሩ ግልጽ ነው። ሞት በየበሩ ቆሞ እያንኳኳ "ኮሮና የለም" ከሚል አስተሳሰብ ልንወጣ ይገባል። ለመኖሩም ለሚያስከትለው ሞትም እኛው እራሳችን ያለፉትን ሁለት ዓመታት በማየታችን ብቻ በቂ ምስክሮች ከመሆናችንም በላይ ዛሬም ጤና ሚኒስቴር በሚያደርሰን የየቀን የምርመራ ውጤትና ሪፖርት በቅርበት እያያንና እየሰማን ነው።

በዓለም ላይ ይህ ሁሉ ሰው ሞቶ ከፍተኛ የሆነ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ተከስቶ እያየን ያየነውን የሰማነውን አምነን እንዳንቀበል ዛሬም በተሳሳቱ ግንዛቤዎች እንዲሁም ኮሮና የለም በሚል አጉል ነገር ዋጋ መክፈል የለብንም። በእርግጥ በሀገራችን ብዙዎችን ሲያስተናግድ የነበረው ትልቁ የኮቪድ ሕክምና ማዕከል ኤካ ኮተቤ ሆስፒታል ከወራት በፊት ማዕከሉ ውስጥ ምንም አይነት የኮሮና ቫይረስ ታማሚ አለመኖሩን ይፋ አድርጎ ነበር። በዚህ ዜና ደስ ብንሰኝም ብዙ ርቀት ግን አልሄድንም ፤ ወዲያውኑ ወደ ሕክምና ማዕከሉ መግባት ያለባቸው የኮቪድ ታማሚዎች ተገኙ። በመሆኑም እኛን የሚያዋጣን በሽታው አለ ብሎ ጥንቃቄ ማድረጉ ብቻ ነው።

> **እስከ ሰኔ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ 4 ሚሊዮን 968 ሺ 76 ሰዎች የላብራቶሪ ምርመራ ያደረጉ ሲሆን ከእነዚህም መካከል 12 ሺ 996 ሰዎች የኮሮና ቫይረስ ተገኝቶባቸዋል ፤ እስከ አሁን ባለው መረጃም በበሽታው ምክንያት ሕይወታቸውን ያጡ ሰዎች ቁጥር 7 ሺ 516 ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን ከበሽታው ያገገሙት ደግሞ 456 ሺ 492 ሰዎች መሆናቸውን ከጤና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል**

ለጤና የምንከፍለው ዋጋ አብዛኛውን ጊዜ ለመኖር ካለን አቋም ወይም ፍላጎት ይመነጫል፤ ነገር ግን ረጅም እድሜን በጤና ለመኖር ስናስብ ልንከተላቸው የሚገቡ ወይም አስፈላጊ የሆኑ የጤና አጠባበቅ ዘዴዎች አሉ እነሱን አጓድሎ ግን ረጅም ዓመት መኖርን መመኘት ትርፉ ድካም ብቻ ነው።

ወጣት ዮሐንስ እሸቱ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ነው። በሞባይል ቤት ጥገና ሥራ የሚተዳደር ሲሆን እንደ ኮሮና በሽታ የሚንቀው ነገር እንዳልነበር ይናገራል። ገና ያን ጊዜ ቫይረሱ ሀገራችን ገባ ሲባል ሰዎች ሲጨነቁ ንግድ ቤቶች ሲዘጉ መጠጥ ቤቶች የሰዓት ገደብ ሲጣልባቸው እኔ ምንም አይመስለኝም ነበር ሥራዬንም እሠራ ነበር። የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ እንኳን የማደርገው ትራንስፖርት ላይ ስገባ ግዴታ ስለሆነ እንዲሁም በመንገድ ላይ ፖሊሶች እንዳያስቆሙኝ ስል ነበር በማለት በወቅቱ ለኮሮና ቫይረስ ሰጥቶት የነበረውን ግምት ያወሳል።

በሽታው ወደ ሀገራችን ከገባ ከዓመት በኋላ ግን ወጣት ዮሐንስ እሱነቱን እስከሚስት የሚያደርስ ሕመም ታመመ ። ባደረገው ምርመራም የኮሮና ቫይረስ ተገኘበት። በወቅቱ ይላል ወጣቱ በሕይወቴ አይቼው ይገጥመኛልም ብዬ የማላስበው አይነት ሕመም ነበር ያመመኝ። መላ ሰውነቴ የእኔ አልነበረም ትኩሳቱ፣ ቅዝቃዜ፣ ላቡ፣ እራስ ምታቱ፣ ቁርጥማቱ ብቻ ብዙ ነገር ከባድ ነበር በማለት ያስታውሳል።

ወጣት ዮሐንስ ለኮሮና የሰጠሁት ዝቅ ያለ ግምት ሞት ደጃፍ አድርሶ ነው የመለሰኝም ይላል። ዛሬ ላይ ቆሞ ሲያስበውም በሥራው እስከማፈር የደረሰ ጸጸት ይሰማዋል። ምክንያቱም የጤና ባለሙያዎች የሚሰጡትን ምክር ሰምቼ ቢሆን ኖሮ ለዛ አይነት ሕመም አልጋለጥም ነበርም ሲል መፀፀቱን ይናገራል።

እስከ አሁን ድረስ ቀዝቀዝ ያለ ነገር ስጠጣ ብሎም አየሩ የሚበርድ ሲሆን ድምጼ ይዘጋል፡፡ ብዙም ጤንነት አይሰማኝም የሚለው ዮሐንስ ሰዎች እንደ እኔ ግዴለሽ ሆነው ራሳቸውን አደጋ ላይ መጣል የለባቸውም የሚል ምክሩንም ያስተላልፋል።

"በሚያልፍ ነገር የማንም ሕይወት መጥፋት የለበትም" የሚለው ዮሐንስ እኔ በወቅቱ ሞቼ ቢሆን ኖሮ ተረስቼ ነበርም ይላል። አሁንም ኮሮና ጠፍቷል እያልን እየተዘናጋን ነው። ነገር ግን በሽታው ሙሉ በሙሉ ጥሎን አልሄደም እንደውም አድፍጦ የእኛን መዘናጋት እየጠበቀ ያለ ይመስለኛል ።በመሆኑም ለሶስተኛ ጊዜ መጥቶ ጉዳት ሳያደርስብን ሁላችንም ልንጠነቀቅ ይገባልም ብሏል።

አዎ ካልደረሰብን አናምንም ካልሆነ በቀር በየቤታችን ቢያንስ አንድ ወይም ሁለት ሰው በዚህ በሽታ ያልተሰቃየ አለ ብሎ መገመት ከባድ ነው። በመሆኑም ሁላችንም ለሀገራችንም ለራሳችንም ለቤተሰባችንም በማሰብ በሽታው ዳግም አገርሽቶ ችግር ላይ ሳይጥለን በፊት ልንጠነቀቅ ይገባል።

በሀገራችን አሁንም ስርጭቱ እየጨመረ ይገኛል።"ኮቪድ የለም" ማለቱም እንደማያዋጣ የሕክምና ባለሙያዎች እየተናገሩ ነው። በቅርቡ እንኳን የኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል በማኅበራዊ ትስስር ገጹ እንዳሰፈረው የኮቪድ 19 በሽታ ጋብ ያለ መስሎ ዳግም ለመነሳሳት ዳር ዳር እያለ በመሆኑ ሁሉም የተለመደ ጥንቃቄውን ያድርግ ሲል መክሯል።

ራስን ከዚህ ወረርሽኝ ለመጠበቅ የበሽታው ምልክቶች ካለባቸው ሰዎች መራቅ፣ በሚያስነጥሱና በሚያስሉበት ወቅት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ፣ እጅን አዘውትሮ መታጠብ፣ ከሌሎች ሰዎች አካላዊ ርቀትን መጠበቅና እና እንደ ከዚህ ቀደሙም ባይሆን ማኅበራዊ ግንኙነቶቻችን በመጠኑ ማድረግ ያስፈልጋል። እነዚህንና ሌሎች ጥንቃቄዎች ማድረግ እራስን ለመጠበቅ ብቻ ሳይሆን የቫይረሱን ስርጭትም ለመግታት ይረዳል። ካልሆነ ግን የቫይረሱ ስርጭት ዳግም ለሶስተኛ ጊዜ ተከስቶብን በአገራችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ኑሯችን ላይ ጫና ማሳደሩ አይቀሬ ነው።በመሆኑም ጠንካራ የጤና ሥርዓት የዘረጉትን ያደጉ ሀገሮች ሳይቀር የሚያሽመደምደው ኮቪድ ዳግም እንዳይጎዳን በማድረግ በኩል ሁላችንም ኃላፊነት አለብን።

በአጠቃላይ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ልክ ቫይረሱ መኖሩ የተሰማ ጊዜ ያሳየውን አይነት የጥንቃቄ ሁኔታ አጠናክሮ መቀጠል ካልተቻለ ቀላል የማይባል የሰው ሕይወት ሊያሳጣ እንደሚችል ዶክተሮች ስጋታቸውን እየተናገሩ ነው።

# ነፃ ሃሳብ



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## ሠልስቱ የአመራር ተግዳሮቶች

### ትዝታና እውነታ፤

በኅዳር ወር 1989 ዓ.ም የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪ የተባሉ የ23 ሀገራት መሪዎች የተካተቱበትን አንድ ሴሚናር በአሜሪካዋ የሐዋይ ክፍለ ግዛት በማዊ ደሴት ለመካፈል ዕድል አጋጥሞት ነበር:: ተሳታፊዎቹ በሙሉ ከዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በስተቀር በየሀገራቸው በከፍተኛ የአመራር ሥልጣን ላይ የነበሩ የአንቱታ ባለጸጎች ነበሩ:: የሴሚናሩ አተገባበር ከፕሮፌሰሮቻችን ወደ ተካፋዮች የሚፈስ የአንድ አቅጣጫ ሌክቸር (One way communication approach) ሳይሆን እያንዳንዱ የሴሚናሩ ተካፋይ የሀገሩን መልከ ብዙ የአመራር ተሞክሮ በሚመደብለት ሰዓት መጥኖ ማቅረብ ይጠበቅበት ነበር::

በዚሁ መሠረትም ይህ ጸሐፊ ተራው ሲደርስ ይመጥናል ያለውን ዝግጅቱን አቅርቦ ካጠናቀቀ በኋላ ለተሳታፊዎቹ የአስተያየትና የጥያቄ እድል ለመስጠት ገና መድረኩን ለውይይት ክፍት ከማድረጉ በሌሎች ሀገራት አቅራቢዎች ባልተስተዋለ መነቃቃት በርካታ የሴሚናሩ ተሳታፊዎች “በእኔን አስቀድመኝ” ፉክክር እየተሽቀዳደሙ እጃቸውን እንደ ችቦ አንጨፈረሩ:: ለምን በኢትዮጵያ ጉዳይ ያን ያህል ጠያቂ ሊበዛ እንደቻለ ግራ የተጋባው ይህ ጸሐፊ ብቻ አልነበረም:: በወቅቱ አሜሪካን ሀገር በስደት ላይ የነበሩትና ያንን ሴሚናር እንዲያስተባብሩ እድል ቀንቷቸው ኃላፊነቱን የተረከቡት ብርጋዴር ጄኔራል ታዬ ጥላሁንም በሁኔታው መገረማቸውን ከሴሚናሩ በኋላ ጉዳዩን አንስተን ስንወያይ ስሜታቸውን አጋርተውኛል::

ጄኔራል ታዬ ጥላሁን ከቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ እስከ ወታደራዊ የደርግ አገዛዝ ዘመን በአየር ኃይል ውስጥ እስከ አዛዥነት፣ በባሕር ኃይልም እንዲሁ በሁለተኛ ረድፍ የሥልጣን እርከን ላይ፣ በመከላከያና በሀገር አስተዳደር ሚኒስቴር መ/ቤቶች ውስጥም በሚኒስትርነት ማዕረግ ሀገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት ያገለገሉ ታላቅ ሰብዕና የነበራቸው ጎምቱ ኢትዮጵያዊ ወታደር ናቸው:: በመጨረሻም ለአራት የስካንዲኔቪያን ሀገራት (ስዊድን፣ ኖርዌይ፣ ዴንማርክና ፊንላንድ) የኢትዮጵያ አምባሳደር በመሆን አገልግለዋል:: በመጨረሻም የወታደራዊ መንግሥትን አስተዳደር ተቃውመው ስደትን በመምረጥ በአሜሪካ ሀገር ይኖሩ ነበር:: ዛሬ ወደ ሀገራቸው ገብተው በሰላም እየኖሩ ይገኛሉ::

ለማንኛውም፡- ይህ ጸሐፊ በሴሚናሩ ተሳታፊዎች የተጠየቃቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች የሚከተሉትን ይመስሉ ነበር:: እናንተ ኢትዮጵያውያን ለምን ጦርነት ወዳድ ሆናችሁ? ለምንስ በረሃብ መቀጣትን ተለማምዳችሁ ለመኖር ወሰናችሁ? ሁልጊዜ የስንዴ ልመና አላሰለቻችሁም? ለምንስ ተፈጥሮና ፍጡር ፊታቸውን አዞሩባችሁ? የበቀደሙ አደጋ ራሱ ለሀገራችሁ የፖለቲካ አመራር ደካማነት ጥሩ ማሳያ ሊሆን አይችልም? መሪዎቻችሁ በጠብመንጃ አፈሙዝ ብቻ ሥልጣን ለመያዝ ከሚሞክሩ ለምን የዲሞክራሲ ባህልን አትለማመዱም? ወዘተ. ከብዙዎቹ ጥያቄዎች ጥቂቶቹ ነበሩ::

ሁሉም ጥያቄዎች የወቅቱ የሀገራዊ እውነታዎቻችን መገለጫዎች ስለነበሩ ከጠያቂዎቹ ጋር እንካ ሰላንትያ በመግጠም መሟገቱና መከራከሩ ፋይዳ አልነበረውም:: የነበረኝ ምርጫ እንደምንም ጥያቄዎቹን አለሳልሶና አድበስብሶ ለማለፍ ጥረት ማድረግ ነበር:: እውነትም በወጥመድ እንደተያዘች ድኩላ ከወዲያ ወዲህ መዝለሌ የተመደበውን የውይይት ጊዜ እምሽክ አድርጎ ስለበላው “ሰዓትህ አልቋል” ስባል የተነፈስኩት ከአጣብቂኝ መውጣቴ አስደስቶኝ “ቁና፣ ቁና” እየተነፈስኩ ጭምር ነበር:: እውነትን ሐሰት ነው ብሎ መሟገት ምንም ውጤት ስለሌለው::

> **አንዳንድ አክቲቪስት ተብዬዎችስ ችግራቸውና መንፈራገጣቸው ከምን ጋር የተያያዘ ነው? የእኔ ሃሳብ ብቻ ይምራ፤ እኔ ብቻ ልደመጥ፣ የእኔ ሃሳብ የሁሉም ችግሮች መክፈቻ ቁልፍ ካልሆነ፤ በሚል የቅዠት ባህር ውስጥ ስለሚዋኙ አይደለምን? ከያኒውንም፣ ነጋዴውንም ሆነ ሌላውን የማኅበረሰብ ክፍል በዚህን መሰሉ ወንጠፍት ብንፈትሸው መዳረሻው “እኔ ካልመራሁ፣ እኔ ቀድሜ ካልታየሁ፣ እኔ፣ እኔ ብቻ…” ከሚለው ምኞት የሚዘል ሆኖ አናገኘውም**

“የበቀደሙ አደጋ” ተብሎ በጥያቄው ውስጥ የተጠቀሰው ክስተት የተፈጸመው ይህ ጸሐፊ ያንን ሴሚናር ይካፈል በነበረበት ወቅት፤ ኅዳር 14 ቀን 1989 ዓ.ም፤ የበረራ ቁጥሩ ኢቲ 961 የሆነ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦይንግ 767 አውሮፕላን በዓላማ ቢስ ጠላፊዎች ክፉ ጭካኔ በኮሞሮስ ደሴት ላይ ተከስክሶ ከ175 ተሳፋሪዎችና የአየር መንገዱ ሠራተኞች መካከል 125ቱ ሕይወታቸውን ሲያጡ 50 ያህሉ በፈጣሪ ተዓምር መትረፋቸውን በማስታወስ ነበር:: በዚህ አደጋ ምክንያት ሕይወታቸውን ካጡት መካከል የጸሐፊው የቅርብ የሥራ ባልደረባ የነበረው የኢትዮጵያና የሕዝቧ ወዳጅ እንግሊዛዊው ሚ/ር አንዲ ሚከንስ እና ሌላ አንድ ወዳጄ ይገኙበት ነበር:: በተዓምር ከተረፉት መካከልም አንዱ የቅርብ ጎረቤቴ ዶ/ር ይስሐቅ ነበሩ:: እኚህ ሰው ከአደጋው ከተረፉ በኋላ ዕድሜ ተጨምሮላቸው ለዓመታት ከኖሩ በኋላ በተፈጥሮ ሞት የተለዩን ከጥቂት ዓመታት በፊት ነበር::

ወደ ሴሚናሩ ትዝታ እንመለስ:: ከሥልጠናው መጠናቀቅ በኋላ እያንዳንዱ ተሳታፊ ወደ ሀገሩ እንደተመለሰ መሻሻል አለበት ብሎ በሚያምንበት የሀገሩ ሁለንተናዊ የአመራር ስልት ዙሪያ እንደ አንድ አደራ ተቀባይ የተማረውን ለወገኖቹ ለማስተላለፍ ቃል ኪዳን መግባት ይጠበቅበት ነበር:: አንድም ተመሳሳይ ሴሚናር በማዘጋጀት ከተባባሪ ወገኖችና ተቋማት ጋር በማበር አደራውን በትጋት መወጣት ወይንም በአመራር ዙሪያ መጽሐፍ መጻፍ ከአማራጮቹ መካከል ጥቂቶቹ ነበሩ::

ይህ ጸሐፊም እንደሌሎቹ ተሳታፊዎች ቃል የገባው ሁለቱንም አማራጮች እተገብራለሁ በማለት ነበር:: የተማረውን በሥልጠና ለማካፈልና በአመራር ዙሪያ ቢያንስ አንድ መጽሐፍ ለመጻፍ:: “ቃል የእምነት ዕዳ ሆኖበትም” ኪዳኑን አክብሮ በ2001 ዓ.ም “የአመራር ጥበብ” በሚል ርዕስ መጽሐፍ ጽፎ ለአንባቢያን እንዲደርስ አድርጓል:: የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖም መጽሐፉ በከፍተኛ ሁኔታ ተወዳጅነት በማትረፉ ተደጋግሞ ለመታተም በቅቷል::

ከገጠመኞቹ ጋር በማዋዛት በአጭሩ በዚህ ጽሑፍ ለመቃኘት የሞከረውም ከስልጠናው በኋላ የቀመረውን ሦስት የሀገራዊ የአመራር ተግዳሮቶቻችንን ከዛሬ እውነታችን ጋር በመፈተሽ በወፍ በረር ቅኝት ለመዳሰስ በማሰብ ነው:: ሦስቱ የተባሉት ተግዳሮቶች የሚከተሉት ናቸው፡- መሪነትን ማን ይጠላል? መመራትስ መች ይወደዳል? ያለ መሪስ እንዴት መኖር ይቻላል? ዛሬያችን ላይ ጫን በማለት ጥያቄዎቹን ተራ በተራ እንፈትሻቸው::

**ሀ. መሪነትን ማን ይጠላል?** መልሱ ብዙ ምርምር አይጠይቅም:: መሪነትን ማንም አይጠላም:: ይህ ጥያቄ ስለ ውጤታማ መሪነት ብዙ ጉዳዮችን እንድንዳስስ ያበረታታናል:: በርግጥም መሪ መሆን፤ አቅም ይኑርም አይኑር፤ የሚጠላ አይደለም:: ምክንያቱም የመሪነት ፍላጎት ተፈጥሯዊ እንጂ ከቀን በኋላ የሚጎናጸፉት ክህሎት አይደለም:: በማንኛውም የሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች አንድ የጋራ ዓላማ ለማስፈጸም ሲሰባሰቡ ከመካከላቸው አንዱ ቀዳሚ መሪ ሌሎች ተከታይ እንዲሆኑ የግድ የሚለን ሰብዕናችን ጭምር ነው::

ለምሳሌ፡- የዕለት ተዕለት የሕይወታችን እንቅስቃሴ ልብ ብለን እናስተውል:: ቡሄ ጨፋሪ ልጆች፣ የ“አበባ አየሽ ወይ” ባህላዊ ከዋኝ ልጃገረዶችና የጨርቅ ኳስ ተፋላሚ ቡድኖች ሳይቀሩ ወደ ባህላዊ ጨዋታቸው ከመግባታቸው አስቀድሞ መጀመሪያ የሚወስኑት ተቀዳሚ ተግባራቸው የቡድን አለቃቸውን ወይንም ካፒቴናቸውን መምረጥ ነው:: የወጣቶችና የጎልማሶች የገና ጨዋታም የገና አባት ሊኖረው ግድ ይላል:: ሙሽራና ሙሽሪይቱም ቀዳሚና አስተባባሪ ሚዜዎች መሰየም ይጠበቅባቸዋል:: የእናቶችና የአባቶች ማኅበርም “ሙሴ” አለው ወዘተ. “መሪነትን የሚሹ” በርካታ መሰል ተሞክሮዎችን መዘርዘር ይቻላል::

መሪ፣ አለቃ፣ አስተባባሪ፣ ዳኛ፣ ሹም፣ ሥራ አስኪያጅ፣ የኮሚቴ ወይንም የቦርድ መሪ፣ ጠቅላይ ሚኒስትርም ይሁን ፕሬዚዳንት የተለያየ ስያሜ ይምሰሉ እንጂ ጽንሰ ሃሳባቸውና ተልእኳቸው በየደረጃቸውና በሥልጣን ክልላቸው ልክ ሌሎቹን በመምራት፤ ወይንም ፊት ቀድሞ በመታየት ተከታዮችን በማስተባበር ተልዕኮን ማሳካት ነው:: በአጭሩ መሪነት ነው:: እንኳን የሰው ልጆች ቀርተው መላእክትም ቢሆኑ መሪ አለቃ እንዳላቸው በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ “የመላእክት አለቃ ሚካኤል” ተብሎ ተጠቅሷል:: ስለዚህም ነው መሪነት ተጠልቶ የሚገፈተር አይደለም የሚባለው::

እርግጥ ነው መሪነት እንደምናስበው ቀለል ተደርጎ ብቻ የሚበየን እንዳልሆነ አይጠፋንም:: ብቃቱና አቅሙ ያለው ባለ ራዕይና ለውጤት የጨከነ መሪ መልካም ተመሪዎችን መፍጠሩ እውነት ነው:: በአንጻሩም መልካም ተመሪም መልካም መሪን ለመፍጠር እድሉ የሰፋ ነው:: የውጤታማ መሪን ባህርያትና መርሕ በዝርዝር ለመተንተን የገጹ ውስንነት ስለሚገድበን ከዚህ በላይ ብዙም አንልም::

የሀገራችንን ወቅታዊ ሁኔታዎች ጠለቅ ብለን ስንፈትሽም ደረጃው ቢለያይም የችግሮቻችን ዋነኛው ማጠንጠኛ ከመሪነት ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ አያከራክርም:: ፖለቲከኞች የሚያምሱን ለምንድን ነው? እኔ ብቻ ካልመራሁ፣ የእኔ ሃሳብ ብቻ ካልተደመጠና ሥራ ላይ ካልዋለ በማለት አይደለምን? ጫካ ተሸሽገው የሚወጉን፣ በአሸባሪነት ተፈርጀው “ሀገርን ካላፈረስን” እያሉ ጦር የሚሰብቁት ምክንያታቸው ምንድን ነው? የመሪነት ወንበር ላይ ለመፈናጠጥ አይደለምን? አንዳንድ አክቲቪስት ተብዬዎችስ ችግራቸውና መንፈራገጣቸው ከምን ጋር የተያያዘ ነው? የእኔ ሃሳብ ብቻ ይምራ፤ እኔ ብቻ ልደመጥ፣ የእኔ ሃሳብ የሁሉም ችግሮች መክፈቻ ቁልፍ ካልሆነ፤ በሚል የቅዠት ባህር ውስጥ ስለሚዋኙ አይደለምን? ከያኒውንም፣ ነጋዴውንም ሆነ ሌላውን የማኅበረሰብ ክፍል በዚህን መሰሉ ወንጠፍት ብንፈትሸው መዳረሻው “እኔ ካልመራሁ፣ እኔ ቀድሜ ካልታየሁ፣ እኔ፣ እኔ ብቻ…” ከሚለው ምኞት የሚዘል ሆኖ አናገኘውም:: ስለዚህም ነው መሪነትን ማንም አይጠላም የሚባለው:: ምክንያቱም ውጤት ሲገኝ ዝና ይኖራል፣ ክብር ይገኝበታል፣ ጥቅምም አይጠፋውማ:: ብሂላችንስ “መሪ የሌለው ጨንባሳ፤ ምርኩዝ የሌለው አንካሳ” ብሎ ማረጋገጫውን ይሰጠን የለ::

**ለ. መመራትስ መች ይወደዳል?** እርግጥ ነው ካልቸገረ በስተቀር ማንም ሰው መመራትን አይወድም:: አሁንም የመከረኛዋን ሀገራችንን አሳር ልብ ተቀልብ ሆነን ብንፈትሽ “የመመራት ጥዩፍነት” አንዱ፤ ምናልባትም ተቀዳሚ ሀገራዊ ችግራችን ሳይሆን እንደማይቀር ይታመናል::

የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን ለምን ህመምተኛ ሆኑ? የማኅበረሰብ አንቂዎች ተብዬዎችስ ከሃሳብ አፍላቂነት ይልቅ ለምን “ጦር ሰባቂነትን” መረጡ? ከወታደራዊ ክፍሎች በስተቀር በአብዛኛው መንግሥታዊና ሕዝባዊ ተቋማት ውስጥ የሚስተዋለው የመሪና ተመሪ መናናቅ መንስኤው ከምን የመነጨ ነው? መብትና ግዴታ መልካቸው ጠይሞ ግራ መጋባት ላይ የደረስነው “ለመመራት አለርጂ” የሆኑ “ደመወዝተኞች” ወይንም ጥቅመኞች እንደ አሸን በመፍላታቸው ምክንያት አይደለምን? “ሆድ ያባውን…” እንዳይሆን እንጂ፤ ብዙ ጉዳዮችን መዳሰስ ይቻል ነበር::

**ሐ. ያለመሪስ እንዴት መኖር ይቻላል?** “መሪ የሌለው ሕዝብ፤ አውራ የሌለው ንብ” እንዲል ምሳሌያችን፤ አለመሪ እኖራለሁ ማለት ውጤቱ እንደ ብሂሉ መንጋነት ነው:: “በመንጋ አስተሳሰብ” ሆ! በማለት ብቻ ያለ መሪ ለመኖር መኖር አይቻልም:: ብዙዎች የሚፋንኑት፣ “እንዳሻን እንሁን ልቀቁን” በማለት ሀገርና ሕዝብ ጤና የሚያጣው፤ “እሽ አትበሉን የንጉሥ ዶሮ ነን” እያሉ አዛዥ ናዛዥ አንፈልግም የሚል የመንጋ አስተሳሰብ ባላቸው ዜጎች አይደለምን? ሆድ ይፍጀው!

**ማጠቃለያው** እንዲህ ነው:: መሪነትን መመኘትና መጓጓት መብትም ነው፤ ሰብዕናችንም ይፈቅድልናል:: ቢሆንም ግን ለመምራት የራዕይ ጽንስ፣ የማስፈጸም ብቃት፣ ለተመሪዎች ፍቅርና ርህራሄ፣ ከራስ ምኞት ይልቅ ለተከታዮች አክብሮትና ለኅሊና ተገዥ መሆን ቀዳሚ መስፈርቶች ናቸው:: አምባገነንነት ለጭቆና እንጂ ለመሪነት ፋይዳ የለውም:: በተመሪዎች ጭንቅላት ላይ የባቢሎን ግንብን እየገነቡ ወደ ሰማየ ሰማየት ለመክነፍ የሚሞከርበት የአመራር ዘዴ ትርፉ በራስ ላይ ፈርዶ እንዳልሆኑ መሆን ነው::

እርግጥ ነው መሪነትን የሚጠላ የለም ብለናል:: መመራትም ላይወደድ ይቻላል:: ያለ መሪ ለመኖር መወሰን ግን እብደትም፤ መታወርም ነው:: “ላብ ደምን ያድናል” የሚል የተለመደ ወታደራዊ አባባል አለ:: ውጤታማ መሪ የዕይታ አድማሱ ሩቅ ነው:: ግቡም የተመሪው ስኬት ነው:: መዳረሻ ውጤቱ “የላብና የደም ግብርን” ቢጠይቅ እንኳን ራሱን መስዋዕት አድርጎ ለማቅረብ አያመነታም:: ልቡም ነፍሱም ለግቡ ስኬትና በተመሪዎች ፍቅርና አደራ የታሰረ ነው:: እንዲህም ቢሆን ግን መሪው መሞገስንም ሆነ መነቀፍን፣ መተቸትንም ሆነ መመስገንን በልበ ሰፊነት ለማስተናገድ ጫንቃው መደደር አለበት:: የውጤታማ መሪ ኒሻኑና ሜዳሊያው የተከታዮቹ ደስታ ነው:: በዘመናት ውስጥ የመሪ ያለህ ጩኸት የበረከተውም ይህን መሰሉን ጸጋ ለመጎናጸፍ ከመትጋት ይልቅ እንደ ባህላዊው የሀገራችን የ“ሆያ ሰለሜ” የሙዚቃ አጃቢ ትርዒት ጅራፍን ለሰልፍ አስከባሪነት መጠቀም ሲጀመር ነው:: ከተመሪው አንጻር ካየነውም መመራትን ጠልቶ ያለ መሪ ካልኖርኩ በሚል ራስ አምላኪነት ፍልስፍና ሕግን ማስለቀስ ሲጀምር “እመቤት ሆይ ፍትሕ” (Lady Justice) ሰይፏን ለመሪው ለማዋስ የዐይኗን መሸፈኛ ጥቁር ቱቢት ብትገልጥ አግባብ አይደለም ብሎ ለመሟገት ያዳግታል:: መሪነትን ማን ይጠላል? መመራትስ መች ይወደዳል? ያለመሪስ እንዴት መኖር ይቻላል? ትዝታዬና እውነቱ ይህን ይመስላል! ሰላም ይሁን!

# ተናጋሪው ዶሴ

## ዝቅተኛ የሥራ አፈፃፀም፤ ያመጣው መዘዝ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ከሳሽ ፍርድን በመሻት ስኳር ኮርፖሬሽንን ችሎት አቁመዋል። ግራ ቀኝ ሙግት በመግጠም በሥር ፍርድ ቤት የተወሰነውን አልፈፅምም በሚል እሳቤ እስከ ሰበር ደርሷል። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች የሚያሳትም ሲሆን፤ በቅፅ 15 በሰነድ መለያ ቁጥር 84661 መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ዳኞች ተሰይመው እና አመልካች አቶ ዳዊት ሸዋቀና በአካል ሳይቀርቡ እና ተጠሪው ስኳር ኮርፖሬሽን ነገረ ፈጅ አቶ ጌታቸው አክሊሉ ቀርበው መዝገቡ ተመርምሮ ፍርድ ተሰጥቷል። የዝግጅት ክፍላችንም የክርክሩን ሂደት በዚህ መንገድ አቅርቦታል።

### የክሱ ጭብጥ

ለእዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ተከሳሽ ነበር። ክሱም በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ የኦዲት ክፍል ኃላፊ ሆኜ እየሠራሁ የሥራ አፈጻጸምህ ዝቅተኛ ነው፤ እንዲሁም በሥራ ላይ ቸልተኝነት አሳይተሃል በሚል ያለማስጠንቀቂያ ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም የሥራ ውሌን ያቋረጠብኝ በመሆኑ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ ካልሆነም ካሳ፣ የስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ክፍያ በዘገየበት እና የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው።

### ተከሳሽ ምን አለ?

ለክሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በአማራጭ በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ ሰጠ። ከሳሽ ከሥራ የተሰናበቱበት ምክንያት በተሰጣቸው የስንብት ደብዳቤ ላይ የተገለጸላቸው ሲሆን፤ ወደ ሥራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄም ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፤ እንዲሁም እንዲከፈላቸው ከጠየቁዋቸው ክፍያዎች ውስጥ የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ ተከፍሏቸዋል። ሌሎች ክፍያዎች ዳግሞ ሊከፈሏቸው አይገባም ሲል ተከራከረ።

### የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ


የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተከሳሽ ያቀረበውን መቃወሚያ ቀደም ሲል በብይን ውድቅ ማድረጉን በመግለጽ በሰጠው ፍርድ፤ ተከሳሽ ለከሳሽ በጻፈው የስንብት ደብዳቤ የሥራ አፈጻጸማቸው ሲገመገም ዝቅተኛ ስለመሆኑ የተመዘኑበትን ማስረጃ ካለመቅረቡም ሌላ በሥራቸው ቸልተኝነት አሳይተዋል ቢልም በምን ምክንያት ቸልተኝነት እንዳሳዩ አልዘረዘረም በማለት የሥራ ውሉ በሕገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል ሲል ወስኗል።

ከሳሽ በአማራጭ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ማለትም የሥራ መሪ ያለበቂ ምክንያት ከሥራ አሠሪው ቢያሰናብት ወደ ሥራ የመመለስ መብት እንዳለው በፍትሐብሔር ሕጉ፣ በኅብረት ስምምነቱም ሆነ በሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ ስላልተገለጸ ተቀባይነት የለውም ሲል ወድቅ አድርጓል። ከሳሽ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን ክፍያዎች በተመለከተም የስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ሲወስን፤ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ግን ከሳሽ የሚሠሩበት ሥራ የእምነት ሥራ እና ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆኑ ማስጠንቀቂያ አለመስጠት በፍትሐብሄር ቁጥር 2577(2) መሠረት ኪሣራ የሚያስከትል አይሆንም ሲል አልተቀበለውም።

ካሳ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄንም የሕግ መሠረት ያለው አይደለም በሚል ውድቅ ሲያደርግ፤ የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ የተከፈላቸው መሆኑንም በቃል ክርክር ወቅት ከሳሽ ስላመኑ በድጋሚ ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል። እንዲሁም ክፍያ በዘገየበት የጠየቁትን ክፍያ በተመለከተም የሚከፈላቸው ክፍያ አይኖርም ሲል ሳይቀበለው ቀርቷል።

### ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ከሳሽም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የይግባኙን መዝገብ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 337 ዘግቶ በማሰናበቱ የሰበር አቤቱታቸውን ለችሎት አቅርበዋል። አመልካች በሰበር አቤቱታቸውም በዋናነት ያቀረቡት የቅሬታ ነጥብ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና ካሳን ፍርድ ቤቶቹ በአዋጅ ቁጥር 377/1996፣ በኅብረት ስምምነቱና በሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ አግባብነት ባላቸው




ድንጋጌዎች መሠረት መወሰን ሲገባቸው ሳይወስኑ ማለፋቸው አግባብ አይደለም ብሏል።

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ፤ ኮርፖሬሽኑ በደንብ ቁጥር 192/2003 የተቋቋመ ሆኖ እያለ አመልካች የተሻሩትን የሥራ መመሪያዎች ደንብና የኅብረት ስምምነት መሠረት በማድረግ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል።

አመልካች ተጠሪው ላቀረቡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል። የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት በሕገ ወጥ መንገድ ነው በሚል የሥር ፍርድ ቤቶች ከወሰኑ በኋላ ካሳና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም ያሉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? በሚል መዝገቡ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል በተያዘው ጭብጥ መሠረት ክርክሩ ምርመራ ተደርጎበታል።

ተጠሪው ድርጅት በአዲስ መልክ በደንብ ቁጥር 192/2003 የተቋቋመ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የሥር ፍርድ ቤቶች ፍርድ ለመስጠት መሠረት ያደረጉት የሥራ መሪዎች ደንብና የኅብረት ስምምነት ስለተሻሩ አግባብነት የላቸውም ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑ ሊመረመር የሚገባ ሆኖ አግኝተናል ይላል ፍርድ ቤቱ።

በደንብ ቁጥር 192/2003 ተፈጻሚ የሆነው ከጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ስለመሆኑ በደንቡ አንቀጽ 12 የተደነገገ ሲሆን፤ አመልካችም ክሱን ያቀረቡት ጥር 27 ቀን 2004 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ የቀረበው ደንቡ ጸንቶ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ነው። በዚህ ደንብ ቀደም ሲል በየራሳቸው የማቋቋሚያ ደንብ ተቋቁመው የነበሩት አራት የስኳር ፋብሪካዎች የስኳር ኮርፖሬሽን በሚል መቋቋማቸውን ከደንቡ መገንዘብ የሚቻል ነው።

ይሁን እንጂ ተጠሪው ቀደም ሲል በደንብ ቁጥር 122/1998 እንደተሻሻለው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በሚል ሲጠራ የነበረ ሲሆን፤ የራሱ የሆነ የኅብረት ስምምነት እና የሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ ያለው ነው። ተጠሪው የኅብረት ስምምነቱና የሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንቡ ተሽረዋል በሚል ክርክር ስለማቅረቡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የማያመላክት ሲሆን ክርክር አቅርበዋል ቢባል እንኳን ፍርድ ቤቱ ባለመቀበል በተሻሩ የሥራ መመሪያዎች ደንብና የኅብረት ስምምነቱ መሠረት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሰጥቶ ከሆነ ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በማቅረብ ፍርዱን ማስለወጥ ሲገባው ይግባኝ አቅርቦ አላስለወጠም።

በዚህ በሰበር ደረጃ ባደረገውም ክርክር የኅብረት ስምምነቱ እና የሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ መሻራቸውን ከመግለጹ በስተቀር በየትኛው የኅብረት ስምምነትና የሥራ መሪዎች ደንብ እንደተተኩ አልጠቀሰም። ስለሆነም የኅብረት ስምምነቱና የሥራ መመሪያዎች መተዳደሪያ ደንብ የተሻሩ ናቸው ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

ዳኞች እንደሚሉት፤ ወደ ጭብጡ ስንመለስ ተጠሪው የሥራ ውሉን ለመቋረጥ የጠቀሳቸው ምክንያቶች የአመልካች የሥራ አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ ነው፣ እንዲሁም በሥራ ላይ ቸልተኝነት አሳይተዋል በሚል እንደሆነ ለሥር ፍርድ ቤቶች በማስረጃነት ከቀረበው የስንብት ደብዳቤ የተረጋገጠ ሲሆን፤ ተጠሪውም አመልካች በሥራ አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ ስለመሆኑ የተመዘኑበትን ማስረጃ ባለማቅረቡ እንዲሁም በሥራ ላይ ቸልተኝነት አሳይተዋል ላለውም ምክንያቱን በመዘርዘር ማስረዳት ባለመቻሉ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የስር ፍርድ ቤቶች ደርሰዋል።

በመሆኑም የሥራ ውሉ በሕገ ወጥ መንገድ መቋረጡ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር እስከሆነ ድረስ ተጠሪ ካሳና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፍል የሚገባ መሆን አለመሆኑን አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ መመልከት ይገባል። ከክርክሩ መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች ሥራ መሪ ናቸው። አሠሪው የሥራ ውሉን ቀሪ በማድረግ ወይም አላድስም በማለት ይህን ውሳኔ በግልጽ የሚያረጋግጥ በቂ ምክንያት የሌለው እንደሆነ ሠራተኛው ተገቢ የሆነ ኪሳራ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ቁጥር 2573 ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው።

በዚህ መልኩ በሕጉ የሥራ ውሉ በቂ ባልሆነ ምክንያት የተቋረጠ ከሆነ አሠሪው ኪሳራ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የተሰናበቱት ያለበቂ ምክንያት መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ካረጋገጡ በኋላ ኪሳራውን ሳይወስኑ ማለፋቸው ሕጉን የተከተለ አይደለም። ኪሳራ መክፈል ተገቢ መሆኑ ከታመነ ደግሞ ስለሚከፈልበት ሁኔታም አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መመልከት የሚገባ ነው።

አመልካች በክሳቸው የስድስት ወር ደመወዝ ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁት አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት በማድረግ ነው። አንድ የሥራ መሪ የሥራ ውሉ ያለ በቂ ምክንያት ሲቋረጥ ሊከፈል የሚገባው የኪሳራ ልክ ሠራተኛው ባለፈው ሶስት ወር ከተቀበለው ደመወዝ ሊበልጥ እንደማይችል በፍትሐብሔር ቁጥር 2574 (2) የተደነገገ ሲሆን ይህንኑ የሕግ አነጋገር በመያዝ በታኅሳስ ወር 2002 ዓ.ም ወደወጣው የተጠሪ የሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ ስንመለስ በአንቀጽ 51(1) በዚህ ደንብ ውስጥ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በሌሎች ሕጎች ፣ደንቦች ወይም በሌላ አኳኋን ተለይቶ የተወሰነው የተሻለና የበለጠ ጥቅም የሚያስገኝ ሆኖ በዚህ ደንብ ውስጥ ባልተጠቀሱም ሆነ በተጠቀሱ ጉዳዮች፣ በኅብረት ስምምነት የተደነገጉት፣በአሠራር ደንብ የተወሰኑትና የሚታወቁት ስለሥራ ሁኔታ፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት፣ የሥራ አካባቢ፣ ጥቅሞች፣ ግልጋሎቶች፣ ሥልጠና፣ የሥራ ውጤት መለኪያ ዘዴ እንዲሁም ይህን ደንብ የማይቃረኑ አግባብ ያላቸው ሌሎች የሥራ ውል ግንኙነቶች የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች የሥራ መሪው የሥራ ውል አካል ሆነው ይቆጠራሉ በሚል ተደንግጎ እናገኛለን።

በዚሁ ድንጋጌ መሠረትም በፍትሐብሔር ሕጉ ከተመለከተው የኪሳራ መጠን ይልቅ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43(4)(ሀ) የተመለከተው የካሳ መጠን የተሻለ ጥቅም የሚያስገኝ በመሆኑ ለአመልካችም ተጠሪው ካሳ ሊከፍላቸው የሚገባው በዚሁ የአዋጁ አንቀጽ መሠረት ሊሆን ይገባል።

ሌላው አመልካች የጠየቁት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ነው። ተጠሪው የአመልካችን የሥራ ውል ሲያቋርጥ ቅድመ ማስጠንቀቂያ አለመስጠቱ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶችም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለአመልካች አይገባቸውም በሚል የወሰኑት አመልካች የሚሰሩት የሥራ ባህሪ በመግለጽ ሲሆን ለዚህም መሠረት ያደረጉት የፍትሐብሔር ቁጥር 2577(2) ድንጋጌን ነው።

በዚህ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር (1) የሥራው ውሉ ልዩ የሆኑ ችሎታዎችን የሚጠይቁ፣የእምነት ሥራዎች እንደሆኑ አሠሪው ውሉን ቀሪ የሚያደርግበትን ወይም የማያድስበትን ምክንያት ለማስታወቅ የማይገደድ መሆኑ የተደነገገ ሲሆን ኪሳራ ለመክፈል የሚገደደው ግን ውሉ እንዲቀር የተደረገው በማይገባ ጊዜና አንደኛውን ወገን ለመጉዳት ወይም ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት ባለማሰብ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። ከዚህ ውጪ ግን የውሉ ያለ ማስጠንቀቂያ ቀሪ መሆን አሠሪው ለሠራተኛው ኪሳራ እንዲከፍል የሚያስገድድ አይሆንም።

በዚህ ጉዳይ ግን ውሉ ቀሪ የተደረገው በማይገባ ጊዜ ወስጥ ስለመሆኑ፣ ወይም ተጠሪው አመልካችን ለመጉዳት ወይም ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት ባለማሰብ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ውሉን ቀሪ ስለማድረጉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የለም። አመልካች በተጠሪው ድርጅት የኦዲት ክፍል ኃላፊ የነበሩ እንደመሆናቸው መጠን የሥራ ውሉ ልዩ ችሎታን የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ ሥራውም በእምነት የሚሠራ በመሆኑ አስቀድሞ የሥራ ውል የሚቋረጥ ስለመሆኑ ማስታወቅ የአሠሪውን ጥቅም ሊጎዳ የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጥር ስለሚችል ማስጠንቀቂያ አለመሥጠቱ በፍትሐብሔር ቁጥር 2577(2) እንደተመለከተው ኪሳራ እንዲከፍል የሚያስገድደው አይሆንም።

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ለአመልካች ከሚሠሩት የሥራ ባህሪ የተነሳ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ የሥራ ውሉን በማቋረጡ ምክንያት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለመክፈል አይገደድም ያሉት የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም።

በመሆኑም ሃሳቡ ሲጠቃለል፤ የስር ፍርድ ቤቶች ለአመልካች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም ያሉት ከዚህ በላይ በተገለጹት ምክንያቶች የተነሳ ተገቢ በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም በሚል ፍርድ ቤቶቹ የወሰኑት ተገቢ ቢሆንም የሥራ ውሉ በሕገ ወጥ መንገድ የተቋረጠ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ ግን ካሳ እንዲከፈላቸው ሳይወስኑ ያለፉት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል ብሏል -ፍርድ ቤቱ።

#### ው ሣ ኔ

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመለያ ቁጥር 03537 በ15/10/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ፍርድ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመለያ ቁጥር 126268 በቀን 17/12/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጠው ትዕዛዝ ተሻረ ፡፡ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤቶች የሥራ ውሉ በተጠሪው ሕገ ወጥ ድርጊት ተቋርጦ እያለ ለአመልካች የካሳ ክፍያ እንዲከፈላቸው ሳይወስኑ ማለፋቸው ተገቢነት የሌለው መሆኑ ተጠቅሶ፤ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43(4)(ሀ) መሠረት የአመልካች የቀን አማካይ ደመወዝ በ180 ተባዝቶ እንዲከፈላቸው ተወሰነ፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ከካሳ ክፍያ በስተቀር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያም ሆነ ሌሎች ክፍያዎችን በተመለከተ የሠጡትን ውሳኔ የፀና ሲሆን፤ የካሳ ክፍያ አፈጻጸም ክሱን የያዘው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይጻፍ የተባለ ሲሆን፤ የፍርድ ቤት ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ በማለት መዝገቡ ተዘጋ፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## በአቋራጩ መንገድ መንገዳገድ

ተገኝ ብሩ

መንገዱ ብዙ የሚያስጉዝ ይመስላል፤ ነገር ግን እጅግ አጭር ነው:: ለአውነት በቀረቡ ትዕይንቶችና ትረካዎች ስለሚታጀብ ብዙዎች ያጎርፉል፤ ነገር ግን መድሻው እሾህማ ውጤቱ ደግሞ የከፋ ነው:: በተለይ በዚህ ቴክኖሎጂ በተንሰራፋበት አለም ይህ አቋራጭ መንገድ ብዙዎች ሊጠቀሙበት ይፈልጋሉ:: በርካቶች ጅማሮው ላይ ባዩት ተታለው አቋራች ነው ባሉት የተሳሳተው መንገድ ገፍተው ይሄዱበታል::

ምን አልባት ዕድለኛ ሆነው ብዙ ሳይገፉ ከመንገዱ ከሚመለሱት በስተቀር፤ በዚያው ላይመለሱ እስከመጨረሻው የሚሄዱ ይበረክታሉ:: ተጓዦቹ ብቻቸውን ቢሆን መልካም ነበር፤ ነገር ግን ብዙዎችን አሳስተውና የበርካቶችን አመለካከት አዛብተው ማስኬዳቸው ነው ክፋቱ:: እያወራሁ ያለሁት በዚህ በአሁኑ ዘመን በማህበራዊ ሚዲያ ውሸት መነሻቸው አድርገውና እብለትን ተመርኩዘው ለመታወቅ ስለሚሯሯጡ ግለሰቦች ነው:: በርካቶቹ ዩቱዩብ፣ፌስ ቡክና ቲክ ቶክ ላይ መዋያና ማደሪያቸው አድርገዋል:: እነዚህ ተጠቅመው በአቋራጩ መንገድ ብዙዎችን ጠልፈው ያስገባሉ::

በአሁኑ ወቅት እውነት ከሚናገረው ይልቅ የሚሰማው የሚቀጥፈው ሆኗል:: ሀቅ ላይ የቆመው ሳይሆን የሚደመጠው የሚያስመስለው መስሏል:: ሰበቦችና ተጨባጭ ያልሆኑ ምክንያቶች ደርድሮ እንዲህ ሆነ አልያም ደግ እንዲያ ተባለ ብሎ እውቅናን በመቀዳጀትና ወዳጅ ማብዛት ለብዙዎች አቋራጭ መንገድ ሆኗል:: ለእርነሱ ዋንኛ ጉዳይ ተከታይ ማብዛት በሚያገኙት የእይታ መጠን ገንዘብ መሰብሰብ በሚመለከትላቸው ሰው ልክ ንዋይ ማጋበስ ነው:: እኛ ደግሞ መረጃ ለመስማት ጉጉ ነንናወደነሱ እንቃረባለን:: ባልተረጋገጠና ተጨባጭ ላልሆነው ትክታቸው ተገዢ ለተዛባ መረጃቸው ተጠቂ ያደርናል:: እነሱ ለመታወቅ ብለው የጀመሩት አቋራጩ መንግድ እኛን አስጉዞ ከማይበጀን ቦታ ያደርሰናል::

እናንተዬ ኢትዮጵያችን እነሱ ከላይ የጠቀስኩላችሁ ማህበራዊ ሚዲያ እየተጠቀሙ እንደሚገልጹልን አይነት ብትሆን ኖሮ ምን ይውጠን ነበር:: ደግነቱ እነሱና እውነቱ እጅጉን የተራራቁ ናቸው:: እነሱ በሚወሸክቱት የሚያገኙትን ገቢ ላይ ተመርኩዘው አልያም ይህቺን አገር ለመጉዳት ከሚያሴሩት ጋር አብረው የእኛን አሉታዊ ሁነቶችን ሁሉ አግዝፈው ያቀርባሉ:: የፈካ ገፅታችንን ሸፍነው ያልነውን ያሳዩናል:: አንድነታችን መላላቱን፣ የእርስ በርሳችን መፋጀት፣መጠላላት፣መነቋቆር፣መገፋፋት መለያችን አድርገው በጥቂት መነሻና በብዙ ቅጥፈት እያጎሉ ለእኩይ አላማቸው ያውሉታል:: በአቋራጭ ለመክበርና ለመታወቅ ይጠቀሙበታል::

አሁን ላለንበት አገራዊ ሁኔታ መውጫ ይሆነን ዘንድ ጥበብንና ትዕግስት የእኛ መለያ ሊሆን ይገባል:: እውነትን ለማየት ጥበብ መጠቀምና እውነታው ከሀሰቱ እንዲለይ መታገስ በብርቱ ያስፈልጋል:: የጠቢቡ ሰለሞንን ጥበብ መላበስ የእዮብን ትዕግስት መጎናፀፍ ያሻናል:: ጥበብ መላበስ እውነትን ከሀሰት ያስለያል:: ትዕግስት ደግሞ ከተሳሳተ እርምጃ ይጠብቃል::

አዎ ነገሮችን በጥበብ መለየት ከአሳሳቾች ይጠብቃል:: ጠቢቡ ሰለሞን ሁለት እናቶች አንድን ህፃን ልጅ "የእኔ ነው፤ የእኔ" በሚል ክርክር ገጥመው የህፃኑ ልጅ እናት ማንነት የለየበት ልዩ ጥበብ ያስደንቀኛል:: ወዶቹ አስቡትማ ያቺ የምር ልጅዋን በሌላ "የእኔ ነው" የተባለባት እውነተኛዋ የህፃኑ እናትና የራስዋን ያልሆነን ልጅ "የእኔ ነው" ያለችው እናት መሀል ያለው ልዩነት::

በእርግጥ ሁለቱም እናቶች ልጅ ወልደው ነበር:: አንደኛዋ ወዲያው በሞት ተነጠቀች እንጂ:: አያችሁ ይህ ለጉዳዩ እውነትነት የቀረበ ምክንያት ነው:: ሁለቱም መውለዳቸው:: እናት የወለደችው ልጇን ታቅፋ በተኛችበት በዚያች ወልዳ ልጇ በሞተባት እናት ተሰረቀባት:: እናት የእስዋ ልጅ ፈፅሞ እንዳልሞተና እንደተሰረቀባት ባወቀች ጊዜ ልጄን መልሽልኝ አለቻት:: ነገር ግን ልጅዋን በሞት ያጣችው እናት "አይ ይሄ የእኔ ልጅ ነው፤ የአንቺ ሞቷል" አለች::

ይሄኔ ክርክር ተነሳና አለመግባባቱ ጠነከረ:: ሁለቱም እናቶች ልጁ የእኔ ነው በሚል ሙግት ውስጥ የሚያስታርቃቸው ጠፋ:: በመጨረሻም ንጉሱ ዘንድ ቀረቡ:: ይህ ንጉስ ጥበበኛ ነበርና ሁለቱንም ጎን ለጎን አቁሞ ሀሳባቸውን ጠየቀ:: ሁለቱም ልጄ ነው ያሉበትን ምክንያትና እውነት አስረዱ:: ያቀረቡት ማስረጃ ሁሉ ግን ተመጣጣኝ ነበር:: እውነትና ውሸት ልክ የሚያስመስል ማስረጃ ታውቃላችሁ:: ልክ እንደዚያ ማለት ነው:: ይሄኔ ጥበበኛው ንጉስ አንድ ነገር አሰበና ለወታደሮቹ እንዲህ ብሎ አዘዛቸው::

ጎራዴ አምጡና ልጁን ለሁለት ቦታ ክፈሉት እናም የልጁን አካል ግማሽ ግማሽ ይካፈሉት አላቸው:: ሴቶቹም በዚህ ይስማሙ እንደሆን ጠየቀ:: ይሄን አንደኛዋ እንደተስማማች ተናገረች:: አንደኛዋ ደግሞ በዚህ ሀሳብ ደንግጣ ተብረከረከች:: ልጇ ሊቆረጥ ነውና ፍርሀት ያዛት በሀሳቡም አልተስማማችም:: እያለቀሰች ፤ ልጁ ለሁለት ተከፍሎ ከሚጎዳብኝ እና ከሚሞት እርስዋ ትውሰድ ብላ ተናገረች:: በዚህ ንግግር የህፃኑ እውነተኛ እናትነት ተለየ::

ልክ እነደዚህ ጥበብን መላበስ እውነትን ማጥራት ይጠይቃል:: ለአቋራጭ መንገደኞች ልብን ከፍቶ ከመስጠት ይልቅ ለምን ብሎ መጠየቅ፤ዓላማቸው ጠንቅቆ መረዳት ያሻል:: አዎን የእኛ እውነት ለሌሎች ለመግለጥ የሚያስፈልገን ጥበብ ነው:: እዚያው እውነት ላይ ፀንቶ በመቆም የሚገኝ ዘላቂ የሆነን ድል ማጣጣም ነው ያለብን:: የዚህች ታላቅ አገር እውነት ላይ መፅናት፤ የዚህ ህዝብ በሀቅ ላይ መቆም ፈፅሞ ሳይለዝብ መቀጠል የሚኖርበት ወቅት ላይ ነን:: እውነታችን ተቀምተን የቆምንበት ሃቅ ተወስዶብን ዛሬ ተሸናፊ መስለን ልንታይ እንችል ይሆናል:: ነገር ግን እያደር እውነት ፀሀይ መሞቅዋ አይቀርም::

እርግጥ ነው፤ እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል:: በትዕግስት ውስጥ የሚገኝ ድል ይጥማል:: በጥረት የሚገኝ ስኬት ወደር የሌለው ነው:: እውነት ላይ ፀንቶ የቆመ የቆመለትን ዓላማ ሳያሳካ ቢያልፍ እንኳን በእውነት መዛግብት ውስጥ ጎልቶ ይወሳል:: የያዘው እውነት የቆመበት ሀቅ ውሎ አድሮ ሁሉም ይረዳውና ስለእውነት ብሎ በፈፀመው ታላቅ ተግባር ሲዘከር ይኖራል:: በተፈጥሮው ተሰባሪ የሆነው ሰው የማይሰበረውና ዘላለማዊ የሆነው እውነት ከራሱ በላይ ከፍ አድርጎ ማንገስ የሚገባው ለዚሁ ነው::

ወገን ለእራሳቸው እኩይ ዓላማ እኛ ያለንበት እውነት ሲያዛቡብን ስምን ዝም እንላለን:: እኛ ያለንበት እውነት ከመግለጥ ባለፈ ያላችሁት ውሸት ነውና አቁሙ፤ይልቁንም እውነትን ይዛችሁ መዋደዳችንን አብስሩልን አንድነታችን የሚያጠነክር መተሳሰራችን ከፍ የሚያደርግ ስራ ስሩልን ማለት ይኖርብናል::

እውነት የሚያዘቡትን ተው ብለንና አስቁመን እኛም እንደ ህዝብ እውነት ላይ መቆም ያለብን ለዚህ ነው:: ምድር በሙሉ በሀሰት ትርክት ተገፍቶ እኛ ላይ ቢፈርድ ለእውነት እስከቆምንና እዚያ ላይ እስከፀናን ድረስ አሸናፊዎቹ እኛ ነን:: አበቃሁ፤ ቸር ያሰማን::

# ዓለም አቀፍ

## የአሜሪካ የተወካዮች ምክር ቤት የመሣሪያ ቁጥጥር ረቂቅ ደንቡን በአብላጫ ድምጽ አሳለፈ



አዲስ አበባ ፦ የአሜሪካ የተወካዮች ምክር ቤት "ልጆቻችንን ለመጠበቅ የወጣ ደንብ" በሚል የተዘጋጀውን ዝርዝር የመሣሪያ ቁጥጥር ረቂቅ ደንብ በአብልጫ ድምፅ አሳልፏል፡፡

በድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ አምሥት "ሪፐብሊካን" የቀረበውን ዝርዝር ደንብ ሲደግፉ ሁለት "ዴሞክራቶች" ደግሞ መቃወማቸውን ሲ ኤን ኤን ዘግቧል።

ይሁን እንጂ ረቂቅ ደንቡ ህግ ሆኖ ይጸድቅ ዘንድ በሴኔቱ ተቀባይነት ማግኘትና መፅደቅ ይኖርበታል።

ረቂቁ ሰዎች መሣሪያ መግዛት የሚችሉበትን ዕድሜ ከ18 ወደ 21 ከፍ እንዲል ይደነግጋል።

መሣሪያ እንዲገዛ ዕድሜው የሚፈቅድለት ማንኛውም ሰው ከ15 ተተኳሽ ጥይቶች በላይ የሚይዝ የጥይት መጋዘን መግዛት እንደማይችልም በወጣው ደንብ ተደንግጓል፡፡

ማንኛውም መሣሪያ የታጠቀ ሰው ቤተሰብ ፣ ፖሊስ እና ሌላ አካል ÷ ግለሰቡ የአዕምሮ መታወክ ደርሶበታል፣ ወይም ሌሎችን የመጉዳት አደገኛ አዝማሚያ ይስተዋልበታል ብለው ሲጠራጠሩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መሣሪያ የመጠቀም መብቱን እንዲነሳ የመጠየቅ መብት የሚፈቅደው ደንብ ህግ ሆኖ እንዲፀድቅ በቀጣይ ለውሳኔ እንደሚቀርብ ሲ ጂ ቲ ኤን ዘግቧል፡፡

በዚህ ዓመት ብቻ በአሜሪካ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሕይወት ከመሣሪያ ጋር በተያያዙ ግጭቶች መቀጠፉን መረጃዎች ያመላክታሉ።

## አሜሪካ የሰሜን ኮሪያን ውጥረት እያባባሰችው ነው ሲሉ ቻይና እና ሩሲያ ወቀሱ

አዲስ አበባ፡- ቻይና እና ሩሲያ ፒዮንግያንግ የምታደርገውን የሚሳኤል ሙከራ መቀጠሏን ተከትሎ አሜሪካ በሰሜን ኮሪያ ያለውን ውጥረት እያባባሰች ነው ሲሉ ወቅሰዋል።

ሰሜን ኮሪያ ባለፈው ወር የባለስቲክ ሚሳኤል ሙከራ ማድረጓን ተከትሎ በአሜሪካ ቀርቦ በተመድ ሊጣልባት የነበረውን ማዕቀብ ሁለቱ ሃገራት ድምጽን በድምጽ የመሻር መብታቸውን ተጠቅመው ውድቅ ማድረጋቸው ይታወሳል።

ሃገራቱ በሰሜን ኮሪያ ላይ ሊጣሉ የታቀዱ ተጨማሪ ማዕቀቦችን በመቃወም እንዲሁም በኮሪያ ልሳነ ምድር ያለውን ውጥረት ለማርገብ ብቸኛው አማራጭ ውይይት እንደሆነም በተደጋጋሚ ሲገልጹ ቆይተዋል።

ቤጂንግ እና ሞስኮ ትናንት በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ ዋሺንግተን በቀጠናው ውጥረት ቀስቅሳለች ሲሉ አውግዘዋል፡፡

ጉባዔው ቻይና እና ሩሲያ በተመድ የፀጥታው ምክር ቤት ባለፈው ወር በአሜሪካ በቀረበውና በሰሜን ኮሪያ ላይ እንዲጣል የታቀደውን ረቂቅ የውሳኔ ሃሳብ የተቃወሙበትን ምክንያት እንዲያብራሩ ለመጠየቅ ያለመ ነው።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የቻይና አምባሳደር ዣንግ ጁን በሰሜን ኮሪያ ላይ የተጣለውን ማዕቀብ እንዲቀንስ ጠይቀዋል፡፡





"አሜሪካ ማድረግ የምትችላቸው ብዙ ነገሮች አሉ" ያሉት አምባሳደሩ ፥ ለአብነትም ሰሜን ኮሪያ ላይ የተጣለውን ማዕቀብ በተወሰኑ አካባቢዎች ማቃለልና ዋሺንግተን ከደቡብ ኮሪያ ጋር የጋራ ወታደራዊ ልምምድ ማድረጓን ማቆም አለባትም ነው" ያሉት፡፡

አምባሳደሩ አክለውም ምንም ቅድመ ሁኔታ ሳይኖር ለውይይት ዝግጁ ስለመሆን ማውራት ብቻ ሳይሆን ወደ እርምጃ መግባት ቁልፉ ጉዳይ መሆኑን አስረድተዋል።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሩሲያ ምክትል አምባሳደር እና ኢቭስቲግኔቫ በበኩላቸው፥ በሰሜን ኮሪያ ላይ የተጣሉ ማዕቀቦች እንዲነሱ ጠይቀዋል።

ሰሜን ኮሪያ ተጨማሪ ሰብአዊ እርዳታ እንደሚያስፈልጋትና ምዕራባውያን ለተፈጠሩ ውጥረቶች እሷኑ መውቀሳቸውን ማቆም አለባቸውም ነው ያሉት፡፡

ሰሜን ኮሪያ ከፈረንጆቹ 2006 ጀምሮ በኒውክሌር እና ባለስቲክ ሚሳኤል ፕሮግራሞቿ ላይ ተመድ የጣለባትን ማዕቀብ ችላ በማለት በዚህ ዓመት ከ12 በላይ አህጉር አቋራጭ ተምዘግዛጊ ሚሳኤልን ጨምሮ የተለያዩ የጦር መሳሪያ ሙከራዎችን አድርጋለች።

ከ2017 በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ስምንት የአጭር ርቀት ባለስቲክ ሚሳኤል በምስራቃዊ የባህር ዳርቻዋ በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ሞክራለች።

የተባበሩት መንግስታት የጣለው ማዕቀብ ሰሜን ኮሪያ በጣም የሚያስፈልጋት ሰብዓዊ እርዳታ ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም ቢልም፥ የእርዳታ ድርጅቶች በንግድና የባንክ እንቅስቃሴዎች ላይ የተጣሉ ክልከላዎች በሚያደርጉት አቅርቦት ላይ እንቅፋት መፍጠሩን ገልጸዋል።

በተመድ የአሜሪካ ምክትል አምባሳደር ጄፍሪ ዴላውረንቲስ ከፒዮንግያንግ ጋር ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ውይይት እንፈልጋለን ማለታቸውን አር ቲ እና ፐረስ ቲቪ ዘግበዋል።

በተጨማሪም ቻይና እና ሩሲያ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በሰሜን ኮሪያ ላይ የተጣለውን ተጨማሪ ማዕቀብ በመቃወም "ገደብ የለሽ" ስትራቴጂያዊ አጋርነታቸውን ከዓለም አቀፍ ደህንነት በላይ ከፍ አድርገው ይሆን ወይ ሲሉም ጠይቀዋል።

ቤጂንግ እና ሞስኮ በየካቲት ወር ላይ "ገደብ የለሽ" አጋርነት ብለው ያወጁትንም ለዚህ በማሳያነት ጠቅሰዋል።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# ባለ ጉዳይ ፤ ያለ ጉዳይ!

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

የዛሬው መንደርደሪያ ታሪካችን እውነተኛ ገጠመኝ ነው ፡፡ በእርግጥ በየቀኑ የሚገጥም ገጠመኝ ስለሆነ እምብዛም እንደ ልዩ ገጠመኝ የሚወሰድ አይደለም፡፡ “የባለ ጉዳይ ቀን” ተብሎ በተመደበው እለት አንድ ባለሥልጣንን ለማግኘት ወረፋ ይዘው የተሰለፉት ባለጉዳዮች አግዳሚው ወንበር ላይ ተደርድረዋል፡፡ባለሥልጣኑ የእንትን ቀን በሚባል ቀን ምክንያት በባለጉዳዮች ቀን በአጠገባቸው ባለው አዳራሽ ውስጥ ናቸው ፡፡ ባለጉዳዮቹ እየጠበቁ ይመጣሉ የተባሉት ባለሥልጣንም ሳይመጡ ሰባት ሰዓት ደረሰ ፡፡ የአዳራሹ ስብሰባ አልቆ ባለሥልጣኑ እየተጣደፉ ወደ ቢሯቸው ገቡ ፡፡ ባለሥልጣኑም በወከባ የተወሰኑትን ጉዳዮች በግርድፉ አይተው፤ ባለጉዳዩን በአግባቡ ማናገር ሳይችሉ ቀርተው በችኮላ መንፈስ የምሣ ሰዓት ነው ብለው ሄዱ፡፡ ከሰዓት ይመለሱ ይሆናል ጠብቁ የተባሉት ባለጉዳዮች እስከ ዘጠኝ ሰዓት ጠበቁ፤ የዚህ ባለታሪክም ከእለቱ ዘጠኝ ሰዓት ሲል ቦታውን ለቀው ወደ ቤታቸው ሄዱ ፡፡

እኒህ ባለጉዳይ መኪናቸው ውስጥ ገብተው ወደ ቤታቸው እየሄዱ ይህን የመሰለ መጉላላት እንዳይኖር በቀላሉ መልስ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነገሮች እያሰቡ ነበር፡፡ የመጀመሪያው አማራጭ ዛሬ ባለሥልጣኑ አይችሉም በሌላ ቀን ተመለሱ የሚለው አንዱ ነው ፡፡ ሌላው እርሳቸው ባይኖሩ እርሳቸውን ተክቶ ችግሮችን ሊፈታ የሚችል ሰው መወከል መቻል ነው ፡፡ የውክልና አሰራር ጉዳይ ለማስፈጸም ብቻ በሆነበት ሀገር ውስጥ ሥራን በውክልና የማሰራት ልምድ አለመኖሩን አስተውለው የጎደለን ነገር ብዙ መሆኑን አሰቡ ፡፡ ሌላኛው ቀላል የባለጉዳይን መጉላላት ሊቀንስ የሚችለው አላስፈላጊ ስብሰባዎችን ማስወገድ ነው ፡፡ እያንዳንዱ ቀን “የእንትን ቀን” እያልን እናከብር ብንል ኑሯችን ሁሉ አዳራሽ ውስጥ ይሆናል ፡፡ አንድ ኃላፊነት ያለበት ግለሰብ ሁሉም መድረኮች ላይ መገኘት የለበትም ፡፡ ነገር ግን እጅግ በተመረጡ የስብሰባዎቹ ተጽእኖ የባለሥልጣኑ ወንበር የተሰጠውን ኃላፊነት ወደፊት የሚያራምድ በሆኑ ቦታዎች ላይ ብቻ መገናኘት ፡፡ ኃላፊነትን በሚመጥን ደረጃ ላይ የሆኑ መድረኮች ላይ መገኘት፡፡ ነገሮችን በክብደታቸው ቅደም ተከተልነት ግምት ማድረግ አለመቻል ትልቁ የሀገራችን አመራሮች ችግር እንደሆነም አሰበ ፡፡

ሁላችንም ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ያልተመለሰው ባለሥልጣንን ኮቴ ተከትለነው አብረን እንውጣ ፡፡ ግለሰቡ ምሳ በልቶ ከሰዓት በኋላ ምናልባት የመብራት ቤቱን ስልክ ክፍያ ሊከፍል አስቀድሞ ከቢሮ እንደወጣ እናስብ ፡፡ የመብራት ክፍያ ሊከፍል የሄደበት ቦታ ላይ እንደእርሱ ዘጠኝ ሰዓት የወጣ አገልግሎት ሰጪ ገጥሞት እየተጉላላ ይሆናል ፡፡ በዚህ ጊዜም ባለሥልጣኑ ስለ ሥራ ሰዓት አክብሮ የመስራት ችግርን ያነሳል፤ በእርግጠኝነት ስለ ደንበኞች አገልግሎትም ያነሳል፤ በእርግጠኝነት ደስ በማይል ስሜት ውስጥ መሆኑን የሚገልጽ አካላዊ እንቅስቃሴም ያደርግ ይሆናል ፡፡ መብራት ተቋርጦ ከሆነ ደግሞ ችግሩ አይጣል ነው፡፡ባለጉዳይ በመሆን ውስጥ ያለ ውጣ ውረድ፤ ባለጉዳዩ እርሱ በሌላ ባለጉዳይ ላይ የሚፈጽመው ውጣ ውረድ፡፡

በምናባችን አንድ ነገር ደግሞ እናስብ ባለጉዳይ ያለጉዳይ ሆኖ ተሰልፎ ሲውል ፡፡ ባለሥልጣኑን ለማናገር ከተሰለፉት መካከል ምንም ጉዳይ የሌለው ዝም ብሎ ባለሥልጣኑን ለማግኘት በማሰብ ብቻ የተሰለፈ ሰው ይኖር ይሆን? አይመስለኝም ፡፡ እንደው አለ ብለን እናስብና ይህ ግለሰቡም ወደ ባለሥልጣኑ ቢሮ ገባ ፡፡ ከእዚያ ጉዳዩ ምን እንደሆነ ሲጠየቅ “አይ እንዲሁ ነው” ቢል፤ ወይንም “እርስዎን ሰላም ለማለት ነው” ቢል ወዘተ የሚፈጥረው ስሜት ምን ይሆን ፡፡ እያንዳንዱን ደቂቃ በጥንቃቄ ለሥራው ለሚጠቀም ሰው አጋጣሚው የሚያበሳጭ ሊሆንም ይችላል ፡፡

በህይወት ጉዞ ውስጥ ባለጉዳይ መሆን እና ያለ ጉዳይ መሆን ምን እንደሆነ እናነሳለን ፡፡ በዚህ ጽሁፍ ህይወትን ከጉዳዮቻችን ጋር እንመለከታለን ፡፡ በጉዳይ በተሞላ የሩጫ ዘመን ውስጥ ስንኖር ባለጉዳይነትም ሆነ ያለጉዳይነት ከሁላችንም የራቀ አይደለም ፡፡ በቅድሚያ ባለጉዳይ፤

### ባለጉዳይ

ጉዳይ የሌለው ሰው የለም፤ ሁሉም የየራሱ ጉዳይ አለው ፡፡ በአውቶብስ ውስጥ ያሉትን ሰዎች አቁመን ብንጠይቅ የሚሰጡን ምላሽ ይኖራቸዋል ፡፡ አንዳንዱ ወደ ትምህርት ቤት፤ አንዳንዱ ወደ ህክምና፤ ሌላው ወደ ገበያ ወዘተ ሁሉም ጉዳይ አለው ፡፡ በህይወት ጉዞ ውስጥ ወደ ምድር ስንመጣ የምናልፍበት ውጣ ውረዱ ውስጥ በሙሉ ጉዳይ አለ ፡፡ በጡረታ ጊዜም ሳይቀር ጉዳይ አለ፡፡ የትላንቱን በጥሞና መርምሮ ከትላንት የተማርነውን አጠገባችን ላሉት የማስተማር፤ የመምከር፤ ጤንነትን የመጠበቅ፤ መጽሐፍን የመጻፍ ወዘተ ፡፡

ጉዳይ ሁሉም ያለው መሆኑን ከተስማማን ባለጉዳዩን ከጉዳዩ ነጥለን በመምከር ወደ ዋናው ሃሳባችን እንግባ፡፡ አንባቢው ራሱን እንደ ባለጉዳይ ይመልከት፤ አንዳች ፋይዳ እንዳለው ፍጡር ፡፡ ከአንድ ጉዳይ ያለፈ አንዳች ነገር በህይወት ውስጥ ሊያከናውን የማይችል ሰው የለም፡፡ ሁሉም ሰው የየራሱ እምቅ አቅም ያለው፤ የየራሱ ቀለም፤ የየራሱ ውበት የለው ፍጡር ነው ፡፡

ራስን በጉዳይ ውስጥ ብቻ የመመልከት ችግር የብዙዎቻችን ችግር ነው ፡፡ ራስን ወደ መጥላት የሚያመጣ፤ ያሳኩትን ነገር በመቁጠር ውስጥ ለህይወት ትርጉም የመስጠት ችግር ፡፡ እኔ ስለ ምንድን ነው ያለሁት ብሎ ራስን ጠይቆ፤ ምላሹም አሉታዊ ሲሆን ራስን መጥላት ይከተላል ፡፡ ሰው በውስጡ ያሉትን እያንዳንዱን አካላቱ ቢመረምር እንዴት ግሩም ፍጥረት መሆኑን ይረዳል ፡፡ በአንጎል ውስጥ፤ በልባችን ውስጥ፤ በሆድ እቃችን ወዘተ ውስጥ ያሉት አካላት ጥምረትን ስናይ የሰው ልጅ እንዴት ባለ ውስብስብ አካላት እንደተደራጀ ስናይ እንገረማለን፤ በእርግጥም መገረምም ይኖርብናል ፡፡ ይህን ሰው ከጉዳዩ ለይተን ስናየው ታላቅነቱን እንመለከታለን ፡፡

ስኬትን በአከናወነው ነገር ውስጥ ለማየት የምናደርገው ሂደት የራሳችንን አቅም አስቀድመን አይተን በትክክለኛው መንገድ ውስጥ እንዳንሆን አድርጎናል ፡፡ ከጉዳይ ያለፈን ህይወት ለመኖር የራእይ ህይወት አስፈላጊ ነው፤ የትልቅ መስል ህይወት ፡፡

### የራዕይ ህይወት፤ የትልቅ ምስል ህይወት

ህይወትን በጉዳይ ውስጥ ከማየት፤ ህይወትን በራዕይ ውስጥ ማየት እጅግ ይለያል ፡፡ በነገ ውስጥ ራሳችንን የምናይበትን ቦታ ዛሬ ላይ መቅረጽ መቻል በጉዳይ ውስጥ ተውጠን ጉዳይ ገድለን ጉዳይ እየተካን ከመኖር በእጅጉ ይለያል ፡፡ በተስፋ ውስጥ የሚኖር ሰው እያየው የሚራመደው፤ ከውስጡ እየሰማው የሚኖርለት፤ ከጉዳይ ስብስብ ከፍ ያለ እይታ ያስፈልገዋል፡፡ እያየ የሚራመደውን ነገር አለማግኘት ማለት የእለት ጉዳይን ከየአቅጣጫው ተቀብሎ ለማስፈጸም በመባከን መኖር ተደርጎም ሊወሰድ ይችላል፡፡ በነገው ተስፋ ቆርጦ በዛሬው አኩርፎ እንዲሁ በዛሬ ውስጥ የመኖር ግራ የመጋባት ህይወት ፡፡

አንባቢ ሆይ ራስህን በነገ ውስጥ እንዴት በትልቅ ምስል ውስጥ ታያለህ? በሥራ የት ደረስህ? በትዳር ህይወትህ የት ደርሰህ? በማህበራዊ አስተዋጾህ የት ደርሰህ? ከዛሬ የጉዳይ ስብስብ ከፍ ያለ ፡፡ በግልጽ መዳረሻችንን በትልም ምስል ውስጥ ዛሬ ላይ መመልከት መቻል ለህይወት ጉዞ ውጤታማነት ትልቁ ግብዓት ነው፡፡ እያንዳንዱን ቀን በውጤታማነት መጠቀም የሚያስችል ግብዓት ፡፡

በዙሪያህ ወዳሉት ልጆች ተመልከት፤ በእነርሱ ህይወት ውስጥ የምንመለከተው አንድ አስደናቂ ነገር አለ፤ እርሱም የራእይ ህይወታቸው ነው ፡፡በዙሪያቸው ካለው ነገር ተነስተው አሻግረው የፊታቸው ያሉትን ቀናት የሚመለከቱ ፡፡ ልጅ አባቱንና እናቱንእያየ አባትነትን ይመለከታል ፡፡ አባት ሲሆን ያለበትን ኃላፊነትም ይረዳል፡፡ በዙሪያው ያሉ ሰዎች ይዘውት ከሚመጡት የጉዳይ ክምር ይልቅ ነገን አሻግሮ የሚመለከትበትን መነጽር ያገኛል ፡፡ ጉዳይን ሊያስፈጽም ሲንቀሳቀስ የሚገኘው በትልቁ ምስል ውስጥ ይሆናል ፡፡ ትልቁን ምስሉን ህዝብን በአግባቡ ማገልገል ብሎ ያሰበ ባለጉዳይን አጉላልቶ በሥራ ሰዓት ጉዳይ ከማስፈጸም ይልቅ እያንዳንዱን ደቂቃ በጥንቃቄ በመጠቀም ምሳሌ ይሆናል ፡፡

በዙሪያህ ያሉትን ልጆች ስትመለከታቸው የተስፋ መቁረጥ ህይወት አታስተውልባቸውም ፡፡ ምክንያቱም ተስፈኞች ስለሆኑ ፡፡ በነገውስጥ ብዙ ነገሮችን የሚያዩ ተስፈኞች ፡፡ ነገን ሲያዩ ጭንቀት አያድርባቸውም፤ ነገርግን ወዳልደረሰቡት ለመድረስ የሚመጡ የእድል ቀናት ሆነው ከመረዳት ውጭ አማራጭ የሌላቸው፤ በጥቃቅን ጉዳዮች ተይዘው የማይውሉ፤ አሁን ያስለቀሳቸውን ከአፍታ በኋላ የሚረሱ ፡፡ ከልጅነት እድሜ ተወጥቶ ወደ ኃላፊነት እድሜ ሲደረስ አዲስ ነገን የማየት አቅም እየደበዘዘ ይሄዳል፤ ትልቅ ምስል የመመልከት አቅምም እንዲሁ ፡፡ ምክንያቱም በተፈጥሮ በነገውስጥ እንድናይ የተሰጠን እያለቀ ሁሉንም ነገር ላይ ደርሰን ከእዚያስ ለሚለው ጥያቄ ምላሽ መስጠት የሚሳነን ስለሚሆን ፡፡ እዚህ ጋር ተፈጥሮ በእድሜ ውስጥ በነገውስጥ ከምትሰጠን ራእይ ባሻገር ራእይ መፍጠር እንዳለብን መረዳት የሚኖርብን ፡፡ የሁለተኛ ክፍል ተማሪ ወደ ሦስተኛ ክፍል ውስጥ በመግባት ውስጥ ስላለው ተስፋ እያየ እንድንሄድ ከሚያደርገን ተስፋ ባሻገር ተስፍን በራዕይ ውስጥ በመፍጠር በጥቃቅን ነገሮች ሰዎች ከመጎተት እንዲሁም ተስፋ ውስጥ ማግኘት ይገባናል ፡፡ እርሱም የራእይ ህይወት ነው ፡፡

### የራዕይ ህይወት፤ የተስፋ ህይወት

ከጉዳይ በላይ የሆንክ ሰው መሆንህ ትርጉም የሚኖረው በራዕይ ውስጥ ነው ፡፡ በራዕይ ውስጥ ለራስህ ቦታ መስጠት ስላለ ፡፡ ራእይ በአንድ ሰው ህይወት ውስጥ ያለውን ሃይል ለመረዳት እንድንችል የሚባክን ሰዓት አያስፈልገንም ፡፡ ራዕይ ሃይል አለው፤ ተስፋን ለመፍጠር የሚሆን ግብዓት ፡፡ ዛሬ የምንፈተንበት የኑሮ ውድነቱ አንድን ነገር አቅዶ ለመጀመር የሚሆን ምልከታን አይሰጥም ፡፡ በሰዎች መካከል መተማመን አለመኖር ደግሞ ከኑሮ ባሻገር ማህበራዊ መስተጋብራችንን አደጋ ውስጥ ጥሎታል ፡፡ በሰዎች የተጎዱ ሰዎች በፍጹም ነጋቸው ውስጥ ብርሃንን ሳይሆን ጭልምተኝነትን ቢያዩ ልንፈርድባቸው አንችልም፤ የተስፋ ጉዞቸው ቢጨልምም እንዲሁ ፡፡ በነገ ውስጥ ተስፋን ማየት እንድንችል ዛሬ ልንሰራ የሚገባንን እንስራ ከተባለ ግን ተጽእኖዎችን በሙሉ አልፎ ወደ ፍጻሜው እንዲመጣ የምንተጋለት ራዕይ ያስፈልገናል፤ ጥሩ ባለጉዳይ የሚያደርግ፤ ከጉዳይ በላይ የሚያኖር ፡፡ ለሥራ ህይወታችን የሰጠነው ራዕይ ይህን ያህል ሰው ተመርቆ ሥራ ማግኘት አልቻለም ብለን በጨለማ ውስጥ ከማስቀመጥ እኔ እንዲህና እንዲያ አይነት ሥራ የሚሰራ ሰው እሆናለሁ ብሎ ለእርሱ የሚያስፈልገውን ትጋት በማድረግ ወደ ህልማችን ለመቅረብ በእያንዳንዱ ሰከንድ መጠጋት ያስፈልጋል፡፡ ባለራዕዮች ልዩነታቸው ከጨለማው አሻግሮ ማየት የሚችሉ መሆናቸው ነውና፡፡ ራዕይን ተከትሎ የተግባር ሰውነት አስፈላጊ ነው ፡፡ እርሱም ለመማርና ለመተግበር ዝግጁ በመሆን ውስጥ የሚገለጽ ፡፡

### ያለጉዳይ መሆን፤ የጥፋት መንገድ

በመነሻታሪካችን ውስጥ ያለጉዳይ ስለመሆን አንስተን ነበር ፡፡ ባለሥልጣን ቢሮ ጉዳይ ሳይኖረው የገባን ሰው በማሰብ ፡፡ በህይወት ውስጥም ጉዳይ መሰናከያ እንደሚሆን፤ ያለ ጉዳይ መሆንም እንዲሁ ወደ ጥፋት መንገድ ይመራል ፡፡ ሰዎች አዎንታዊ አስተሳሰብ ኖሯቸው ጥሩ የሚባል ሥራ እንደሚሰሩ ሁሉ ለምንም ነገር ደንታ ቢስ በሆነ ህይወት ውስጥም በማለፍ ጥፋትን ሊያመጡም ይችላሉ ፡፡ ጥፋት ሆን ተብሎ እንዲሁም ሳይታሰብበት ሊሆን ይችላል ፡፡

አንዳንድ ሰው በዘመኑ ሁሉ ሰርቶ የሚያልፈው ጥቂት ነገር ሊሆን ይችላል፤ ዋናው ጉዳይ ጥቂትም ሆነ ብዙ መሆኑ አይደለም ነገርግን ሊሆን የተገባውን ሆኖ ማለፉ እንጂ ፡፡ ያለጉዳይ መሆን ፈጽሞ የማይቻል ቢሆንም የምንኖርለት ዓላማን ሳይዙ መኖር ግን በህይወት ውስጥ ያጋጥማል ፡፡ እናት ስለ ልጇቿ፤ ወንድምና እህት እንደ ወንድምና እህትነታቸው፤ አሠሪ ለሠራተኛው ወዘተ የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ትርጉሙ ብዙ ነው ፡፡ ይህ ትርጉም ፍሬ የሚኖረው ኑሯችን ውስጥ ዓላማ በሚይዘው ቦታ ነው ፡፡ አባት ልጆችን ወልዶ አስቀምጦ በልጆቹ ላይ ዓላማ ከሌለው የሚሰጠውን ትርጉም ማሰብ ከባድ ነው ፡፡



አንባቢ ሆይ፤ በጉዳይህ እስረኛ ሆነህ ለራስህ ቦታን ከመስጠት አትቆጠብ እንዲሁም ጉዳይ የሌለህ ሆነህ እንዲሁ የምትኖርም አትሁን ፡፡ ታላቁ ቀመር የሚዛን ቀመር ነው፤ ሚዛኑም በወርቃማው ህግ ውስጥ የሚገለጽ ፡፡ የዓላማ ኑሮ ማጠቃለያው በአጠገባችን ካለው ሰው ጀምሮ ለ ሰው ትርጉም ያለው ሰው መሆን፡፡ የእሴት ህይወት ፡፡

### እሴታችንን መለየት መቻል

እያንዳንዳችን እንዲኖረን የምንፈልገው ከሌላው መቀበል የምንፈልገው አለ፤ እኛም መስጠት የሚጠበቅብን፤ የእሴት ህይወት ፡፡ በጉዳዮች መካከል ተውጠን እንዳንጠፋ፤ የህይወት ጉዞም ከዓላማ መስመር ውጭ እንዳይሆንብን የሚያደርግ ፡፡ ከትላንት ወደዛሬ የመጣ በውስጣችን እውቅና የሰጠነው እሴት አለ ፡፡ ተቋማት ራዕያቸውን ለማሳካት የሚረዳቸውን እሴት ዘርዝረው ይፋ ያደርጋሉ ፡፡ በግል ህይወታችን ውስጥ የራሳችን ያልናቸውን እሴቶች እንዲሁ ሊዘረዘሩ የሚችሉ ሆነው እናገኛቸዋለን ፡፡ ቆጥረን የምናውቃቸው፤ በየቀኑ እየጨመርን ሄደን የጥንካሬያችን አካል የምናደርጋቸው ጥንካሬያችንን ስንቆጥር የምናገኛቸው ፡፡

### የባለጉዳዩ ጥንካሬ

ማጠቃለያችን ጉዳይ የሌለው ሰው የለም፤ አንተም አለህ፤ በትልቅ ዓላማ ውስጥ የሚኖር ባለ ጉዳይነት ፡፡ በእሴት ውስጥ በተገነባ ጥንካሬ ውስጥ ወደ ፍጻሜው የሚደርስ ፡፡ ጥንካሬን በማወቅ የሚያስፈልግም ጥንካሬም አለ ፡፡ ባለጉዳዩ ጥንካሬውን አለማወቅ የህይወትን አቅጣጫ ድንግዝግዝ ውስጥ ከሚጨምሩት ነገሮች መካከል ዋናው ነው ፡፡ መፍትሔው ደግሞ ጥንካሬን ማወቅ ፡፡

ጥንካሬ ሌላ ጥንካሬን የሚወልድ ሆኖ ሥራ ላይ ሲውል ወደ ውጤት የሚያመራ ነው፤ ውጤቱም ባለጉዳይን የማያጉላላ ፡፡ እያንዳንዱ ሰው የራሱን ጥንካሬ ከማየት ምናልባትም የሌሎችን የማየት አቅም ሊኖረው ይችላል ፡፡ በመሆኑም ሌሎች ስለጥንካሬያችን እንዲሁም ድክመታችን የሚነግሩንን በጥሞና ማድመጥ በትልቅ ምስል ውስጥ ወደ ፍሬ መድረስ እንችላለን ፡፡

በህይወት ጉዞ ውስጥ በድንግዝግዝ እየተራመድክ እንደሆነ ካሰብክ ዛሬ ቆመህ ለራስህ ምላሽ ስጥ፤ ምላሹም ጥንካሬህን በማወቅ ውስጥ በዓላማ መኖር ይሁን ፡፡ ሆነን ማለፍ የምንፈልገውን ማድረግ የምንችል መሆናችን የሚወሰነው በጥንካሬያችን ውስጥ በእሴት ነው ፡፡ አንድ ሰው ሁሉንም ነገሮች መሆን ባይችልም አንዳች በልዩነት ሊያደርገው የሚችለው ነገር መኖሩን ግን መረዳት አለበት፡፡ ስለሆነም ለራስ ቦታ እንስጥ፤ ከምንሰራው ሥራ ውጭ የሚሆን ቦታ መስጠት ፡፡ ባለጉዳይ መሆን፤ ነገርግን ከባለጉዳይነት በላይ ለራስ ቦታ የሰጠ ፡፡ በጥቃቅን ጉዳይ የማይያዝ፤ ትልቅ ምስል ያለው ፡፡ የህይወት ባለጉዳይነት!

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የካበተ ልምድ፣ እወቅትና ፍላጎት ያስገኙት ከፍታ

ፍሬሕይወት አወቀ



አቶ ደረጄ እያሱ



ድርጅቱ ለ 52 ሠራተኞች የሥራ ዕድል ከፍቷል

የማስታወቂያ ሥራዎች አዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ በክልል ከተሞች ሳይቀር የከተሞችን ገጽታ በማበላሸት እንዲሁም በማቆሸሸ ስማቸው በእጅጉ ይነሳል። ማስታወቂያዎቹ ወቅት ሲያልፍባቸው የሚያስወግዳቸው ካለመኖሩና በሥርዓት የሚመሩ ካለመሆናቸው ጋር ተያይዞ ከትንሹ ማስታወቂያ አንስቶ እስከ ትላልቆቹ ቢልቦርዶች ድረስ የከተሞች ችግሮች መሆናቸው አይካድም። ይህ ሁሉ ችግር የሚያመለክተው ማስታወቂያውን የሚመራ አካል በሚገባ ኃላፊነቱን አለመወጣቱን ብቻ አይደለም፤ የማስታወቂያ ስራ እየዘመነ አለመሄዱም ጭምር ነው።

የማስታወቂያ ሥራ አሁን አሁን እየዘመነ መጥቷል፤ ምስጋና ለኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ በርካታ ማስታወቂያዎች በማኅበራዊ ድረ ገጾችና በመሳሰሉት ለፈላጊዎቻቸው እንዲደርሱ እየተደረገ ነው። ይህም ማስታወቂያዎች በቆየው አሠራር በየቦታው ቢለጠፉ በከተሞች ላይ ሊደርስ የሚችለውን መቆሸሽ እያስቀረው ነው። ቢልቦርዶችና የመሳሰሉትም ዘመኑ በወለደው ቴክኖሎጂ ተውበው የሚቀርቡ እንደመሆናቸው የከተማም ውበት መሆን እየቻሉ ናቸው።

አሁንም ቢሆን በአገሪቱ የማስታወቂያና የሕትመት ሥራ ገና ብዙ ያልተሰራበት ዘርፍ መሆኑን በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ። በዛሬው የስኬት ገጻችንም በማስታወቂያና የሕትመት ሥራ እንግዳ ይዞ ቀርቧል። አቶ ደረጄ እያሱ ይባላሉ። የስካይ ማተሚያ ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ ናቸው።

አቶ ደረጄ በትምህርት ዝግጅታቸው በኢኮኖሚክስ ትምህርትን የተማሩ ሲሆን በማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ለስምንት ዓመታት ሠርተዋል። አቶ ደረጄ በመንግሥት ሥራ የሚያገኙት የወር ደመወዝ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን በማስተዳደር ረጅም ርቀት ሊያስኬድ እንደማይችል በማመን ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችን ለመሥራት ይወጥናሉ። ራሳቸውን ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር ማዋሀድን ‹‹ሀ›› ብለው በመጀመር ወደ ግል ሥራ ያመራሉ።

የቴክኖሎጂውን ዕውቀት በተለያዩ አጫጭር ኮርሶች በማዳበር በቀጥታ ወደ ኮምፒዩተር ጥገና አገልግሎት ያመሩት አቶ ደረጄ፤ የማስታወቂያና የሕትመት ሥራውም በዚህ ወቅት የተወለደ ስለመሆኑ ነው የሚያስታውሱት። የኮምፒውተር ጥገና ሥራውን ዘር በማድረግ ተረግዞ የተወለደው የማስታወቂያና ሕትመት ሥራ ዛሬ 13 ዓመታትን አስቆጥሯል።

ጠንካራ የሥራ ባህልን ባህሪያቸው ማድረግ በመቻላቸው የግላቸውን ሥራ ለመሥራት መንገድ ጠረገላቸው። ለሥራ ያላቸው ፍላጎትና ፍቅር ለአዲሱ ሥራቸው ትልቅ አቅም ሆናቸው። ከኮምፒውተር ጥገናው በተጨማሪ አንዳንድ የዲዛይን ሥራዎችን በመሥራት ዘርፉን ለማስፋት መውተርተር ጀመሩ።

የመንግሥት ሥራቸውን በመልቀቅ ወደ ግል ሥራ የገቡት አቶ ደረጄ፤ ባለቤታቸውን ይዘው ወደ ሥራው ገቡ፤ አቶ ደረጄ ሥራውን ተፍ ተፍ ብለው ከበር ሲያደርሱት ባለቤታቸው ወይዘሮ ሰናይት ደግሞ የመጣውን ሥራ ሙያቸውን ተጠቅመው ደንበኞቻቸው በሚፈልጉት መልኩ የዲዛይን ሥራውን ያቀላጥፉትና ወደ ሌሎች ማተሚያ ቤት በመውሰድ አሳትመው ለደንበኞቻቸው ማቅረቡን ተያያዙት። እንዲህ እንዲህ እያለ የተጀመረው የማስታወቂያና የሕትመትና ሥራ መሠረት እየያዘ ከእድገት ጉዞው ሊያጨናግፈው የቻለ የለም።

ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ እንዲሉ ለዛሬው የስኬት ጉዞ ባለቤታቸው ወይዘሮ ሠናይት ዓለሙ የነበራቸው ሚና ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዝ አሁንም በብርቱ የሚተጋገዙ ጥንዶች ስለመሆናቸው አቶ ደረጄ ተናግረው አይጠግቡም።

ይህን ሁሉ አርገው አቶ ደረጄ አልረኩም፤ በኮምፒዩተር የሠሯቸውን ዲዛይኖች ደንበኞቻቸው ወደ ማተሚያ ቤት በመውሰድ ሲያሳትሙ ያስተውላሉ፤ በዚህም ሥራው ቅብብሎሽ ያለው መሆኑን አረጋገጡ። ይሄኔ አንድ ሀሳብ የአዕምሯቸውን ጓዳ ደጋግሞ አንኳኳ፤ ለጥሪው ምላሽ ለመስጠት ሳያመነቱ ማተሚያ ቤት መክፈት እንዳለባቸውና ዲዛይኖቻቸውን በራሳቸው ማተሚያ ቤት ማሳተም እንደሚችሉ ለራሳቸው ቃል ገቡ፤ አቅማቸው አሟጠው በመጠቀም ሀዋሳ ከተማ ላይ ስካይ ማተሚያ ቤትን አቋቋሙ።

በዘርፉ ያላቸውን ዕውቀትና ከፍተኛ ፍላጎታቸውን መሠረት በማድረግ ሁለት ሆነው የጀመሩት የማተሚያ ቤት ሥራ መነሻ ካፒታሉ ስድስት መቶ ብር ብቻ ነበር። ስድስት መቶ ብሩም ቢሆን አንድ ወንበርና አንድ ጠረጴዛ ተገዝቶበት በ150 ብር የቤት ኪራይ ነው ወደ ሥራው የተገባ።

ወቅቱ ለዘርፉ የሚመጥን የተሻለ ቁሳቁስና ገንዘብ ይዘው ነገር ግን ገበያውን መፍጠር ያልቻሉ በርካቶች የነበሩበት መሆኑን ያስታወሱት አቶ ደረጄ፤ እርሳቸው ግን በወቅቱ ካፒታሉ ሳይኖራቸው በዘርፉ ያላቸውን የካበተ ልምድና ዕውቀት እንዲሁም ከፍተኛ ፍላጎትን መሠረት በማድረግ በገበያው ውስጥ ያለውን ክፍተት ለመድፈን ታትረዋል። ወደ ሥራው ሲገቡ ምቹ ሁኔታዎች አልነበሩም። ይሁንና በሚሰጡት ጥራት ያለው አገልግሎት፣ ትዕግስትና ቁርጠኝነት ሁሉንም ፈተናዎች ማለፍ ችለዋል።

በአሁኑ ወቅትም ከ150 ብር ኪራይ ቤት ወጥተው በሀዋሳ ከተማ 500 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ማተሚያ ቤት ማቋቋም ችለዋል። ከማስታወቂያና የሕትመት ሥራቸው ጎን ለጎን የታሸገ ውሃ የማከፋፈል ሥራም ይሠራሉ። ለዚሁ ሥራቸውም ከማተሚያ ቤታቸው አጠገብ 500 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ መጋዘን ገንብተዋል።

አሁን በማስታወቂያ የሥራ ክፍላቸው ዘመኑ የዋጃቸውን ማሽኖች ጨምሮ አጠቃላይ ከሰባት የሚበልጡ ማሽኖች አሉ። ከእነዚህ ማሽኖች መካከልም በዋናነት የቢል ቦርድና የስቲከር ማስታወቂያዎችን ጨምሮ የቲሸርት ሕትመቶች፣ የሌዘር፣ የጣውላ፣ የማይካ እንዲሁም በኤምዲኤፍ የሚሠሩ የተለያዩ የማስታወቂያው ሥራዎች ማሽኖች ይገኙበታል። ኤምዲኤፍና ጣውላን በመጠቀም ሲኤንሲ በተባለው ማሽን የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችንና ፊደላትን በመቅረጽ ቲሸርቶች፣ ኮፍያ፣ ብርጭቆና የተለያዩ የስጦታ ዕቃዎችን የማስታወቂያ ክፍሉ ያመርታል።

በሕትመቱ ዘርፍም ከጀርመን አገር ከቀረጥ ነጻ ባስገቧቸው ዘመናዊ የወረቀት ማሽኖች በመጠቀም የተለያዩ የወረቀት፣ የጋዜጣና የመጽሔት ሥራዎችን ማተሚያ ቤቱ ይሠራል። በተለይም የሠርግ፣ የልደት ካርዶችን ጨምሮ በመጽሔት ዘርፉ የምርቃትና ሌሎች መጽሔቶችን እንዲሁም የተለያዩ የልቦለድ መጽሐፍቶችንና የዩኒቨርሲቲ ጥናታዊ ጽሑፎችንም ያትማል።

በማስታወቂያ ሥራቸው ትምህርት ሰጪ ቢልቦርዶች፣ የሙዚቃ ኮንሰርቶችና እንደ ቴሌኮሙኒኬሽን አይነት ወቅታዊ ማስታወቂያዎችን በተለያየ ቦታ ይተክላሉ። ከዚህ በተጨማሪም የትራፊክ ምልክት መብራቶችን ይሠራሉ።

የሥራ መነሻቸውና የማምረቻ ፋብሪካቸው ሀዋሳ ከተማ ላይ ቢሆንም፣ አዲስ አበባ ላይም ሰፊ ገበያና ፍላጎት ያለ በመሆኑ ቅርንጫፍ በመክፈት ጥሩ ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ። ከቻይና በሚገቡ በሶላር የሚሰሩና ኤልዲዎችን በመጠቀም የተለያዩ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ምልክቶችን ለአብነትም የፍጥነት ምልክቶችን በአዲስ አበባ ከተማ በአራቱም አቅጣጫ ይሠራሉ። በማይካ ሥራ የጠረጴዛ ምልክቶችን ጭምር ያመርታሉ።

አዲስ አበባ ላይ በሚሠሩት ሥራ በአብዛኛው አጀንዳ፣ ካላንደር መጽሔትና የተለያዩ ካርዶች ጭምር ወደ ውጭ አገር ተልከው ሲሠሩ መታዘብ የቻሉት አቶ ደረጄ፤ ይህን ለማስቀረትና በአገር ውስጥ ጥራት ያለውን ማንኛውንም የሕትመት ሥራ ለመሥራት ተዘጋጅተዋል። ይህ ሳይሆን የቀረበት ዋናው ምክንያት በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይልና ዘመኑን የዋጁ መሣሪያዎች ባለመኖራቸው እንደሆነ በመረዳታቸው ይህን ክፍተት ለመሙላት ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን አቶ ደረጄ ይጠቅሳሉ።

ጥራት ያለው የማስታወቂያና የሕትመት ሥራ ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው አቶ ደረጄ፤ በመፈለግ ብቻ የተወሰኑ አይደሉም፤ በግላቸው በተለያዩ አገራት ተዘዋውረው ልምድ ለመቅሰም ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ተዘዋውረው የልምድና የዕውቀት ሽግግር ካደረጉባቸው አገራት መካከልም ጃፓን፣ ቻይና፣ ሕንድና ዱባይ በመሄድ ከዘርፉ ጋር የተያያዙ ባዛሮች ላይ ተሳትፈዋል። በቀጣይም በእነዚህ አገራት ላይ የተመለከቷቸውን ዘመናዊና የረቀቁ ማሽኖችን ወደ አገራቸው በማምጣት የማስታወቂያና የሕትመት ሥራውን ለማዘመን አቅደዋል።

ለማስታወቂያና ሕትመት ሥራ የሚያገለግሉት አብዛኞቹ ግብዓቶች ውጭ ቀመስ እንደሆኑ የጠቀሱት አቶ ደረጄ፤ በአሁኑ ወቅት ጥሬ ዕቃውን በቀላሉ ለማግኘት ከፍተኛ ችግር እንደሆነም ነው የሚናገሩት። ይህ መሆኑም በደንበኞች ላይ ዋጋው እንዲጨምር አድርጓል ይላሉ። ‹‹ሰፊ የሰው ኃይል፣ የሥራ ፍላጎትና የምርት ተፈላጊነት በአገሪቱ አለ። ዋናው ደግሞ ፍላጎት ነውና ዘርፉ ገና ያልተሠራበት እንደመሆኑ ብዙ መሥራት ይቻላል ይላሉ።

በአሁኑ ወቅት በባነር የሚሠሩት የማስታወቂያ ሥራዎች ቀርተው በስክሪን የሚሠሩ የማስታወቂያ ሥራዎች ተተክተዋል። ስለዚህ ይህንኑ የኤል ዲ እና የኤች ዲ የማስታወቂያ ሥራዎች በስፋትና በጥራት በመሥራት የማስታወቂያውን ሥራ ማዘመን የግድ ነው የሚሉት አቶ ደረጄ፤ በተለይም የከተማን ውበት በመጠበቅ ዘመናዊ የማስታወቂያ ሥራዎቹ የጎላ ድርሻ አላቸው ይላሉ።

በባነርና በተለያዩ ወረቀቶች የሚሰቀሉ ማስታወቂያዎች ከተሞችን በማቆሸሽ ውበታቸውን እንደሚያጠፉ ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት ግን በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚሰቀሉ የማስታወቂያ ስክሪኖች ለከተሞች ውበት መሆን እንደቻሉ ይናገራሉ። ማስታወቂያዎች የከተሞችን ውበት መጠበቅ እንዳለባቸው አስገንዝበው፣ባለቤት ሊኖራቸው ይገባልም ብለዋል።

አቶ ደረጄ ለሥራው ካላቸው ቅርበት፣ ዕውቀትና ፍላጎት የተነሳ ሥራውን ማስፋት ችለዋል፤ ለዜጎችም የሥራ እድሎችን አስገኝተዋል። በአሁኑ ወቅት ለ52 ሰዎች በቋሚነት የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል። ሥራው ሁሌም የሚሠራና በተለያዩ ወቅቶች ደግሞ ሰፊ የሰው ኃይል የሚፈልግ መሆኑን ተናግረው፣ ይህ ሲሆን ከ100 እስከ 200 ሰዎችን በኮንትራት እንደሚያሠሩም ያብራራሉ።

አብዛኛው የማስታወቂያና የሕትመት ሥራ ሙያዊ ዕውቀት የሚፈልግ እንዳልሆነም ነው የሚናገሩት። ብዛት ያላቸውን ሠራተኞች የሚቀጥሩት ከጎዳና ተዳዳሪዎች እንደሆነም አጫውተውናል። ፍላጎት ላላቸው የጎዳና ልጆች ቅድሚያ በመስጠት ቀለል ባለ ስልጠና ወደ ሥራ እንዲገቡ ያደርጋሉ። በተለይም በአካባቢያቸው ለሚገኙ የጎዳና ልጆች ይህን የሥራ ዕድል በማመቻቸት ከመደበኛው ክፍያ በተሻለ ክፍያ በማሠራት ገቢ ማግኘት እንዲችሉ እያደረጉ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ለአካል ጉዳተኞችም ስልጠና ሰጥተው ወደ ሥራ እንደሚያሠማሯቸው ተናግረው፣ ከ52 ቋሚ ሠራተኞቻቸው መካከልም አብዛኞቹ የአካል ጉዳት ያለባቸው መሆናቸውንም ይጠቁማሉ። በቀጣይም ቢሆን የአካል ጉዳት ላለባቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች በራቸው ክፍት መሆኑን ነው አቶ ደረጄ ያመለከቱት።

በዘርፉ የሚሰጥ ስልጠና ባለመኖሩ ባለሙያዎችን ለማግኘት ችግር መሆኑን ጠቅሰው፣ የሚገኙዋቸው ሠራተኞች መደበኛ ባልሆነ ስልጠና የሰለጠኑና በልምድ የሚሠሩ መሆናቸውን ይገልጻሉ። አቶ ደረጄ በስካይ ማተሚያ ድርጅት ውስጥ ለሠራተኞች ስልጠና በመስጠት ባሰለጠኗቸው ሙያተኞች ሥራውን ለመሥራት አቅደዋል። የጎዳና ልጆችንና አካል ጉዳተኞችን ወደ ሥራ ከማሠማራት በተጨማሪ ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻር በተለይም የሀዋሳ ከተማ ገጽታን ማጉላትና አረጋውያንን በመርዳት ተሳትፎ ያደርጋሉ።

ለ13 ዓመታት በዘርፉ የቆየው ስካይ የማስታወቂያና የሕትመት ሥራ በጣም ትንሽ በተባለው ሲልክ ስክሪን ወጥሮ በቀለም ከማተም ተነስቶ፣ በአሁኑ ወቅት ቲሸርትን በዲጂታል ሕትመት እስከ ማምረት ደርሷል። በማስታወቂያው ዘርፍም እንዲሁ በቀለም ቀርጸው ታቤላ ላይ ይሠሩት የነበረው ሥራ በዘመናዊ መንገድ በዲጂታል ቀይረው እየሠሩ ናቸው፤ በአሁኑ ወቅት የድርጅቱ ካፒታል አስር ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር ደርሷል።

ዘመኑ የውድድር እንደመሆኑ ሥራን በተሻለ ጥራት ሠርቶ ደንበኞችን ማስደሰት የግድ ስለመሆኑ ያነሱት አቶ ደረጄ፤ ድርጅታቸው ‹‹ደንበኛህን ለማስደሰት ሠራተኛህን ተንከባከብ›› በሚል መርሕ የሚመራ እንደሆነም አጫውተውናል። ታድያ ሠራተኞቻቸውን ከማስደሰት ባለፈ ጤናማና ቤተሰባዊ የሆነ ግንኙነት ያላቸው አቶ ደረጄ፤ ይህም ለሥራቸው ስኬት ወሳኝ ሆኖ ያገኙት እንደሆነ አጫውተውናል። በቀጣይም የተሠማሩበትን የማስታወቂያና የሕትመት ዘርፍ በማሳደግ በውጭ አገር የሚታተሙትን የሕትመት ውጤቶች በአገር ውስጥ በማተም ለዘርፉ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ማስቀረትን ዓላማ አድርገው ይሠራሉ። እኛም እቅዳቸው እንዲሰምር በመመኘት አበቃን።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

# የመንገድ ግንባታው ዘርፍ ተስፋና ተግዳሮት

መላኩ ኤርሴ

የመንገድ መሰረተ ልማት እንደ ስሙ ለሁሉም ልማቶች መሰረት የሆነ ዘርፍ ነው:: ድህነትን ለመቀነስ፣ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት እንዲሁም ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማስፋፋትና ህዝቡን ተደራሽ ለማድረግ የመንገድ መሰረተ ልማት እጅግ አስፈላጊ ነው:: ከተሞችን ከምርት አካባቢዎች፣ የግብርና አካባቢዎችን ደግሞ ከገበያ ስፍራዎች ጋር በማገናኘት የአርሶ አደሩንም ሆነ የከተማ ነዋሪውን የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መንገድ ወሳኝ ነው:: ይህ ዘርፍ ለሁሉም ዘርፎች መሰረት እንደመሆኑ ዘርፉን ለማልማት ከፍተኛ ሀብት ይፈልጋል::

ለዚህም ነው ኢትዮጵያ ለዚህ ዘርፍ ከፍተኛ ሀብት በመመደብ የመንገድ መሰረተ ልማትን ለማስፋፋት በትኩረት ስትሰራ ነው የቆየችው:: ባለፉት ጥቂት አስርት ዓመታት ውስጥ በዘርፉ በተከናወኑ ስራዎች የሀገሪቱን የመንገድ ሽፋን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ተችሏል::

የመንገድ ልማቱ ግን ብዙ ፈተናዎችን አልፎ ነው ለአገልግሎት ሲበቃ የሚታየው:: ከመንገድ ግንባታ ጋር ተያይዞ በርካታ ችግሮችም ይነሱ ነበር፤ አሁንም እየተነሱ ናቸው:: ከሀገራዊ ለውጡ በኋላ ባሉት ዓመታት በዘርፉ የታዩ ጥንካሬዎችን ለማስቀጠል እና ድክመቶችን ለማረም ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፤ የተጓተቱ ፕሮጀክቶችን በፍጥነት ለማጠናቀቅ ተሰርቷል፤ ይሁንና ዛሬም ልማቱን እያጓተቱ የሚገኙ ችግሮች ይስተዋላሉ::

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴርን የ2014 በጀት ዓመት የ10 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከትናንት በስቲያ ባዳመጠበት ወቅት ከምክር ቤቱ አባላት በርካታ ጥያቄዎች እና ማብራሪያዎች ከተጠየቀባቸው እና ምላሽና ማብራሪያ ከተሰጠባቸው ንዑስ ዘርፎች አንዱ የመንገድ መሰረተ ልማት ነው::

የሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸውን እና የተጠሪ ተቋማትን የአፈጻጸም ሪፖርት ያቀረቡት የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ባለፉት 10 ወራት በብዙ ችግሮች ውስጥ ሆኖም አመርቂ ውጤት አስመዝግቧል:: በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ለ2014 በጀት ዓመት የተያዙ የፊስካል ስራዎች 1 ሺህ 265 ኪሎ ሜትር ነባር መንገዶችን ለማጠናከር፣ የነባር መንገዶች ደረጃን ለማሻሻል፣ የአዲስ መንገዶች ግንባታን ለማከናወን፣ የፍጥነት መንገድ ግንባታን ለማካሄድ ታቅዶ 935 ኪሎ ሜትር መፈጸም ተችሏል:: ይህም እቅዱ 74 በመቶ ነው::

በሌላ በኩል 326 ኪሎ ሜትር መንገዶች ላይ ከባድ ጥገና ለማከናወን ታቅዶ 155 ኪሎ ሜትር ማከናወን መቻሉን ሚኒስትሯ ጠቅሰዋል:: ይህም ከተያዘው እቅድ 46 በመቶ ብቻ ነው:: በዚህ ዘርፍ የተመዘገበው አነስተኛ ነው:: ከአምናው አንጻር ሲታይም 11 በመቶ ቅናሽ ታይቷል:: ለዚህም ቅናሽ የኮምቦልቻና የነቀምት ዲስትሪክቶች ጥገና በግጭት ምክንያት መስተጓጎላቸው አፈጻጸሙ አነስተኛ እንዲሆን ማድረጉ ነው ተብሏል::

የ659 ኪሎ ሜትር ወቅታዊ መንገዶች ጥገና ለማከናወን ታቅዶ 523 ኪሎ ሜትር 79 በመቶ መከናወኑን የጠቀሱት ሚኒስትሯ፤ በዚህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ27 በመቶ ብልጫ መታየቱን ተናግረዋል:: በተጨማሪም የ8255 ኪሎ ሜትር መደበኛ ጥገና ለመስራት ታቅዶ 7204 ኪሎ ሜትር ጥገና መካሄዱን አስታውቀዋል:: በአጠቃላይ በመንገድ ግንባታና ጥገና የተመዘገበው አማካይ አፈጻጸም 84 በመቶ መሆኑን ነው ያመለከቱት::

ሚኒስትሯ ሪፖርቱን ለምክር ቤቱ ካቀረቡ በኋላ ከምክር ቤቱ አባላት በርካታ ጥያቄዎች እና ማብራሪያዎች ተነስተዋል:: ከአባላቱ ከተነሱ ጥያቄዎች መካከል የመንገድ ፕሮጀክቶች ጥራታቸው በተጠበቀ መንገድ እንዲገነቡ ምን ያህል ጥንቃቄ እየተደረገ ነው? የሚለው ይገኝበታል:: ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ወጥቶ የሚገነቡ መንገዶች ከመሬት መንሸራተት፣ ከአፈር መደርመስ እንዲሁም የመንገድ ግንባታ ግብዓችን አይነት እና ባህሪይ ካለማጥናት የተነሳ ለብልሽት ሲዳረጉ ይስታዋላል:: ስለሆነም ሀገሪቱ ባላት ውስን ሀብት የምትገነባቸው የመንገድ መሰረተ ልማቶች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉ የዘርፉን ውጤታማነት ለማሻሻል የተከናወኑ ሳይንሳዊ የምርምር ስራዎች እንዲሁም ስታንደርዳይዜሽን እና የቁጥጥር ስራዎች ምንድን ናቸው? የሚል ጥያቄ ተነስቷል::




በተጨማሪም የመንገድ መሰረተ ልማቶች በሚሰራባቸው አካባቢዎች ለሚካሄዱ የንብረት ግመታ፣ ካሳ ክፊያና ወሰን ማስከበር ችግሮች በወቅቱ መፍታት ባለመቻሉ የተጀመሩ የመንገድ ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜና ጥራት እንዳይጠናቀቁ ማነቆ ከመሆኑም ባሻገር ለመንገድ ግንባታ ከሚውለው ወጪ ጋር ተቀራራቢ የሆነ ሀብት ለካሳ ክፊያ እየወጣ ነው:: ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች በባለቤትነት እንዲሰሩ ከማብቃት፣ ከመደገፍና የአሰራር እና የህግ ስርዓት አዘጋጅቶች ከማሳተፍ አንጻር ምን ተሰራ? በህግ ማስከበርና በጸጥታ ችግሮች ምክንያት የተቋረጡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ወደ ስራ በማስገባት ረገድ ጦርነቱ በአንጻራዊነት ከቆመ በኋላ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያከናወናቸው ተግባራት ካሉ ቢገለጹ? የሚሉ ጥያቄዎችም ቀርበዋል::

አማካሪዎች፣እያስተዳደሯቸውእና እየተቆጣጠሯቸው ያሉትን ፕሮጀክቶች አስመልክቶ ለሚነሱ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣ የተስተካከለና ትክክለኛ መረጃ አለመላክ፣ የሚልኳቸው ሰነዶችም ቢሆኑ የጥራት ጉድለት የሚስታዋልባቸው መሆን፣ የተሟላ ዲዛይን አለማቅረብና የዲዛይን መቀያየር ይንጸባረቃል:: ስለሆነም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአማካሪ ድርጅቶች በሙያዊ ስነምግባርና ተጠያቂነት መንፈስ ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ ምን የህግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል? በመንገድ ዘርፍ በ2014 በጀት ዓመት ከታቀደው እቅድ ውስጥ በአስር ወር ውስጥ የፊስካል ስራዎች በአማካይ 79 በመቶ ማሳካት እንደተቻለ ሪፖርቱ ያመላክታል:: ይሁን እንጂ በሁሉም በሀገሪቱ አካባቢዎች የመንገድ መሰረተ ልማት ሽፋን ከህዝብ ፍላጎት አንጻር ተደራሽ ለማድረግ ምን እየተሰራ ነው:: በተጨማሪም ታቅዶና በጀት ተይዞላቸው ወደ ስራ ያልገቡ የመንገድ ፕሮጀክቶች ምክንያት ምንድን ነው የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ተነስተዋል::

ለተነሱት ጥያቄዎች የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ በሰጡት ምላሽና ማብራሪያ፤ የወሰን ማስከበር ችግር የመንገድ ግንባታ ዘርፍ ዋነኛው ማነቆ ሆኖ መቆየቱን አስገንዝበዋል:: በዋናነት የገንዘብ ፍሰት ችግር አንዱ ማነቆ መሆኑንም ጠቅሰው፣ በርካታ የወሰን ማስከበር ችግር ያጋጠማቸው ፕሮጀክቶች አሁንም እንዳሉ አስታውቀዋል:: ካለባቸው ወሰን ማስከበር ችግር አንጻር ግንባታቸው መቆም የነበረባቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች ቢኖሩም ከነችግራቸውም ቢሆን ፕሮጀክቶችን ላለማቆም ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል::

እንደ ኢንጂነር ሀብታሙ ማብራሪያ፤ በትክክል የካሳ ተመን ተገምቶ ያልተከፈላቸው በርካታ ባለመብቶች አሉ:: ይህም የመልካም አስተዳደር ችግር ሆኗል:: ከፍተኛ ሀገራዊ ችግር ውስጥ ተሁኖ ልማቱ እየተሰራ መሆኑን ህዝቡም ይገነዘባል::

የመንገድ ፕሮጀክት የፌዴራል መንግስት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ቢሆንም ባሉ ፕሮጀክቶች ልክ የገንዘብ ፍሰት የለም፤ የገንዘብ እጥረት አለ ያሉት ኢንጂነር ሀብታሙ፣ ለወሰን ማስከበር አንዱ ችግር ይህ የገንዘብ እጥረት መሆኑን አስታውቀዋል:: የሚጠየቀውን ከፍተኛ የካሳ ግምት መክፈል ለአስተዳደሩ አዳጋች እንደመሆነም ተናግረው፣ ሁሉም አካል ይህን አውቆ ልማቱ እንዳይቆም ሊተባበር ይገባል ሲሉ አስገንዝበዋል:: አንዳንድ ጊዜ ፍትሃዊ ያልሆኑ ካሳዎች ሲጠየቁ ይስተዋላል:: ይህ ሁኔታ ካልተቀየረ የፌዴራል የመንገድ ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠል አዳጋች መሆኑንም ነው ኢንጂነር ሃብታሙ ያስገነዘቡት::

ክልሎች በሚያስገነቧቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች ላይ መሰል ችግሮች ብዙውን ጊዜ ሲያጋጥም እንደማይታይ የጠቆሙት ኢንጂነር ሃብታሙ፣ የፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶችን ውጫዊ አካል ፕሮጀክቶች አድርጎ የማየት አዝማሚያዎች በመኖራቸው ችግሩ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል ይላሉ:: ወደፊት መሰል ችግር እንዳያጋጥም የወሰን ማስከበር ስራዎች በሚሰሩበት ወቅት የፌዴራል መንግስት ከክልሎች መንግስታት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ማስተካከያ እና ማሻሻያ መኖር አለበት:: የባለድርሻ አካላት ትብብር የሚያስፈልግ ጉዳይ ነውም ብለዋል::

እንደ ኢንጂነር ሃብታሙ ማብራሪያ፤ የጸጥታ ችግሮች ባሉባቸው እና ዝናብ በብዛት በሚጥልባቸው አካባቢዎች ግንባታ ለማከናወን ፍላጎትና አቅም ያላቸው ተቋራጮች እየተገኙ አለመሆኑንም ተናግረዋል:: ይህም ችግር በአንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ ፕሮጀክቶች ግንባታ እንዳይፋጠን እንቅፋት እንደሆነም አስታውቀዋል::

‹‹ብዙ ስራ እና ብዙ ፕሮጀክቶች አሉ:: ከዚህ ቀደም ከተገነባው በላይ የአስፋልት መንገድ ስራ እየተሰራ ነው:: ነገር ግን በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በቂ ተቋራጭ እየተገኘ አይደለም ሲሉም ተናግረዋል::

ሀገር ውስጥ ያሉ ተቋጮች ቁጥር እና አቅም ማነስ አንዱ ችግር ኢንጂነር ሀብታሙ ጠቅሰው፣ በሀገር ውስጥ የሚስታዋለው አለመረጋጋት የውጭ ሀገራት ተቋራጮች በብዛት ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይመጡ ተጽዕኖ እየፈጠረ መሆኑንም ጠቁመዋል:: በዚህ ምክንያት መጀመር የነበረባቸው በርካታ ፕሮጀክቶች ሳይጀመሩ መቆየታቸውን ኢንጂነር ሃብታሙ አንስተዋል::

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ ሰኒ በበኩላቸው በሰጡት ምላሽና ማብራሪያ፤ በሀገሪቱ የተከሰተው የጸጥታ ችግር በብዙ የመንገድ ፕሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ ውድመት ማድረሱን ጠቅሰው፣ ብዙ ማሽነሪዎች መዘረፋቸውንም አስታውቀዋል:: እነዚህን ማሽነሪዎች በግዥ እንተካ ቢባል ብዙ ጊዜ ሊፈጅ ይችላል ያሉት ሚኒስትሯ፣ ይህ ሁሉ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም እንዲጓተት የሚያደርግ ነው ብለዋል:: አንዳንድ መጠነኛ ጉዳት በደረሰባቸው እና በአንጻራዊነት ሰላማዊ በሆኑ አካባቢዎች ከተለያዩ ፕሮጀክቶች ማሽነሪዎችን በማንቀሳቀስ ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ጠቅሰዋል::

ሚኒስትሯ እንዳሉት፤ የመንገዶች አስተዳደር በመንገዶች ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ የሚሰራቸውን ስራዎች ውጤታማነት ከፍ ለማድረግ ያልተማከለ አሰራር ዘርግቷል:: መንገዶች አስተዳደር ከዚህ ቀደም ከ200 በላይ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ከማዕከል ነበር ክትትልና ቁጥጥር ሲያደርግ የነበረው:: ይህ በራሱ የአፈጻጸም ሂደቱን ያዘገየዋል:: የጥራቱን ክትትል እና ቁጥጥር እንዲደናቀፍ የራሱን ሚና ይጫወታል:: ይህንን ችግር ለመቅረፍ በእያንዳንዱ ዲስትሪክት የራሱን ፕሮጀክት አፊስ ማደራጀት ተችሏል:: እስከ ቀበሌ ያለውን የፌዴራል መንገድ ከአንድ ማዕከል ማስተዳደር ችግር ስለሚሆን ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቶችን በማደራጀት ክትትል እና ቁጥጥር በቅርበት እንዲደረግ ትልልቅ ስራዎች ተሰርተዋል::

ከመንገዶች ጥራት ጋር ተያይዞ፤ የግንባታ ጥራት ሳይረጋገጥ የሚሰሩ ስራዎች፣ የሶስተኛ ወገን ማረጋገጥ የማይችልባቸው አሰራሮች የጥራት ችግር እንዲፈጠር ምክንያት እንደሚሆኑ ተናግረው፣ ይህን ችግር ለመፍታትም በአፍሪካ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችል የምርምር ማዕከል ግንባታ ለማካሄድ ዝግጅቱ መጠናቀቁን አስታውቀዋል:: ማዕከሉ ለአብነት ያህል የግንባታ ግብዓቶችን መርምሮ ደረጃቸው ምን ይመስላል የሚለውን መለየት የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል:: ግብዓቱ ከደረጃ በታች ነው ወይስ ደረጃውን ያሟላል የሚለውን የሚያረጋግጥ ይሆናል:: የመጣው ግብዓት ከደረጃ በታች ከሆነ ጥቅም ላይ እንዳይውል ይደረጋል ብለዋል::

እንደ ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ ማብራሪያ፤ የካሳ ክፊያ ለመንገዶች ግንባታ መዘግየት ዋነኛው መንስኤ እየሆነ ከመሆኑም ባሻገር በፌዴራል መንግስቱ ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ነው:: ለካሳ ክፊያ ከ10 ቢሊየን ብር በላይ ወጪ እየተደረገ ነው:: ካሳዎቹ ተገቢ ናቸው ወይ የሚለው ያጠያይቃል::

አንዳንዶች የካሳ ክፊያ ተገቢ ስለሆነ ጥያቄ ሲያነሱ፤ በሌላ በኩል በማይገባው መንገድ የፖለቲካ ቅርጽ በማስያዝ ለሌላ ዓላማ የሚጠቀምበትም አካል አለ ያሉት ሚኒስትሯ፣ ይህንን በየፈርጁ ማየት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል:: የፌዴራል መንግስት መንገድ በዚህ አቅጣጫ ያልፋል ከተባለ በአንድ ሌሊት ጎጆ የሚቀለስበት እና ካሳ የሚጠየቅበት ሁኔታ እንዳለም ጠቅሰዋል::

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ የፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶችን በሌላ ሀገር መንግስት እንደሚገነባ ፕሮጀክት የማየት አዝማሚያ አለ:: አላግባብ ግምት ይጠየቃል:: እንዲህ አይነቶቹ ችግሮች ከከሳ አዋጁ ጋር የሚያያዙ በመሆናቸው የፌዴራል ፕሮጀክቶች የሚባሉት በቀጥታ ወደ ክልሎች እንዲወርዱ በማድረግ የህዝብ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መንገድ መቀጠል ያስፈልጋል::

የመንገድ ፖሊሲ ማሻሻያ ማድረግ ስለሚያስፈልግ የመንገድ ፖሊሲ በማስጸደቅ ሂደት ላይ ነው:: ይህ ፖሊሲ የፌዴራል መንግስት ክልልን ከክልል፣ ሀገርን ከሀገር ጋር የሚያገናኙ መንገዶች ላይ ትኩረት እንዲያደርግ እንዲሁም ክልሎች ደግሞ ዞንን ከክልል፣ ዞንን ከወረዳ የሚያገናኙ መንገዶች ላይ ትኩረት እንዲያደርግ ይሰራል:: ይህም በአሁኑ ወቅት ከወሰን ማስከበር እና ከካሳ ክፊያ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮችን ለመቅረፍ እንደሚያስችል ሚኒስትሯ ጠቁመዋል:: ፖሊሲው የባለቤትነት ስሜት እንዲኖር እንደሚረዳ ተናግረው፣ በእያንዳንዱ ፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ የራሱ የሆነ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረውም አስታውቀዋል፤ የጥራት እና የመዘግየት ችግሮችን ይፈታል ይላሉ::

በተለያዩ ምክንያቶች የቆሙ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠል 9 ነጥብ 9 ቢሊየን ብር ዳግም መለቀቁን የጠቆሙት ሚኒስትሯ፣ መንግስት ይህን እርምጃ የወሰደው ፕሮጀክቶቹ በአስቸኳይ ማለቅ ያለባቸው በመሆናቸው ነው ብለዋል:: ለፕሮጀክቶቹ ዳግም ፈንድ መለቀቁ ሌሎች ፕሮጀክቶችን የሚገነቡ ተቋራጮች የዋጋ ማሻሻያ ይደረግልናል በሚል ስራዎችን እንዳያጓትቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል ብለዋል::

የመሰረተ ልማትና ኮንስትራክሽን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ፤ በመጨረሻ የመንገድ ዘርፍን አስመልክተው በሰጡት ማጠቃለያ የመንገዶች አስተዳደር ከነበረው ሁኔታ አንጻር ሲታይ ፊስካል አፈጻጸሙ ጥሩ መሆኑን ጠቁመው፣ በርካታ ተስፋ ሰጪ የሪፎርም ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን በመስክ ምልከታ መታዘብ መቻሉንም አስታውቀዋል:: የተጀመሩ መልካም ስራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ያስገነዘቡት ሰብሳቢዋ፤ ከዚህ ጎን ለጎን በምክር ቤቱ በጀት ተይዞ እና ታቅዶ ወደ ስራ ያልተገቡ የመንገድ ፕሮጀክቶች፤ ከካሳ ክፊያ እና ወሰን ማስከበር በመሳሰሉ በተለያዩ መሰል ችግሮች ምክያቶች የቆሙ ፕሮጀክቶች በልዩ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቶ ከሚመለከታቸው ክልሎችና ከስራ ሀላፊዎች ጋር በመቀናጀት ፈጣን ምላሽ መስጠት እንዳለበት አስገንዝበዋል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለግብርና የተሰጠው ልዩ ትኩረት ከዘርፉ የሚጠበቀውን ግዙፍ ውጤት የሚያሳካ ነው!

ይህ ወቅት የሀገራችን የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነው የግብርናው ዘርፍ በእጅጉ ባተሌ የሚሆንበት ነው፡፡ አርሶ አደሩ በተለይ ከሰሞኑ አሀዱ ያልነውን ሰኔን ይዞ ባሉት ቀጣይ ወራት ለእርሻ ስራው ሙሉ ጊዜውን፣ እውቀቱንና ጉልበቱን ሳይሰስት የሚሰጥበት ነው፡፡

ግብርናው ፊትም የሀገር ዋልታና ማገር ሆኖ የኖረ አሁን ደግሞ የሀገር የምግብ ዋስትና መሰረትና የውጭ ምንዛሬ አለኝታ መሆኑን በተጨባጭ እያረጋገጠ የሚገኝ እንደመሆኑ በእርግጥም በዚህ ወቅት ለዚሁ ትልቅ ሥራ መባተሉ የሚያስመሰግን ነው፡፡ ዓለም በምግብ እህል ዋጋ መወደድ እና እጥረት እየታመሰ ባለበት በዚህ ወቅት የሀገራችን ግብርና ከ366 ሚሊየን ኩንታል በላይ እህል በመኸር ወቅት ብቻ አምርቶ ህዝቡን እየመገበ ይገኛል፡፡

ሀገራችን በምግብ ዋስትና በኩል የሚቀራት ስራ የሚያስፈልጋትን ያህል ስንዴ አለማምረት ላይ ሆኖ ቆይቷል፤ በዚህ የተነሳም በስንዴ ሊለማ የሚችል ሰፊ መሬት እያላት በየዓመቱ የውጭ ምንዛሬ በማውጣት ስንዴ ከውጭ ስታስገባ ኖራለች፡፡ ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ ግን ሀገር በዚህ ሁኔታ መቀጠል የለባትም የሚል አቋም በመንግስት ተይዞ መሰራቱን ተከትሎ ከጥቂት ዓመታት በፊት በቆላማዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ስንዴን በመስኖ ለማልማት የተጀመረው ጥረት ገና ከጅመሩ ስኬታማ እየሆነ ነው፡፡ ልማቱ በደጋና ወይናደጋ አካባቢዎች እንዲሰፋ ተደርጓል፡፡ በዚህ የበጋ ወቅት ብቻ 400 ሺ ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ በማልማት ከ16 በሚሊየን ኩንታል በላይ ማምረት ተችሏል፡፡

ግብርናው የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ብቻ አልተወሰነም፡፡ በውጭ ኃይሎች ጫና እና በመሳሰሉት ችግሮች ሳቢያ ሀገር በውጭ ምንዛሬ እጥረት እየተፈተነች ባለችበት በዚህ ወቅት ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት በኩል ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ዘርፍ መሆን ችሏል፡፡ ከግብርናው ዘርፍ ቡና ብቻውን ከአንድ ቢሊየን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ አስገኝቷል፤ ይህ ግኝት የግብርናው ዘርፍ ካስገኘው የውጭ ምንዛሬ 50 በመቶውን ይዟል፡፡

ዘርፉ ይህን ያህል ስኬታማ የሆነው መንግስት በኩታ ገጠም እርሻ፣ በግብአት አቅርቦት፣ በበጋ መስኖ እንዲሁም አንድም ማሳ ጦም እንዳያደር በሚል ባከናወናቸውን ተግባራት እንዲሁም አርሶ አደሩም በእነዚህ ላይ ጭምር በመመስረት ባደረገው ርብርብ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ሀገር በጦርነት እና በውጭ ኃይሎች ጠንካራ ጫና ፈተና ውስጥ በነበረችበት የምርት ዘመን ይህን ያህል ስኬት ማስመዘገብ ከተቻለ ሀገር ሰላም በሆነችበት፣ የውጭ ተጽእኖውም ረገብ ባለበት በዚህ የመኸር ወቅት ግብርናው ላይ ይበልጥ ኢንቨስት በማድረግ ምርትና ምርታማነቱን ማስቀጠል አልፎም ተርፎ ይበልጥ ማሳደግ እንደሚቻል ጥርጥር የለውም፡፡

ዘንድሮ ግብርናውን ውጤታማ ለማድረግ የሚረዱ አስቻይ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ መንግስት ግብርናውን ለማዘመን ከመቼውም ጊዜ በላይ እየሰራ ነው፡፡ በቅርቡ የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ሁሴን እንዳረጋገጡትም፤ መንግስት ለግብርናው ትኩረት መስጠቱን ተከትሎ አበረታች ስኬቶች እየተመዘገቡ ናቸው፡፡

መንግስት ግብርናውን ከኋላ ቀር አስተራረስ ለማውጣት እየወሰደ ባለው እርምጃ ሜካናይዝድ የግብርና መሳሪያዎች ያለቀረጥ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ ዋና ዋናዎቹ እህል አምራቾች የአማራና ኦሮሚያ ክልሎች ትራክተሮችን ለአርሶ አደሮች በብዛት እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡ አስቀድሞም በኩታ ገጠም እርሻ ላይ በትኩረት እየተሰራ አንደመሆኑ የትራክተሮቹ መገኘት ደግሞ ግብርናው ይበልጥ የዘመነ እንዲሆን በማድረግ ለበለጠ ምርትና ምርታማነት ያበቃዋል፡፡

ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ትኩረት በመስጠት እየተሰራ ነው፤ በበጋ መስኖ በስንዴ ዘር የሚሸፈነውን ማሳ ከ400 ሺ ሄክታር ወደ አንድ ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ ይህን በአምስት ክልሎች የተጀመረውን የበጋ መስኖ የስንዴ ልማት በቀጣይ ወደ ሌሎች ክልሎች በማስፋት ጭምር የሚተገበር ነው፡፡ እንደ መንግስት እምነት የሀገሪቱን የስንዴ ፍላጎት በማሟላት በቅርብ ዓመታት ስንዴ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታስቧል፡፡ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የተገኙ ተሞክሮዎችም የተቀመጡ ዕቅዶችን ለማሳካት እንደሚቻል የሚያመላክቱ ናቸው፡፡

ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ግብአቶችን ለማቅረብና ለማሰራጨት ከፍተኛ ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፤ ከውጭ ኃይሎች ጫና ጋር በተያያዘ ማዳበሪያ ማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ ቢቆይም፣ መንግስት በወሰዳቸው እርምጃዎች ለምርት ዘመኑ የሚያስፈልገውን ማዳበሪያ በወቅቱ ማግኘት ተችሏል፡፡ በዚህም የ12 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሞ ጅቡቲ ወደብ ከደረሰ ቆይቷል፡፡ ከእዚህ ውስጥም ሰባት ነጥብ ሰባት ሚሊየን ኩንታሉ ወደ ክልሎች ተጓጉዟል፡፡ ሶስት ሚሊየን ኩንታሉ አርሶ አደሩ እጅ ገብቷል፡፡ የማዳበሪያ ፍላጎት እየጨመረ መምጣትን ተከትሎ ሊኖር የሚችለውን ክፍተት ለመሙላት የተፈጥሮ ማዳበሪያ ላይ በትኩረት ለመስራት ታቅዷል፡፡ በምርጥ ዘር አቅርቦት በኩል ተመሳሳይ ተግባር እየተከናወነ ነው፡፡

የሚትዮሮሎጂ መረጃዎች እንደሚያመለክቱትም የዘንድሮው የክረምት ወቅት የአየር ሁኔታ ለግብርናው ስራ ምቹ ነው፡፡ ጸረ ሰብል ተባይ በሰብል ልማት ላይ የሚደርሰውን የተባይና በሽታ ጉዳት ለመቀነስ አምስት የርጭት አውሮፕላኖች እና የ23 ድሮኖች ግዥ ተፈጽሟል፡፡ ይህም በየጊዜው የሃገሪቱን ግብርና እየተፈታተነ ያለውን የድህረ ምርት ብክነት ለመቀነስ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ታምኖበታል፡፡

እነዚህ አስቻይ ሁኔታዎች የግብርና ሚኒስቴር በ2014 / 2015 የመኸር ወቅት 390 ሚሊየን ኩንታል ለማምረት የያዘውን እቅድ ለማሳካት እንደሚቻል ያመላክታሉ፡፡ የግብርናውን ዘርፍ እቅድ ለማሳካት አስቻይ ሁኔታዎች ናቸውና ምቹ መደላድልም ይፈጥራሉ፡፡ በቀጣይ ደግሞ አርሶ አደሩ፣ የግብርና ባለሙያውና ሌሎች ከግብርናው ዘርፉ ጋር ጥብቅ ትስስር ያላቸው ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ርብርብ እንዲያደርጉ መስራት ያስፈልጋል፡፡

አርሶ አደሩ ማሳውን ማለስለስ፣ በወቅቱ በዘር መሸፈን እና ቡቃያውን መንከባከብ የሁልጊዜ ስራዎቹ ቢሆኑም ስራውን ከዕለት ተለት ስራ በማውጣት ለበለጠ ምርትና ምርታማነት ቤተሰቡን ይዞ መስራት ይኖርበታል፡፡ ሌሎች ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አርሶ አደሮችም ድጋፍ በማድረግ እንደ መንግስት የተያዘው እቅድ እንዲሳካ መስራት ይገባል፡፡

የግብርና ባለሙያው ምክርና ድጋፍ በመስጠት የትራንስፖርት ዘርፉና እንደ ኅብረት ስራ ማህበራት ያሉት ተቋማት ደግሞ ለአርሶ አደሩ የሚያስፈልጉ እንደ ግብአት ያሉትን በወቅቱ እና በሀገር ዋጋ መሰረት እንዲደርሱ በቅርበት እና በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል፡፡ በተለይ ማደበሪያ በማሰራጨት በኩል ከዋጋ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ተገቢ ያልሆኑ የዋጋ ጭማሪዎች እንዳይኖሩ ማድረግም አስፈላጊ ነው!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአዲሱ ክልል ተስፋዎች እንዳይከስሙ እንጠንቀቅ

(አቤል ገ/ኪዳን)

ሰሞኑን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መግለጫ አውጥቷል፡፡ አዲስ የተወለደው ክልል እስካሁን በዝምታ ስራውን እየሰራ ከሚዲያ ትርኢት ርቆ ስለቆየ መግለጫው ትኩረትን የሚስብ ነበር፡፡ረዘም ያለው መግለጫ ካህዴህ ለተባለ በክልሉ ለሚንቀሳቀስ ፓርቲ መግለጫ የተሰጠ ምላሽ ነበር፡፡

"በህዝቦች መፈቃቀድና መተባበር የተፈጠረ ክልል በተዛባ መረጃና ፕሮፖጋንዳ ሊናወጥ አይገባም!!" በሚል ርዕስ የተሰጠው መግለጫ ከክልሉ ርዕሰ መዲናነት ጉዳይ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ለካህዴህ መግለጫ የተሰጠው የክልሉ ምላሽ እንደሚለው ከሆነ ካህዴህ የክልሉ መመስረት ለከፋ ህዝብ የሚጎዳ ነው ብሎ መግለጫ እንደሰጠ እንዲሁም የክልሉ መዲና ከአንድ ከተማ ወደ ብዙ ከተማ መቀየሩ እንዳልተስማማው የሚያሳይ ነው፡፡

በመጀመሪያ ወደ ሌሎች ዝርዝሮች ከመግባታችን በፊት ጥቂት ማስታወሻዎችን እንያዝ፡፡አንደኛ ጉዳይ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ሀገሪቱ ላለፉት ሶስት አስርት አመታት ስትከተለው ከቆየችው ብሄርን መሰረት ያደረገ የክልል አደረጃጀት በተለየ ሁኔታ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥን ፤ሶሺዮ ኢኮኖሚን እና ፖለቲካዊ ትንታኔን ተከትሎ የተመሰረተ ክልል ነው፡፡

ይህም ማለት ክልሉ ከሌሎቹ ክልሎች በተለየ ስድስት የተለያዩ ህዝቦች ( ካፋ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ምዕራብ ኦሞ እና ኮንታ) በጋራ ስምምነት የመሰረቱት ክልል ነው፡፡ ይህ ለኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርዓት አዲስ ልምምድ ነው፡፡በመሆኑም የዚህ ክልል ስኬትም ሆነ ውድቀት ብዙ አንድምታ ይኖረዋል፡፡

የክልሉ ምስረታ ጉዳይ ከለውጡ ወዲህ ከተከናወኑ ትልልቅ ፖለቲካው እርምጃዎች መሀከል አንዱ ሲሆን በአንድ ጎን የህዝብን ራስን በራስ የማስተዳደር እድል ለሚጠይቁ የፖለቲካ ሀይሎች መሻታቸውን የመለሰ ነው፡፡በሌላ መልኩ አሁን ያለው በቋንቋ ላይ የተመሰረተ ፌደራላዊ አወቃቀር ሌላ አማራጭ ያስፈልገዋል ለሚሉም እንዲሁ ሌላኛው አማራጭ በተግባር ሲውል የሚታይበትን እድል የሰጠ ነው፡፡

ከሁሉም በላይ ግን የክልሉ ምስረታ የስድስቱን ህዝቦች የዘመናት የልማት እና የዴሞክራሲ ጥያቄ መልስ የመስጠት ሂደት ያስጀመረ አጋጣሚ ነው፡፡ስለዚህም ክልሉ የውስጡንም ሆነ የውጪውን ሀይል ፍላጎት ያረካ ክልል ነው ማለት እንችላለን፡፡ይህ የካህዴህ መግለጫ መልስ ያስፈለገውም ከዚህ አዎንታዊ መንፈስ የሚቃረን በመሆኑ ይመስላል፡፡

በሌላ መልኩ ይህ አዲስ ክልል አዲስ አሰራርም ይዞ መጥቷል፡፡እሱም ብዝሀ ከተማነት ነው፡፡ይህም በክልሉ ህገ መንግስት የሰፈረ ነው፡፡በህዳር 14/2014 የጸደቀው የክልሉ ህገ መንግስት በስድስተኛ አንቀጹ ላይ "የክልሉ መንግስት ብዝሀ ዋና ከተሞች ይኖሩታል፡፡ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል" ይላል፡፡

ይህም በሌሎቹ ክልሎች ካለው የተለየ እና ለኢትዮጵያ ፖለቲካም አዲስ ልምምድ ነው፡፡እነዚህ ሁለት ምክንያቶች ማለትም ምልክአ ምድርን እና ሶሺዮ ኢኮኖሚን የተከተለ የክልል አመሰራረት እና ብዝሀ ዋና ከተማነት አዲስ እና ምናልባትም ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ውጥንቅጥ ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉ ተስፋ ሰጪ ክስተቶች ናቸው፡፡ስለዚህም እነዚህን ፖለቲካዊ እርምጃዎች በጥንቃቄ መምራት ያስፈልጋል፡፡

ወደ ዋናው ጉዳያችን ስንመለስ ባለ 7 ነጥቡ የካህዴህ መግለጫ መሰረታዊ ጭብጡ አንድ ነው፡፡ ይሄውም የክልሉ ብዝሀ ከተማነትን መቃወም ነው፡፡ እልፍ ብሎም በሶስተኛ ነጥቡ ላይ የክልሉ ርእሰ መዲና መሆን ያለበት የካፋ ዞን ነው ይላል፡፡ሌሎቹ የተቃውም አመክንዮዎች የክልል ርዕሰ መዲና በመሆን ከሚገኝ ከልማት ተጠቃሚነት እንዲሁም የክልሉ ርዕሰ መዲናዎች ብዙ ቦታ መሆናቸው ከሚያመጣው ሎጅስቲካዊ ጣጣ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በነዚህ መከራከሪያዎች ላይ ብዙ ማለት አይቻልም፡፡ምክንያቱም የክልሉ ህዝብ ከ6 ወር በፊት ባጸደቀው ህገ መንግስት ላይ ወስኖባቸዋልና፡፡ይልቁንም ብዙ ማለት የሚቻለው ይህን አዲስ ዴሞክራሲያዊ የሆነ እመርታ ሳይጨናገፍ እንዴት እናስቀጥለው በሚለው ላይ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ይህ ክልል ስድስት ህዝቦች በስምምነት የመሰረቱት የተለየ ክልል ነው፡፡ይህም አዲስ እና ትልቅ እመርታ ነው፡፡እያንዳንዱ ዞን እና ብሄር ክልል ልሁን ብሎ ሀገር በሚያምስበት በዚህ ወቅት በስምምነት በሰላማዊ መንገድ ክልል መሆን መቻል አስገራሚ እና ሊበረታታ የሚገባ የፖለቲካ እርምጃ ነው፡፡

በሌላ መልኩ ቀደም ብለን እንደገለጽነው ክልሉ ዋነኞቹ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ርእዮቶች የተዋሀዱበት እና የተስማሙበት ነው፡፡ሶስተኛ ባለብዙ ርዕሰ ከተማ መሆኑ በሌላው አለም የተለመደ ቢሆንም በእኛ ሀገር ሆኖ የማያውቅ በመሆኑ ይህም ተስፋ ሰጪ እመርታ ነው፡፡

የተለያዩ ሀይሎች በአንዲት ከተማ ላይ የበላይ ለመሆን በሚተራመሱባት ሀገር ሁላችንም ልማቱንም ውሳኔውንም በጋራ እንካፈል የሚል መንፈስ አስደሳች ነው፡፡ለዚህም ነው እንደ ካህዴህ ያሉ ፓርቲዎችን መግለጫ በጥንቃቄ ማየት የሚያስፈልገው፡፡ በብዙ ተስፋ የተመሰረተ ክልል ወደ ኋላ እንዳይንሸራተት እና ትርምስ ውስጥ እንዳይገባ ሁሉም የፖለቲካ ሀይሎች እርምጃቸውን ሊጠነቀቁ ይገባል፡፡

የክልል መዲናነትን በተመለከተ እንኳን በክልል ከተማነት ይቅርና በሀገርም ደረጃ ቢሆን ከአንድ በላይ መዲና ያላቸው ከተሞች ብዙ ናቸው፡፡ለምሳሌ ያህል ናይጄሪያ ፤ ታንዛንያ ፤ ቤኒን ፤ አይቮሪኮስት እና ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ከአንድ በላይ መዲና አላቸው፡፡ከአፍሪካ ውጭም ሆላንድ ፤ ቦሊቪያ ፤ እስራኤል እና ሌሎችን መጥቀስ እንችላለን፡፡ስለዚህም በሀገር ደረጃ የሰራ በክልል ደረጃ አይሆንም ማለት አይቻልም፡፡

እንደ አሜሪካ ባሉ ሀገራት ደግሞ ህግ አውጪው፤ ህግ ተርጓሚው እና ህግ አስፈጻሚው አካላት በመዲናይቱ ዋሽንግተን ቢቀመጡም እንኳ የኢኮኖሚ መዲናዋ ኒውዮርክ ናት፡፡ኒውዮርክ የአሜሪካ የኢኮኖሚ ማዕከል የሆነችው በነበራት መልክአ ምድራዊ ብልጫ ነው፡፡ ከተማዋ ያሏት ወደቦች እና ለወደቦች ቅርበት አውሮፓውያን ነጋዴዎች ማረፊያቸው እንዲያደርጓት እንዳስገደዳቸው ታሪክ ይናገራል፡፡

ከዚህ በመነሳት ከደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል ከተሞች መሀከል አንዷ ባላት መልክአ ምድራዊ ወይም ሌላ አይነት ብልጫ የክልሉ የኢኮኖሚ ማዕከል ስትሆን ሌላዋ የፖለቲካ ማዕከል ልትሆን እና የክልሉን ምክር ቤት ልትይዝ ትችላለች፡፡ የክልሉ ፌደራል ፍርድ ቤትን ሌላኛዋ ከተማ ልትወስድም ትችላለች፡፡

በዚህ መልኩ የክልሉ የመንግስት ስራ አንድ ቦታ ላይ እንዳይከማች እና ሁሉንም ተጠቃሚ እንዲያደርግ ማድረግ ይቻላል፡፡ ከዚያ በተለየ የክልሉ መዲና አንድ ቦታ ይሁን ከተባለ ክልሉን ከመሰረቱት ስድስት ህዝቦች አምስቱ የህዋሳው ጉዞ ቀርቶ ወደ አዲሱ መዲናቸው መሄድ ይቀጥላሉ ማለት ነው፡፡ይህ ደግሞ ከክልሉ የመመስረት አላማዎች አንዱን ብላሽ ያደርገዋል፡፡

ሲጠቃለል ሀሳብን መግለጽ እና ተቃውሞን ማሰማት መብት ነው፡፡ለክልሉ እድገትም ይጠቅማል፡፡ ነገር ግን ከ6 ወር በፊት ያጸደቁትን ህገ መንግስት ገና በ6ኛው ወር አልተሳተፍኩበትም ማለት አያዋጣም፡፡ እኔ በፈለግኩት መንገድ ነገሮች ካልሄዱ ተነጥዬ ክልል እሆናለሁ ማለት በተጨባጭ የማያስኬድ ሀሳብ ነው፡፡

ብቸኛው መፍትሄ የተገኙ ድሎችን አጠናክሮ በመቀጠል በሰጥቶ መቀበል መርህ መፍትሄዎችን መፈለግ ነው፡፡በዚህ መንገድ የሚመጣ የዚህ ክልል ስኬት ምናልባትም ለኢትዮጵያ አዲስ አማራጭ መስመር ሊፈጥር ይችላል፡፡

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ከጣራው ስር - ለመኖር አለመብላት፣ባለመብላት መኖር

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ደምቆ ከሚታየው ሰፈር ራመድ ብሎ ከጠባቧ ግቢ ጎራ የሚል ቢገኝ ድንገት ከህሊናው ሊላተም ፣ ከማንነቱ ሊጣላ ግድ ይለዋል:: በእርግጥ ለእንዲህ አይነቱ እውነት በተፈጥሮ የሚቸር ዕዝነ- ልቦና ያስፈልግ ይሆናል:: እንደኔ ግን ሰው ሆኖ መፈጠር ብቻውን ለስሜቱ መጋባት በቂ ነው እላለሁ ::

ስድስት ኪሎ አካባቢ ተገኝተናል:: በተለምዶ ምስካየ ኅዙናን መድኃኒዓለም ከሚባለው ሰፈር:: አስፓልቱን ሻገር ብለን እንደነገሩ መለስ ያለች የአንዲት ግቢ በርን ከፍተናል:: እንደው ለወጉ «ግቢ» እንበለው እንጂ ቦታው ሁለት ሰዎችን ጎን ለጎን አያራምድም :: ስፍራው ለመንገዱ ግርግር የቀረበ ቢሆንም ግቢው በሚያስደንቅ ጭርታ ተውጧል::

የአስፓልቱን ሁካታ ለጀርባችን ትተን በቀጭኑ ሽለቋማ መንገድ ወደውስጥ አለፍን:: ዓይኖቻችን በቁልፍ የተዘጉ ጎስቋላ ቤቶችን እያስቃኙን ነው:: ግድግዳውን እየታከክን ፊትና ኋላ ተራመድን :: ብዙ አልራቅንም:: ከአንድ የተከፈተ ቤት ደጃፍ ስንደርስ ባለንበት ልንቆም ግድ ሆነ:: በሩን አልፈን ወደውስጥ ለመግባት እግራችን ተገታ :: መግቢያው በዋዛ ዘው የሚባልበት አልሆነም:: ለመራመድ የሚፈትነውን የዝቅታ ደፍ በጥንቃቄ ማለፍ ያስፈልጋል::

ሁኔታው እያስደነቀን ወደውስጥ ዘለቅን:: ጠባቧና ጽዱ ክፍል ቁልጭ ብላ ታየችን:: አራት ማዕዘኗን ቤት ለአፍታ ቃኘናት:: በአንደኛው ግድግዳ የእጅ መዳፍ የምታክል መስኮት ቢጤ ተለጥፎላታል:: ለንፋስ መሆኑ ነው:: ይህች ጎጆና ባለቤቷ ለዓመታት አብረው ዘልቀዋል::

ጠባቧ ቤት ጎን ከማሳረፍ የዘለለ ለአሳዳሪዋ ማብላት ማጠጣት ይሉትን ወግ አታውቀውም:: ከጣራዋ በታች ውላ ለምታድረው አንዲት ነፍስ ውህን ሳትለግስ ፣ ረሀብ ጥማት ሳታስታግስ ዓመታትን ገፍታለች:: በእነዚህ ጊዜያት በትኩስ ዕንባ የታጀቡ የመከራ ቀናት ተቆጥረዋል:: መከራው ፍፃሜ አልባ እስኪመስልም ከዘንድሮ ደርሷል::

በዚህች ቤት አሁንም ፍላጎት፤ ከተፈጥሮ እየተጋጨ፤ ፍጡር በተፈጥሮ እየተፈተነ ውሎ አዳሩ ቀጥሏል :: ለመኖር፤ እስትንፋስን ለማርዘም ባለው ትግል ግብግቡ አልተቋጨም:: የዚህ ቤት ሕይወት ከሌሎች ሁሉ ይለያል:: የማይቻለውን ችላ ቀኗን የምትገፋው ሴት በቤቷ በልቶ የማደር ወግን አልታደለችም:: ከራሷና ከተፈጥሮ መጋጨት ግጼታዋ ሆኗል::

ከጣራው ስር በየቀኑ ለሚፈሰው ትኩስ ዕንባ፤ ግድ የሚለው የለም:: በየዕለቱ ስለሚራበው ሆድና በውሀ ጥም ስለሚደርቀው ጉሮሮም አንዳች የሚደነቅ አልተገኘም:: አዎ! በቤቱ ሁሌም የምግብ ሽታ ያውዳል:: እንደወጉ እሳት ነዶ፤ እንደ ራስ አቅም ወጥ እንጀራው ይዘጋጃል::

ይህን ያደረጉ እጆች ግን ቀን ለዚህች ነፍስ አጉርሰው፤ አጠጥተው አያውቁም:: እነሱ መብላት ላማረው ሆድ፤ ጥም ላሳረረው ጉሮሮ ሊሆኑ አልታደሉም:: ይህን እንሞክረው ቢሉ እነሱም ከተፈጥሮ ይጋጫሉ:: በቤቱ እህል ውሀ ከአፍ አይደርስም:: ተበልቶ፤ተጠጥቶ«ተመስገን ማለት አይታወቅም:: በየቀኑ ከምሰቡ የሚያፈጡ ፣ዓይኖች በእንክርት ውለው ያድራሉ:: አይደበቄው እውነት ለጎጇዋ ባለቤት የተፈረደ ይመስላል:: እሷ እንደሰው ወግ ባትሆን በትካዜ ተውጣለች:: በትኩስ ዕንባ ተሸፍናለች::

ተመልሰን ወደውጭ እየወጣን ነው:: ከበሩ ማሬ ደሴ ትጠብቀናለች:: ቁጭ ብለን ከማውጋታችን በፊት ገጽታዋ በትኩስ ዕንባ ተቀበለን:: «አይዞሽ! » ብሎ ማጽናናቱ ቀላል አልነበረም:: ይህን ቃል ማሬ ምናልባትም ለዓመታት ሰምታው ይሆናል:: በየቀኑ እንዲህ መባሉ ለእሷ ብርቅ አይደለም:: የማያባራ ትኩስ ዕንባ፤ ከልብ የማይወጣ ሲቃና ብሶት መገለጫዋ ሆኗል::

አሁንም በጉንጮቸዋ እየወረደ በአንገቷ የሚንቆረቆረው ዕንባ አላባራም::እንደምንም አረጋግተን ታሪኳን እንድትነግረን ጠየቅናት:: ሳግ እያነቃት፤ ልታወጋን ተዘጋጀች:: አልቻለችም:: በዓይኖቿ የሞላው ትኩስ ዕንባ ቀደማት:: አልከለከለችውም:: ከልጅነት ማንነቷ ከሚቀዳው እውነት፤ እየኖረችው እስካለው የመከራ ሕይወት ትተርክልን ያዘች::

### ልጅነቴ ማርና ወተቴ...

በቀዬው የሚጫወቱት የሰፈር ልጆች ቡረቃ አልቀዘቀዘም:: እየሮጡ ይፈነድቃሉ ፣ እየጮሁ ይደሰታሉ:: በመንደሩ መሐል የቆመው የድንጋይ ቤት እንደወትሮው ልጆቹን ቁልቁል እያስተዋለ ነው :: በዕድሜ ጠገቡ የካብ ቤት ዙሪያ ሕፃናቱ ጨዋታቸው ቀጥሏል::

የአስራ ሁለት ዓመቷ ማሬ ዛሬም ጓደኞቿ መሐል ተገኝታለች:: ገና በሶስት ዓመቷ እናቷን ያጣችው ታዳጊ ብቸኝነት ይሰማታል:: እህት ወንድሞቿ ባልታወቀ ምክንያት ተከታትለው ሞተዋል:: አሁን ከአባቷ በቀር «የኔ» ትለው የላትም:: ኃዘንተኛው አባት የመጨረሻ ልጃቸውን በመንደሩ ትተው ከአካባቢው ርቀዋል::




ማሬ ደሴ

ልጆቹ እየቦረቁ ይዘላሉ ፣ይሮጣሉ:: አሁንም አንጋፋው የድንጋይ ቤት ከላይ ሆኖ ቁልቁል ያያቸዋል :: ቤቱ ድንገት ሸርተት እንደማለት ሞከረ :: ሁኔታውን ያስተዋለው የለም :: የዓመሉ መለወጥ ያልገባቸው ሕጻናት ጨዋታውን አላቆሙም:: አሁን የካቡ ቤት ያለ ይመስላል:: ለአፍታ ተንገዳግዶ በቁመናው ተዘረገፈ:: ድንጋይ በድንጋይ ተቀባብሎ ከመሬቱ ሲያርፍ በመንደሩ አስደንጋጭ ድምጽ አስተጋባ:: ስፍራው በአቧራ ጭስ ፣ተሸፍኖ :: የልጆቹ ድምጽ በከባድ ነውጥ ተዋጠ::

ድንገት የቤቱን መደርመስ ያስተዋሉ ጩኸታቸው በረከተ:: ከደቂቃዎች በፊት በርከት ያሉ ልጆች ቤቱ ስር ይጫወቱ ነበር:: ሁሉም በዓይኖቻቸው ፈለጓቸው:: «ተመስገን » አብዛኞቹ ከጉዳት ነጻ ሆነዋል:: እፎይታን ተቀባበሉ:: አፍታ አልቆዩም:: ማሬን አስታወሷት:: ከተረፉት መሐል አልታየችም:: ተደናግጠው ፍለጋቸውን ቀጠሉ:: አላጧትም:: ልጅቷ ከተደረመሰው ካብ ስር ትልቅ ድንጋይ ተጭኗት ወድቃለች::

ሁኔታውን ጠጋ ብለው አስተዋሉ:: ሰዎቹ ክፉኛ የተጎዳችውን ልጅ ደፍረው ሊያነሷት አልሞከሩም:: አባቷ ከሄዱበት እስኪመለሱ ጠበቁ :: አባት እየሮጡ ከመንደሩ ደረሱ:: በሰላም የተዋት ልጃቸው አይሆኑ ሆናለች:: እግሮቿ፤ ተላቀዋል:: ወገቧ ተሰብሯል:: ዓይኖቿን እንጨት ወግቷቸዋል፡፤እጆቿ እየሠሩ አይደለም::

አባት ፈጥነው የወደቀች የሙት ልጃቸውን አነሱ:: ዕለቱን ሕክምና ማድረስ አልሆነላቸውም:: የገጠር ሕይወት የሀገር ቤት ኑሮ ቢያግዳቸው ቀናትን ቆጠሩ:: አንድ ቀን የማሬ አጎት ከቤት ደርሰው ሕክምና ሊወስዷት ቆረጡ:: ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሆነ ::

### አዲስ አበባ..

ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የደረሰችው ማሬ ሕክምና አገኝታለች:: ዕለት በዕለት የሚከታተሏት ሐኪሞች ጉዳቷ የከፋ መሆኑን አውቀዋል:: ማሬ በከባድ ስቃይ ሕይወትን ቀጥላለች:: አሁን መላ አካሏ እያገዛት አይደለም:: እጇቿ አይታዘዙም :: የእግሮቿ ጉዳት ከፍቷል :: አንደኛው ዓይኗ ጠፍቶ አንዱ ስጋት ላይ ነው:: ብሶተኛዋ ታዳጊ ብቸኝነትን ከስቃይ መቀበል ይዛለች::

ሐኪሞቹ ለማሬ ትጋታቸውን ቀጥለዋል:: ድካማቸው ፍሬ የያዘ አይመስልም :: ለወራት በእጃቸው የቆየችው ጉዳተኛ ሁኔታ ተስፋ ያስቆርጣል:: ለእግሯ ብረት አስገብተው በክራንች ሞክረዋል :: የወገቧ ጥልቅ ጉዳት አካሏን ማንቀሳቀስ አልቻለም:: አሁን ማሬ ቆሞ የመሄድ ሕልሟ ከስሟል :: ይህን ተከትሎ የአባቷን ሞት መስማቷ ልቧን ክፉኛ ሰብሮታል::

### ኑሮ በዘመድ ቤት...

ማሬ ከሆስፒታል ከወጣች በኋላ በዊልቸር ልትጠቀም ግድ ብሏል:: ቀጣዩን ሕክምናና ማረፊያ ያገዛት የማዘር ትሬዛ ማዕከል ለአንድ አመት ተንከባከባት:: ጥቂት ቆይቶ ግን ከድርጅቱ ተሰናበተች :: ማሬ አዲስ አበባ ‹‹የኔ›› የምትለው ሰው የለም:: ደግነቱ ዘመዶቿ ሊቀበሏት ወደዋል:: አሁን አንድ ዓይኗ ጠፍቷል:: ሙሉ አካሏ ከእሷ አይደለም:: እንደልብ መውጣት መግባት አይሆንላትም:: ትናንት ስትሮጥ እንዳልነበር ዛሬ ከሰው እጅ ወድቃለች:: ይህን ችግር ይዛ ሌሎችን ማስቸገርና መቸገሩ በእጅጉ ይከብዳል:: ምርጫ አልነበራትም:: የዘመድ ቤትን ኑሮን ሳትወድ ተቀበለች::

ዘመዶቿ ብዙ ቤተሰብ አላቸው:: ልጆች ለማሳደግ ኑሮን ለማሸነፍ ይሮጣሉ:: ይህን የምታየው ማሬ በእንግድነቷ ተጨነቀች:: ያለሥራ፤ የልጆቹን እንጀራ መካፈሉ አሳቀቃት:: ሁሉም በእሷ የተማረሩ፤ የሰለቹ መሰላት:: ውሎ አድሮ ፍራቻዋ እውነት ሆነ:: ዘመዶቿ አፍ አውጥተው እሷን መያዝ፣ማኖር እንደማይችሉ ነገሯት:: ተምራ መለወጥ ለምትሻው ታዳጊ ውሳኔያቸው ከባድ መርዶ ሆነ::

ማሬ ግራ ገብቷታል:: ሀገር ቤት የምትመለስበት አንዳች ተስፋ የለም :: የዘመዶቿ ድንገቴ ውሳኔ እያስጨነቃት ነው:: አንድ ቀን ግን በአክስቷ ባል ጥረት የኑሮ መንገዷ ተቀየረ:: ተስፋ የዓይነስራውንና የአካልጉዳተኞች ማዕከልን በሥራ ተቀላቀለች:: ይህ መሆኑ ብቻ የማሬን ችግር አልፈታም:: አሁንም ቋሚ የመኖሪያ ቤት አላገኘችም::

ችግሯን የተረዱ አሠሪዎች በአንዲት ሻይ ቤት እንድታድር ፈቀዱላት:: ማሬ ማረፊያ ስታገኝ ፈጣሪን አመሰገነች:: እንዲህ መሆኑ ሌሎችን አላስደሰተም:: በድርጅቱ የሚሠሩ አንዳንዶች እገዛውን ከጥቅም ቆጥረው ተቃወሙ:: የማሬ ሕይወት ዳግም ከችግር ወደቀ:: በድንገት መጠጊያዋን እንድትለቅ ተወስኖ ከስፍራው ተባረረች::

ማሬ ግራ ተጋባች:: አሁን የቀድሞ ዘመዷቿን ከመለመን ውጭ ምርጫ አላገኘችም:: ሽሮሜዳን አልፋ አቀበቱን ወጣች:: ከግቢው ደርሳ ችግሯን አዋየች:: ዘመዶቿ ደግመው አልሰሟትም:: ወደመጣችበት እንድትመለስ ቁርጡን ነገሯት:: ባይተዋሯ ማሬ ሳግ እያነቃት ከግቢው ራቀች:: አሁን ተስፋዋ ተሟጧል:: ትሄድበት ትጠጋበት ጥግ የላትም:: ሆድ ብሏታል፤ ዕንባዋ በጉንጭ በአንገቷ ይወርዳል::

ማሬ ዊልቸሯን እየገፋች ከአንድ ፖሊስ ጣቢያ ደረሰች:: ታሪኳን ዘርዝራም እንደ ወንጀለኛ እጇን ሰጠች:: ችግሯን የተረዱ ኃላፊዎች ከበሩ ጥግ እንድታድር ፈቀዱላት:: ሕይወት ከፖሊስ ጣቢያ ደጃፍ ቀጠለ:: የዛሬን እንጂ የነገን የማታውቀው ማሬ የእለቱን እያመሰገነች ተኝታ ተነሳች:: የእንክርት ሕይወትን ለመደች:: አንድ ቀን ግን ከአንድ የሕግ ባለሙያ የሰማችው ምክር ከልቧ ገባ:: እሱ ያላትን ልትፈጽም ከራሷ ተስማማች::

### በከንቲባው ፊት...

ማሬ በእጇ ያለውን ማመልከቻ ይዛ ወደ አዲስ አበባ አስተዳደር ቀረበች:: አጋጣሚ ሆኖ ደጅ አልጠናችም:: ከሚመለከተው ሰው በግንባር ተገናኘች :: በወቅቱ የከተማዋ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ነበሩ:: ከንቲባ ኩማ ታሪኳን በወጉ አደመጡ፤ ችግሯን ከልብ ተረዱ:: ኃዘኗ ኃዘናቸው ሆነ:: አልዘገዩም:: ለማሬ አካል ጉዳት የሚመጥን ምቹ የቀበሌ ቤት እንዲሰጥ አስቸኳይ ትዕዛዝ አሳለፉ::

የጉለሌ ክፍለ ከተማና የሚመለከታቸው ሁሉ ለከንቲባው ትዕዛዝ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ሲተጉ ከረሙ:: ዊልቸር በወጉ የሚያስገባ፤ አመቺ መጸዳጃ ያለው ምቹ ቤት መኖሩ ተረጋገጠ:: ቤቱን ለማስረከብ በዕለተ ዓርብ ቀጠሮ ተይዞም ማሬ ተጠራች:: ፡ በተባለው ቀን ስፍራው ስትደርስ አስረካቢዎቹ ቤቱን አሳይተው «እንኳን ደስ አለሽ» አሏት::

እንደተባለው ቤቱ ለአካል ጉዳተኛ የሚመጥን፤ ለዊልቸር ጉዞ የሚያመች ነው:: ማሬ በደስታ ፈጣሪዋን አመሰገነች:: ቃል አክባሪ አስረካቢዎቿን ደጋግማ መረቀች:: ውል ለማሰር ለሰኞ ተቀጥራም ከግቢው ራቀች::

### የነበረው እንዳልነበረ...

ለማሬ ዕለተ ሰኞ ሲያዘግም ደርሷል:: ይህ ቀን ለእሷ ከሌሎች ዕለታት የተለየ ሆኗል:: ቀጠሮዋን አክብራ የደረሰችው የቤት ባለቤት የሰዎቹን መምጣት እየጠበቀች ነው:: ቁልፉ ከእጇ ገብቷል:: የቀራት ቢኖር የውል ስምምነት ብቻ ነው::

ድንገት አጠገቧ የደረሰው አስረካቢ ገጽታው እንደቀድሞ አልሆነም:: ዓርብ ዕለት የሰጣት ቤት በስህተት መሆኑን ደጋግሞ እየነገራት ነው:: ቤቱ ለእሷ እንደማይገባ ያሳወቃት ሰው ይመጥናቸዋል ያላቸውን ተረካቢዎች አቅርቦ ቁልፉን ከእጇ ነጥቋል:: ማሬ በሁኔታው ደንግጣ መፍትሔ ጠየቀች :: ኃላፊ ተብዬው ለእሷ የምትመጥነውን ትንሽዬ ቤት እየጠቆመ ከዚህ በኋላ ዳግም እንዳትጠይቀው በቁጣ አስጠነቀቃት::

ማሬ የነበረው እንዳልነበረ መሆኑ ገብቷታል:: ዳግመኛ ቃል የማውጣት አቅም የላትም:: የተባለውን ቤት ለመረከብ ከስፍራው ደርሳ ከመንገድ ቆማለች:: በሩ ላይ ያለው የእንጨት ድልድይ ወደግቢው ለመግባት አያመችም:: ይህን ያዩ ልበ መልካሞች ከነዊልቸሯ ተሸከመው ከቤቷ ደጃፍ አድርሰዋታል::

ቀጭኑን ጭቃማ መንገድ በመከራ አልፋ ከጠባቧ ጎጆ የደረሰችው ማሬ በጭንቀት ተውጣለች:: ለእሷ ይበጃል የተባለው ቤት በእጅጉ ሆድ ያስብሳል:: የበሩ መግቢያ ገደል ነው:: በግቢው መብራት ፣ ውሀና መጸዳጃ የለም:: እንደምንም ከቤት ተንሸራታ ገባች:: በዋዛ መውጣት ሳትችልም ቀናትን በረሀብና ጥማት ገፋች:: ቀበሌ በምልልስ ደጅ ጠናች:: ስለቤቱ ተስፋ ተነፈጋት:: «ጆሮ ዳባ ልበስ» ያሉት ኃላፊዎች እየተቀያየሩ ፊት ነሷት፤ ጀርባ አዞሩባት::

### ዓመታትን በዕንባ...

እነሆ ማሬ «ላንቺ ይሁን» በተባለው ቤት ኑሮን በሰቀቀን መግፋት ይዛለች:: በዚህ ቤት ያበሰለችውን መጉረስ ፣ የቀዳችውን መጠጣት አልተፈቀደላትም:: ከስራ መልስ ጎጆዋ ከገባች ተጠቅልላ ከመተኛት የዘለለ ምርጫ የላትም:: የጎረቤት ምግብ ቢሸታት፣ለአውደ ዓመት ጥሪ ቢደርሳት አንዲት ስኒ ቡና ፉት አትልም:: በቤቷ ካለው፤ ልቅመስ፤ ልጎንጭ ካለችም መፈጠሯን ትጠላለች፤ ከተፈጥሮ ትጋጫለች::


ማሬ ሁሌም በእጇ ያለውን እያየች ትራባለች፤ ትጠማለች:: ጠጥታ፣ላለመሽናት፤ በልታ ላለመጸዳዳት የወሰደችው ብቸኛ ርምጃ በረሀብ እየተሰቃዩ ፣በውሀ ጥም ማረር ሆኗል:: ከቤት ሆና ድንገት ሆዷ ቢንጓጓ ቀጥሎ የሚሆነውን እያሰበች ትጨነቃለች:: እንደሴት ልጅ ወግ ብዙ ያስፈልጋታል:: በቤቷ ገላዋን ብትታጠብ፤ ልብሷን ብታጥብ ትወዳለች:: ይህን ልሞክር ካለች ግን ችግሩ ይብሳል:: አንድም የአቅም ጉዳይ፤ ሌላም ወሀውን ትደፉበት ቦታ አታገኝም::

ማሬ ውላ ከምትገባበት፤ እንጀራ ቦታዋ ጉዳይዋን ጨርሳ ፣ከቤት ትደርሳለች:: የዓርብ ስንቋ እስከ ሰኞ ያዘልቃታል:: እህል ባፏ የሚዞረው ሥራ ስትገባ ነው:: በዚህ ስፍራ መጸዳጃ ታገኛለች :: እንደወጉ ትሆናለች:: ቤት የምትውልባቸው ቀናት ለዚህች ሴት የፈተና መሰላሎች ናቸው:: እየራባት የማትበላባቸው፤ እየጠማት የማትጠጣባቸው አስከፊ ቀናት:: ማሬ ከሁሉም በዘመነ ኮረና ያሳለፈችውን የጨለማ ጊዜ አትረሳም:: የዛኔ መሥሪያ ቤቷ በመዘጋቱ ከቤት የምትወጣበት ምክንያት አልነበረም:: በወቅቱ በረሀብ ተቆራምዳለች፣ጥቂት ብዙ ዋጋ ከፍላለች:: ለእሷ አሁንም ያለችበት ቤት የመቃብር ያህል ነው:: ያለሕይወት የሚጋደሙበት፣ያለተስፋ የሚያድሩበት የጨለማ ኑሮ ::

### እረ ! መሳ ምቱ...

ወዳጆቼ! «ኑሮ ካሉት» እንዲሉ ሆኖ ከጣራው ሥር ሕይወት እንዲህ እየተኖረ ነው:: ቤት ብቻውን ትርጉም የለውም:: ፍቺው የሚታወቀው ገበናን ሸፍኖ በወጉ በልተው፣ጠጥተው ሲያድሩበት፤ ጭምር ነው:: አሁን ለዚህች የተጨነቀች ነፍስ አስቸኳይ መላ ያሻል:: ይህ ይሆን ዘንድ የመልካም ሰዎች ልብ፤ የቀበሌው አመራር ነን ባዮች ይሁንታ ያስፈልጋል:: ወገን ባለበት፣መንግሥት በቆመበት ሀገር ይህ መሰሉ ታሪክ ሊሰማ አይገባም :: በሮች ይንኳኩ ፣ዕንባዎች ይታበሱ::

# ስፖርት



# ዋልያዎቹ ከከፍታው እንዳይወርዱ

ቦጋለ አበበ

የኢትዮጵያን እግር ኳስ ከዳር እስከ ዳር ያነቃቃና ሕዝቦቿንም ያስፈነጠዘው የድል ስሜት አሁንም አልበረደም። ብርቅዬዎቹ ዋልያዎች በሀገራቸው ዓለም አቀፍ ጨዋታን ማድረግ የሚያስችል ስታዲየም በማጣታቸው ወደ ገለልተኛ አገር ማላዊ ተሰደው ጣፋጩን ድል ከባሕርማዶ ለሕዝባቸው ልከዋል። ዋልያዎቹ ከስልሳ ዓመት በኋላ የአፍሪካ እግር ኳስ ኃያሏን አገር ግብጽን ማሸነፋቸው ድል ማድረጋቸው ከስፖርት የበለጠ ብዙ ትርጉም እንዳለው ተደጋግሞ ተነግሯል። በዚህ ታሪካዊ ድል በተመዘገበበት ጨዋታ ዋልያዎቹ ፈርኦኖቹን አሳምነው ያሸነፉበት መንገድ እንዲሁም ቴክኒካዊ ጉዳዮችን አንስቶ ዛሬ ላይ መተንተንም አንባቢን ማሰልቸት ነው። በአጭሩ ዋልያዎቹ ከተከላካይ እስከ አማካኝ፣ ከአማካኝ እስከ አጥቂ መስመር ድንቅ ነበሩ ብሎ ማለፍ በቂ ነው።



ሁሉም ባለድርሻ አካላት የዋልያዎቹ ድል እያጣጣሙ ስለቀጣዩ የቤት ሥራ ከወዲሁ ማሰብና መዘጋጀት አለባቸው፣

ዋልያዎቹ ለዘመናት ዝቅ ተደርገው ከሚታዩበት ደረጃ ወደ ከፍታው ተመልሰዋል። ከዚህ ከፍታ እንዳይንሸራተቱ ምን ይደረግ የሚለው ጉዳይ የሁሉም የቤት ሥራ መሆን አለበት። ለዚህም ብዙ መስተካከል ካለባቸው አስተዳደራዊ ዝርዝር ነጥቦች ውስጥ አንኳሮቹን መጠቆም ወይም ማስታወስ ተገቢ ነው። ይህ የዋልያዎቹ ልብን የሚያሞቅና የሁሉም ኩራት የሆነ ድል ነገም እንዲቀጥል ከአሰልጣኝ ውበቱ አባተ ጀምሮ በፌዴሬሽን በኩል ከወዲሁ ዝርዝር እቅዶችን አውጥቶ መዘጋጀት ቀዳሚ ጉዳይ ነው። አንድ አሰልጣኝ ምን ጊዜም ከትልቅ ድልም ይሁን ሽንፈት በኋላ ቀጣይ ትኩረቱ ከፊቱ ያለው ፍልሚያ ነው። የዋልያዎቹና ፈርኦኖቹ ፍጥጫ አሁንም አላበቃም። በቀጣይ መስከረም ላይ የመልሱ ጨዋታ በካይሮ ይደረጋል። በሐሙሱ ምሽት ጨዋታ አስደንጋጭ ሽንፈት የገጠማቸው ፈርኦኖቹም ከደረሰባቸው ትችት(ውግዘት ማለት ይቀላል) አገግመው ሕዝባቸውን በተሻለ ድል ለመካስና ዋልያዎቹን ለመበቀል ያንን ቀን እንደሚጠብቁት እርግጥ ነው። ለዚህ ዋልያዎቹም ከወዲሁ በስነልቦናም በአካል ብቃትና ቴክኒካዊ ጉዳዮች ራሳቸውን ማዘጋጀት እንዳለባቸው ይጠፋቸዋል ተብሎ አይታሰብም። የአሁኑ ድል አንዴ ተመዝግቧል፣ታሪክም ያስታውሰዋል። የበለጠ ትርጉም ያለው ድል እንዲሆን ግን ስለመልሱ ጨዋታም ማሰብ ያስፈልጋል። ዋልያዎቹ ከየትኛውም የአፍሪካ ብሔራዊ ቡድን ያነሰ አቅም እንደሌላቸው አሳይተዋል። በእርግጥ ከዚህ ቀደም በተለይም ባለፈው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ እንደ ኮትዲቯር ያሉ ግዙፍ ቡድኖችን በማሸነፍ ብልጭ ብሎ ሳናጣጥመው የሚጠፋ ተስፋ አሳይተውናል። ነገር ግን ቀጣይነት የለውም። ለምን? ይህን በአግባቡ አጢኖ ዋልያዎቹ ፈርኦኖቹን በረቱበት ጨዋታ የነበራቸውን በውጤት የታጀበ አቅም እንዴት በቀጣይ ጨዋታዎች መድገም ይቻላል የሚለውን ጉዳይ የአሰልጣኝ ቡድን አባላትና የቴክኒክ ኮሚቴው ጊዜ ወስዶ ሊመለከተው ይገባል። ጎን ለጎንም ፌዴሬሽኑ የተሻሉ ከሚባሉ ብሔራዊ ቡድኖች ጋር ዋልያዎቹ በርካታ የወዳጅነት ጨዋታዎችን በማድረግ አቋማቸውን እየፈተሹ በጎደለው የሚሞሉበትን፣ የተጣመመውን የሚያቀኑበትን እድል መፍጠር ለነገ የሚለው የቤት ሥራ መሆን የለበትም።

ፌዴሬሽኑ ዋልያዎቹ ከሜዳቸው ውጪ ጨዋታዎችን ለማድረግ በመገደዳቸው በአንድ ጨዋታ ለሜዳ ኪራይና ለመሳሰሉት ብቻ እስከ ሃምሳ ሺ ዶላር ወጪ እንደሚያደርግ ባለፈው መግለጫው ጠቁሞ ነበር። ይህም ካለው አቅም አንጻር ብዙ እንደማያራምደውና ጨዋታዎችን ከአገር ውጪ ሄዶ ማድረግ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደሚሳነው ስጋቱን ገልጾ ነበር። ይህ ዋልያዎቹና በአጠቃላይ የኢትዮጵያ እግር ኳስ በተነቃቃበት በዚህ ወቅት በሕዝብ ስሜት ላይ ውሃ ሊከልስ የሚችል አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ነገ ዋልያዎቹ በዚህ መነቃቃት ላይ ወደ አፍሪካ ዋንጫ የማምራት እድላቸው እየሰፋ ሲሄድ ይሄ አይነቱ እንቅፋት ሊነሳ አይገባም። መንግሥትም ይሁን የሚመለከተው አካልና ባለሃብቶች ድሎች ሲመዘገቡ ጮቤ ከመርገጥና ጊዜያዊ ሽልማቶችን ከማዥጎድጎድ በዘለለ ስለ ዋልያዎቹ ቀጣይ መንገድ ማሰብ አለባቸው።

ይህን የፋይናንስ ጉዳይ እንቅፋት እንዲሆን ካደረጉ ምክንያቶች ዋነኛው ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ጨዋታዎችን በሜዳዋ የሚያስተናግድ ስታድየም አለመኖሩ ነው። ከዚህ ቀደም ይህ የስታድየም ችግር ሲነሳ "ለየትኛው እግር ኳስ ነው" የሚሉ ምላሾች ከተለያዩ ወገኖች ሲሰጡ ማየት የተለመደ ነው። የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አሕመድም ባለፈው የፓርላማ ንግግራቸው በስታድየሞች ዙሪያ በሰጡት ምላሽ "መጀመሪያ ሥርታችሁ የተሻለ ነገር አሳዩ፣አፍሪካ ዋንጫና ኦሊምፒክ ላይ ደጋግማችሁ በመሳተፍ ውጤት አሳዩን" በማለት መናገራቸው ይታወሳል። እርግጥ ነው መንግሥት ደረጃቸውን የጠበቁ ስታድየሞች እንዲኖሩ ትኩረት ለመስጠት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያሉትን ማሳያዎች ይፈልግ ይሆናል። ዋልያዎቹ በፈርኦኖቹ ላይ የተቀዳጁት ድል ለዚህ በቂ ነው ማለት ባይቻልም የመንግሥትን አንጀት ለማራራት አያንስም። ስለዚህም ይህን የተጀመረ መነቃቃት አስቀጥሎ ዋልያዎቹን በቀጣዩ የአፍሪካ ዋንጫ ዳግም ለመመልከት ሌላው ቢቀር አንድ ስታዲየም እንኳን ቢሆን ርብርብ ተደርጎበት የመጨረሻዎቹን የማጣሪያ ጨዋታዎች ለማድረግ ዋልያዎቹ ከስደት ቢድኑ መልካም ነው።


### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት ስም፡ ሳኖፊ አቬንትስ ደች ላንድ ጂኤምቢኤች (SANOFI-AVENTIS DEUTSCHLAND GmbH) አድራሻ፡ Brüningstrasse 50, 65926 Frankfurt am Main, Germany
2. የማመልከቻ ቁጥር፡FTM/5532/2014
3. የንግድ ምልክት፡ **LASIX**
4. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በ28/07/2011 ዓ.ም በVol-LXXVIII No. 208 አዲስ ዘመን ላይ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው።
5. የንግድ ምልክቱ እ.ኤ.አ ከ16/12/2021 እስከ 16/12/2028 እ.ኤ.አ ታድሷል፡፡ በመሆኑም ማንኛዉም ሰዉ ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-274 4/10/2014 (11/6/2022)

### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት ስም፡ ሳኖፊ (SANOFI) አድራሻ፡ 54 rue La Boétie, 75008 Paris, France
2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/5601/2014
3. ንግድ ምልክት፡ **PLAVIX**
4. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በ02/01/2008ዓ.ም በVol-LXXV No. 002 አዲስ ዘመን ላይ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው።
5. የንግድ ምልክቱ እ.ኤ.አ ከ22/12/2021 እስከ 22/12/2028 እ.ኤ.አ ታድሷል፡፡ በመሆኑም ማንኛዉም ሰዉ ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-274 4/10/2014 (11/6/2022)

### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት ስም፡ (ዱራሴል ባትሪስ ቢቪቢኤ ሊሚጽት) DURACELL BATTERIES BVBA LIMITED አድራሻ፡ Nijverheidslaan 7, 3200 Aarschot, Belgium.
2. የማመልከቻ ቁጥር፡FTM/5459/2014
3. የንግድ ምልክት፡ **DAIMON**
4. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በ26/02/2009 ዓ.ም በVol-LXXVI No. 056 አዲስ ዘመን ላይ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው።
5. የንግድ ምልክቱ እ.ኤ.አ ከ10/12/2021 እስከ 10/12/2028 እ.ኤ.አ ታድሷል፡፡ በመሆኑም ማንኛዉም ሰዉ ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-274 4/10/2014 (11/6/2022)

### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት ስም፡ ዘ ፕሮክተር ኤንድ ጋምብል ካምፓኒ (THE PROCTER & GAMBLE COMPANY) አድራሻ፡ One Procter & Gamble Plaza, Cincinnati, Ohio 45202, United States of America
2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/3813/2014
3. የንግድ ምልክት፡ **PAMPERS BABY-DRY**
4. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በ01/09/2011 ዓ.ም በVol-LXXVIII No. 241 አዲስ ዘመን ላይ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው።
5. የንግድ ምልክቱ እ.ኤ.አ ከ01/07/2021 እስከ 01/07/2028 እ.ኤ.አ ታድሷል፡፡ በመሆኑም ማንኛዉም ሰዉ ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-274 4/10/2014 (11/6/2022)

### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት ስም፡ (አምካ ፕሮዳክትስ (ፕሮፕራይተሪ) ሊሚትድ) AMKA PRODUCTS (PROPRIETARY) LIMITED አድራሻ፡ 14 Ellman Street, Sunderland Ridge, Pretoria, Gauteng, South Africa
2. የማመልከቻ ቁጥር፡FTM/2547/2014
3. የንግድ ምልክት፡ **STA-SOF-FRO**
4. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በ11/04/2000 ዓ.ም በVol-LXVII No. 101 አዲስ ዘመን ላይ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው።
5. የንግድ ምልክቱ እ.ኤ.አ ከ03/12/2021 እስከ 03/12/2028 እ.ኤ.አ ታድሷል፡፡ በመሆኑም ማንኛዉም ሰዉ ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-274 4/10/2014 (11/6/2022)

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም አልመአብ ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03 01 A13267 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር 6FPGXXMJ2GEU86826 ሞዴል RANGER የሞተር ቁጥር PF2H-GEU86826 የሊብሬ ቁጥር 142986 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 23/9/2014 አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት

### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት ስም፡ ፕሮክተር ኤንድ ጋምብል ካምፓኒ (The Procter & Gamble company) አድራሻ፡ One Procter & Gamble Plaza, Cincinnati, Ohio 45202, USA.
2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/1390/2013
3. ምልክት፡ **HEAD & SHOULDERS**
4. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በ17/12/2011 ዓ.ም በVol-LXXVIII No. 347 አዲስ ዘመን ላይ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው።
5. የንግድ ምልክቱ እ.ኤ.አ ከ01/11/2020 እስከ 01/11/2027 እ.ኤ.አ ታድሷል፡፡ በመሆኑም ማንኛዉም ሰዉ ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-274 4/10/2014 (11/6/2022)

የባለንብረት ስም ጌትነት በሪሁን አባተ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A65806 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር MROHR29G902030821 ሞዴል KUN25L-CRMSHW የሞተር ቁጥር 2KD-5011749 የሊብሬ ቁጥር 393414 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 30/9/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት